## አዘጋጆች

ደነደአ ቦጋለ

ከበቡሽ ለሜሳ

ለሚ ቤኛ

## ተርጓሚዎች

ምናሴ ተክሌ

ደጀኔ ሮቢ

ወላንሳ ሸመልሽ

ተዋበች አበበ

## የጥራት ቁጥጥር

ደቀቦ ጉዬ

## ግራፊክስ

ታደሰ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምዕራፍ 1 የስነ-ጥበባዊ ግንዛቤ........................................................1

1.1መሰረታዊ የዲዛይን አለባውያን ጥቅምና ድርሻ..................................3

1.2 የኢትዮጵያ ሙዚቃ እና ባህላዊ ዉዝዋዜ ........................................18

1.3 የስነ-ቲያትር እና ስነ-ፊልም ልዩነት ...........................................27

ምዕራፍ 2..................................................................................37

የስነ-ጥበብ ፈጠራ ችሎታ.............................................................37

2.1. የውሃ ቀለም ቅብና ህትመት ስራ ..............................................38

2.2.የሶልፌጅዮ ልምምድ በትዝታና በባቲ ቅኝት...................................78

2.3.ባህላዊ ዉዝወዋዜ.......................................................................94

2.4.የስነ-ትያትርና ስነ-ፊልም ሃሳብ መፃፍ............................................96

ምዕራፍ 3.................................................................................108

የታሪክ እና የባህል ነባራዊ ሁኔታ......................................................108

3.1 የኦሮሞ ዘፋኞች እና ተወዛዋገ*ች የሙዚቃ ታሪክ.........................109

3.2 ባህላዊ ጌጣጌጦች ..................................................................119

3.3 በሀገር በቀል እውቀት ስነ-ትያትር እና ስነ- ....................................123

ፊልምን ማሳየት.........................................................................123

ምዕራፍ 4..................................................................................137

የሥነ-ጥበባት መስዕቦች ........................................................................ 137

4.1 የስነ-ጥበባት ስራ ጥቅም በተግባር ማሳየት ....................................... 138

4.2 ሀገር በቀል ስነ-ጥበባት ስራዎች ........................................................ 138

4.2.3. የሀገር በቀል የትያትር ስራዎች.................................................. 146

ምዕራፍ 5.............................................................................................. 153

የስነ - ጥበባት ትስስር ............................................................................ 153

5.1 የሽክላ ስራና ማሳመሪያ ሙ.ያ ቅደም ተከተል................................ 153

5.2 የስነ-ትያትር ትምህርት ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነት ..................... 156

5.3 ትያትር ከጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ጋር ያለው ትስስር ............................................................................................. 158

# ምዕራፍ 1

# የስነ-ጥበባዊ ግንዛቤ

## የዚህ ትምህርት ምዕራፍ ዉጤቶች፤

## በዚህ ትምህርት ምዕራፍ መጨረሻ፤

- የዲዛይን አካላት ትርጉም እና ምንነትን ትረዳላችሁ፡፡
- መሠረታዊ የዲዛይን አካላትን ትለያላችሁ፡፡
- የዲዛይን አካላት ያላቸውን ጥቅሞች ትለያላችሁ፡፡
- የሙዚቃ እና ውዝዋዜን ግንኙነት ለይተህ/ሽ ታሰላስላችሁ፡፡
- የሶልፌጅዮ ትርጉም እና ፒች (የድምጽ ከፍታና ዝቅታ) ትረዳላችሁ፡፡
- በክልላችን የሚገኙ ዘፋኞች ታሪክ ታውቃላችሁ፡፡
- የስነ-ስየቲያትርእና የስነ-ፊልም ልዩነትን ትረዳላችሁ፡፡

## መግቢያ

ለአንድ ዲዛይን መፈጠር የዲዛይን አካላት ጥምረት ወይም ቅንጅት ወሳኝ ናቸው፡፡ አንድ ዲዛይን በትክክል ሙሉ ነው የሚያስብለው የዲይዛን አካላት በሚገባ ሁኔታ ሲቀናጁ ወይም ሲሰሩ ነው፡፡ ስለዚህም ፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አስፈላጊው

ፅንሰ- ሃሳብ የዲዛይን ስነ-ጥበብ እና የዲዛይን አካላትን በስፋት ይዞ ቀርቧል፡፡

ስድስተኛ (6) ክፍል በተማራችሁት ትምህርት መሠረት የሜጀር፣ ማይነር፣ፒችና የቁልፎች ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታና ሚና/ድርሻ ተገልያአል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ የሙዚቃ፣የባህል ውዝዋዜ፣ሶልፌጅዮ፣ያገራችን ሙዚቃ ጠቀሜታና ድርሻ፣የሙዚቀኞችና ተወዛዋገሮች ታሪክና የመሳሰሉትን ትማራለህ/ሽ::

ባለፉት ጊዜያቶች የስነ-ትያትር ምንነት ፣የትያትር ተዉኔተ ጽሁፍ አካላት ፣አለባበስና እቃዎች በትያትር ማሳየት ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ እንዲሁም የስነ-ጥበብ ትምህርት ከሌሎች ትምህርት ጋር ያለውን ግንኙነት ተምረሃል/ሻል፡፡ በተጨማሪም፤ የተዉኔት ጽሁፍ ምንነትና ዝግጅት በራሳችን ሀሳብ ስነ-ትያትርና ስነ-ፊልም በመጠቀም በዚህም ክፍል የስነ-ፊልምና ስነ-ትያትር ልዩነት፣አጠቃቀም፣ድርሰት እንዲሁም የሀገር በቀል እውቀት በመጠቀም ለማህበረሰቡ አጉልቶ ማሳወቅን ትማራለህ/ሽ፡፡

## 1.1መሰረታዊ የዲዛይን አለባውያን ጥቅምና ድርሻ

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት፤**

**በዚህ ትምህርት ርዕስ መጨረሻ ላይ፤**

- የዲዛይን ትርጉም ትገልጻላችሁ፡፡
- የዲዛይን አለባውያንን በመለየት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የዲዛይን አለባውያን ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡

**ውይይት 1**

ቤት ለመሥራት የተለየ ዲዛይን ወይም ሌላ ነገር ለመስራት የተሳለ ዲዛይን ወይም ስዕል አይታችሁ ታውቃለችሁ? በየቡድናችሁ በመሆን ተወያዩና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

### 1.1.1.የዲዛይን ትርጉም/ፍቺ

የዲዛይን ጥበብ (ሙያ) ከቴክኖሎጂና ከሰው ልጅ እድገት ጋር እኩል እያደገ የመጣ ነው፡፡ ከድሮ ዘመን ጀምሮ የሰው ልጅ ባህሉንና ታሪኩን ዲዛይንን በመጠቀም ሲያንፀባርቅ የቆየና አሁንም እየተጠቀመበት ያለ ነው፡፡ አንድ ሰው ዲዛይን ከመስራቱ በፊት ዲዛይኑ እንዴት እንደሚሰራና ምን እንደሚመስል ማወቅ ይኖርበታል፡፡

ዲዛይን ማለት የዕቃ ወይም ስዕላዊ ስራ እቅድ ወይም የስራ ሀደት መመሪያ (ንድፈ-ትልም) ማለት ነው፡፡ እንዲሁም የመነሻው የስዕላዊ እቅድ ወይም የፎርምን ፍሰት የያዘ ነው፡፡ ይሁንና፣ ግልጽ ያልሆነ ንድፈ-ትልም ሳይኖራቸው የሚሰሩ እጅ ስራና ሎሎችም በዲዛይን ስራ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

ዲዛይን ከስነ-ጥበብ ስራዎች አንዱ ሆኖ ሰዓሊው በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የአንድ የሰውነት ፍሰት ወይም ፎርም በማቀናጀት ትርጉም

ባለው (ሙሉ በሙሉ) መንገድ የሚፈለገውን መልዕክት የሚያስተላልፍበት ነው፡፡ እንዲሁም ተፈጥሯዊና ሰው-ሰራሽ የፎርም ይዘቶችን በማቀላቀል፣በመጨመር ወይም በመቀነስ የተፈለገውን መልእክት የሚያስተላለፍበት መንገድ ነዉ፡፡ይህም የሚሆነው ፈጠራው ለዐይን በሚያምር ሁኔታ መልእክት የሚችል ሆኖ ስገኝ ነዉ፡፡ያማረ ዲዛይን ለመስራት፣የስራዉ ባህርይ እና ለማስተላለፍ የተፈለገው መልዕክት በደንብ ወይም በጥልቀት አስቀድሞ ሊታወቅ ይገባል፡፡

## 1.1.2.የዲዛይን አለባውያን

**ውይይት 2**

የዲዛይን አካላት አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ በየቡድናችሁ ተወያዩበት እና ለክፍሉ አቅርቡ፡፡

አንድ የዲዛይን ስራ ይዘታዊ ቅንብር መገለጫ አሉት፡፡ ይህ እንደ ግባት የሚያገለግለው ይዘታዊ ቅንብር ደግሞ የዲዛይን አካል ነው፡፡ የዲዛይን አካላት ማለት፡- የንድፍ ግንባታ ወይም ቅንብር የሚፈጥረው የዲዛይኑ ስራ ማለት ነው፡፡ ለሚፈጠረዉ ዲዛይን ስራ መነሻ ነው፡፡ ሰባት (7) የዲዛይን ክፍለ-አካላት አሉ፡፡እነርሱም፣

1. መስመር
2. ቅርፅ(ዝርገ-ቅርጽ)
3. ፎርም(ዝርገ-ገጽ)
4. ቀለም
5. ቦታ
6. ለስላሳማነት ወይም ሻካራማነት(ጥራት)
7. ፍካት(ብርሃንና ጥላ)

የዲዛይንና የስነ-ስዕል አለባውያን አንድ ስም ቢኖራቸውም በተወሰነ ደረጃ የትርጉም ልዩነት አላቸዉ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ አለባውያን የዲዛይኑን ይዘት የሚገልጹ በመሆናቸው ነው፡፡፡


**ለዲዛይን ሥራ መስመሮችን በተለያየ መንገድ መጠቀም**

**መስመሮች የተለያየ ባህሪያት አላቸው፡፡ እነሱም፡-**

- **መርዘምና ማጠር ወይም መካከለኛ መሆን**
- **ወፍራምና ቀጭን መሆን**
- **ለስለሳና ሸካራ መሆን**
- **ቀጣይነት**
- **አቅጣጫ መቀየር**

## የመስመር አጠቃቀም

መስመር ከሚሰጣቸው ጥቅሞች ውስጥ ፊደላትና ቁጥሮችን ለመፃፍ የምንገለገልበትን ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ ፊደላትም ሆኑ ቁጥሮች የተለያዩ መስመሮች በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈጠሩ እንደሆኑ ባለፉት ክፍሎች ተምረቸዋል፡፡ በመሆኑም ፊደል ወይም ቁጥር ለመፃፍ በመጀመሪያ እጅ ለመፍታት ለኒደረግ ልምምድ በተለያዩ መስመሮች ላይ መለማመድ ያስፈልጋል፡፡



በዲዛይን ስራ ውስጥ የመስመር ጥቅም ይህ ብቻ አይደለም፡፡ መስመሮች በትክክል ከተቀናጁ ማራኪና ትርጉም ያለው ዲዛይን ይሰጣሉ፡፡ ይህም የራሱ የሆነ ህግና ሂደት አለው፡፡

- ✓ ማቀናጀት
- ✓ የገፅታ ሁኔታ
- ✓ ለዓይን ማራኪነት
- ✓ እንቅስቃሴ ይፈጥራል

በአጠቃቀም ላይ በመመስረት መስመሮች እንደሚከተሉት ይከፈላሉ፡፡

## ሀ. ከፍታ መስመር (እንደርከኔ)

የከፍታ መስመር (contour line) በተከታታይነት በመሰመር የስዕል መጨረሻው ጠርዝ በጥልቀት ተሰምሮ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የመስመር አይነት፤ ጠርዝን ወይም የዲዛይኑ ወይም ንድፉ መጨረሻ ስፍራ ለመፍጠር የሚያገለግል ነው፡፡ የከፍታ (የኮንቱር) መስመር ከሌሎች የስዕል መስመሮች ይልቅ በተደጋጋሚ በስዕሉ ላይ እና በቅርጹ ውጭአዊና ውስጣዊ ስፍራዎች ላይ የሚፈጠር ነው፡፡




ስዕል 8፡የኮንቱር መስመር የሚሳይ ስዕል

## ለ. የንድፍ መስመር

እርሳስን ወይም ሌሎች የስዕል (የመሳያ) መሣሪያን በመጠቀም ፍጥነት ባለዉ ሁኔታ የሚሰራ ስዕላዊ መስመር ነው፡፡ ይህ መስመር ድርጊትን ፣ እንቅስቃሴንና ተግባርን የሚያሳይ ነዉ፡፡

.



ስዕል 9፡የንድፍ መስመርን የሚያሳይ ስዕል

## ሐ. እምፐላይድ መስመር

የአምፐላየድ መስመሮች የሚፈጠሩት የሰው ልጅ በሚያሰምረው ወይም የተለያዩ እቃዎችን በመቀናጀት ሳይሆን ከርቀት የሚታዩ መስመሮች ናቸው፡፡ ይህ ማለት ከርቀት የሚታዩ ነገሮች በራሳቸው ግዜ ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ለየት ያለ መስመር ማለት ነው፡፡ በሚሰራው ስራ ላይ ተሞርኩዞ ምናባዊ ሀሳብ በማመንጨት ተጨባጭ አድርገን የምንወክልበት ነው፡፡



ስዕል 10፡እምፐላይድ መስመርን የሚያሳይ ስእል



## መ. የቆር መስመር (ውጫዊ መስመር)


ይህ መስመር ብዙውን ግዜ የስዕሉ ውጫዊ (ድንበር) ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ስለዚህም በዲዛይን እና በእቃዎች ጠርዝ ላይ ይገኛል ማለት ነው፡፡

ስዕል 11.የቆር መስመርን የሚያሳይ ስዕል

## ሠ. ካለግራፍ መስመር

ካለግራፍ ማለት ውበት ያለው የእጅ ፅሁፍ ሲጻፍ ማለት ነው፡፡ በስነ-ጥበብ እና ዲዛይን ስራ ውስጥ በሚያምር እጅ ጽሁፍ ከምንመለከተው ነው፡፡

ነገሮች ሚዛናቸውን ጠብቀው ስለሚቆሙ ረጅም መስለው እንዲታዩ ያደርጋቸዋል፡፡ በስዕል ውስጥም ቆሞ ያለ ነገርን ለማሳየት ያገለግላሉ፡፡



## ተግባር 1

**የመስመር አጠቃቀምን የሚያሳዩ ስዕሎችን በማየት ሌላ ስዕል ሰርታችሁ ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡**

## ሀ. ቅርፅ(ዝርገ-ቅርፅ)

**መልመጃ 1**


ቅርፅ ማለት ምን ማለት ነው?

ቅርፅ ከዲዛይን አካላት አንዱ ሲሆን ርዝመት እና ቁመት እንዲሁም እኩል አካል ያለዉ ሆኖ በመስመር የሚገለፅ ነው፡፡ የመስመሮች ጫፍ በዲዛይን ውስጥ ሲገናኙ እና ስፍራን ስሸፍኑ የሚፈጠር ነዉ፡፡

የቅርፅ አይነቶች ሁለት ናቸዉ፡፡እነርሱም፤

1. መሰረታዊ ቅርፅ
2. ኢ-መሰረታዊ ቅርፅ/መሰረታዊ ያልሆነ ቅርፅ/

## መሰረታዊ ቅርፆች፡- ጂኦሜትሪካል/



መሰረታዊ ቅርፅ ያላቸው ሆኖ ማዕዘንም ቅርፅ ኖሯቸው በሒሳብ ትምህርት ውስጥም የተለያዩ የቅርፅ መልኮች ለማሳየት የምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡

እነዚህ ቅርጽዎች በአብዛኛው ሰው ሰራሽ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በቀላሉ የተለያዩ መሳሪያዎች በመጠቀም የሚሰሩና ምቹ የሆኑ ናቸው፡፡

## ኢ-መሰረታዊ ቅርፆች/መሰረታዊ ያልሆኑ ቅርፆች

እነዚህ ቅርፅዎች በአብዛኛው ተፈጥሮአዊ የሆኑ ነገሮች ላይ የሚታዩ ዘዌ /ማዕዘን/ ለመለካት አስቸጋሪ የሆኑ መልኮች ናቸው፡፡ለምሳሌ፡- የደመና ቅርጽ፣የዛፍ፣ ቅጠልና የመሳሰሉት አካላት ላይ ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ሁሉም ነገሮች ከቅርጽ እንደሚገነቡ ሁሉ የዲዛይን አካላትንም ከተለያዩ የቅርፅ ዓይነት መገንበት ይቻላል፡፡



እነዚህ ቅርፆችም ቅብ የተቀቡ፣ፎቶ አልያም የቅብ አልባ ስእሎች ላይ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

### ሐ. ፎርም


#### ተግባር 3

ፎርም ማለት ምን ማለት ነው?

ፎርም ማለት ፡- ከዲዛይን አካላት አንዱ እና ከቅርፅ ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ግን ልዩነቱ በስነ-ስዕል ውስጥ ርዝመት፣ስፋትና ቁመት ኖሮት አንድ ፊዚካላዊ አካል ከራሱ ሰውነት ጋር ያለውን ፍሰት /ውህደት በስዕል ውስጥ ብቻ የምንመለከተው ነው፡፡

ፎርም በቅርፅ ላይ ተጨማሪ የሆነ አካል/ምልከታን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ለምሳሌ ክብ ቅርፅ ለጥ ያለ አካል ያለው ሆኖ ቁመትና ርዝመት ኖሮት በስዕል ውስጥ ብቻ የምንመለከተው ነው፡፡ ነገር ግን በቅብ ወይም በእርሳስ ምት ብርሃንና ጥላ ሰርተን ወደ እሰፊር በመቀየር የኳስን ቅርፅ ይይዛል፡፡በዲዛይን ውስጥ ፎርም በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም፤

1. መሠረታዊ ፎርም
2. ኢ. መሠረታዊ (ተፈጽጥሮአዊ ዝርገ-ገጽ)



ስዕል 13፡ መሠረታዊ እና መሠረታዊ ያልሆኑ ፎርሞች የሚያሳይ ስዕ

ጂኦሜትሪካል ፎርም ተመጣጣኝነት እና ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ሆነው በአብዛኛው ተፈጥሮአዊ በሆኑ ነገሮች ላይ የማይገኙ ናቸው፡፡ ስለዚህም በአብዛኛው ሰው-ሰራሽ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚታዩ ናቸውማለት ነዉ፡፡ ነገር ግን ጂኦሜትሪካል ያልሆኑ ፎርሞች ተመሳሳይ ያልሆኑ ገፅታን ተጎናፅፈው በአብዛኛው ግዜ ተፈጥሮአዊ ቁሶች ላይ የሚታዩ ናቸው፡፡ ነገሮች በተፈጥሮ እንዳሉ ሁሉ ፎርሞችም በተፈጥሮ በተለያዩ ቁሶች ላይ እንመለከተዋለን፡፡ ለምሳሌ፡ -ድንጋይ፣ዛፍ፣የመሬት አቀማመጥ እና የመሳሰሉት ላይ ይታያል፡፡ በተጨማሪ፣ መሰረታዊ እና ጠቃሚ የሆኑ ፎርሞች ደግሞ ሉል ( እስፊር) ኪዩብ፣ኮን፣ሲሊንደር፣ፒራሚድ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ርዝመት፣ቁመት እና ስፋት ኖሯቸው በስዕል መልክ ሲገለጹ ፎርም ይሆናሉ፡፡ ሰው-ሰራሽ ፎርሞች በሒሳብ ትምህርት ውስጥ እንደ ጂኦሜትሪካል ቅርፅ ሆነው የሚያገለግሉ፣ተፈጥሮአዊ እና ኦርጋኒክ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### መ.ፍካት (ብርሃንና ጥላ)

ብርሃን እና ጥላ (ፍካት) አንዳንዴ እንደ ቶን ይተረጎማል፡፡ቶን የአንድ ነገር ብርሃማነት ወይም ጥቁረት ደረጃ ቢለያይ ብርሃን እና ጥላ ተብሎ ይጠራል፡፡


ፍካት በአንድ ዲዛይን ስራ ውስጥ ስዕሉ ያለውን የብርሃን እና ጥላ መጠን የሚገልጽ ወይም የሚሳይ ነው፡፡ ብርሃን በስዕሉ አካል ላይ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የፍካት ደረጃ ይጨምራል፡፡ ነገር ግን የጥላ መጠኑ እየጨመረ ሲሄድ የፍካት ደረጃው ይቀንሳል፡፡ ስለዚህም፡- ተማሪዎች ስዕልን ስትስሉ የብርሃን የጥላ መጠን እንደ አስፈላጊነቱ ማመጣጠን አስፈላጊ ነው፡፡

ፍካት /ቫልዩ/ ንድፍና ቀለም ቅብ ለመስራት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የብርሃን እና ጥላ በስዕሉ ላይ በማቀናጀት ስዕሉ ውበት እና ትርጉም እንዲኖረው በማድረግ የተቀናጀ መልእክት እና የዐይን ስበት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ /ፍካት በባህሪው ቁመትና ርዝመት ያለው ሆኖ በአይናችን ብቻ ስዕሉን በማየት የምንረዳው የሆናል፡፡ ፍካትና ቀለም ቅብ በስነ-ስዕል ውስጥ ተቀራራቢ የሚያደርጋቸው ነገሮች አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ፡- ብርሃን እና ጥላን ሁሉም የዲዛይን ስራ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ቢሆንም የቀለም ቅብ ሁል ጊዜ ፍካት ሊኖረው አይገደድም፡፡ ስለዚህም የብርሃን እና ጥላ በስዕል ውስጥ ያላቸው ከፍተኛ ልዩነት የስፍራውን ጥልቀት ሊገልፅ የሚችል ሆኖ፤ በተጨማሪም ስሜት እና ሁኔታ በስዕላችን ላይ እንድንሰራ ይረዳል፡፡

#### ለ. የፍካት ደረጃ

የፍካት ደረጃ ማለት በስዕሉ ላይ ያለው የብርሃንና ጥላ፣ልዩነት፣መጠን፣ ደረጃ፣የሚያሳይ ሂደት ሆኖ ቶን ተብሎ ይጠራል፡፡ የፍካት እስኬል /ደረጃ/፣ብርሃን ደረጃ እየጨመረ ሲሄድ አልያም የጥቁረቱ ደረጃዉ

ሲጨምር ወይም እየቀነሰ በሚሄድበት ጊዜ የሚፈጠር የብርሃን እና ጥላ ደረጃ ነው፡፡




## ሠ. ቀለም

ስለ ቀለማት አፈጣጠር ለማወቅ አስቀድመን በተወሰነ መልኩ ስለቀለማት ንድፈ-ሃሳብ (ቲዮሪ) መረዳት ይኖርብናል፡፡ ቀለም የሚለው ስም ጠቅላላ የቀለሞች መጠሪያ ነው፡፡ ቀለም ከብርሃን ነጸብራቅ እና ከሰው ሰራሽ የሚገኝ ነው፡፡ አነስተኛ ብርሃን ካለበት ቦታ ሁሉ አነስተኛ መልክ/ቀለም እይታ ይታያል፡፡ ሀይለኛ ብርሃን ሲኖር ደግሞ ቀለሙ በሚገባ ግልፅ ሆኖ በባህሪው የተለያዩ ድምቀት ይኖረዋል፡፡ በብርሃን ነጸብራቅ ውስጥ ያሉ ቀለማት/አንድ ላይ ሲታዩ ንጣት ያለው ወይም ብርሃናማ መስለው ይታያሉ፡፡ ነገር ግን የብረሃን ነፀብራቅ ውስጥ

ያሉ የተለያዩ ቀለማት ሰባት(7) ሆነዉ ቀስተ-ደመና ተብለዉ ይጠራሉ፡ ፡ ይህም ሊታየን የሚችለው ፀሐይ በካፍያ ውስጥ ስትወጣና አንድ የፀሐይ ጮራ/ቀስት ፕሪዝም በሚባል የብርሃን አስተላላፊ ሶስት ጎነ-ቅርፅ ያለው መስታወት ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ የሚፈጠሩ ቀለማት ናቸው፡፡

ሆኖም እኚህ ቀለማት ብዛታቸው እና ቅደም ተከተላቸው መቼም ቢሆን የማይቀያየር እና ስማቸውም የቀለማት እስፔክትረም በማለት የሚታወቅ ሆኖ ሰባቱን ቀለማት በአንድ ላይ ይዞ የሚታየው እይታ ነው፡፡ አንድን መልክ ለማየት ደግሞ በእስፔክትረም ውስጥ ያሉትን ቀለማት ነገሮች/አካላት የየራሳቸውን መልክ ከራሳቸው ላይ ሲያንጸባርቁ እና ነፀብራቁን ደግሞ በዓይናችን ስናየው ነው፡፡ ስለዚህም ሶስት ነገሮች ማለትም ዐይን፣አካልና ቀለም (ብርሃን) አብረው ሲኖሩ ወይም ቅንጅት ስፈጥሩ ነገሮች ትርጉም ባለው ሁኔታይታዩናል፡፡

### ረ.ሸካራና ለስላሳማነት

ሸካረማነት እና ለስላሳማነት ማለት አንድ ገፅታ ሊኖረው የሚገባ ንፁህነት (ጥራት) ነው፡፡ ስለዚህም ሁሉም ነገሮች የራሳቸውን የገጽታ ጥራት ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህም የገፅታን ጥራት የሚገለጸዉ በቁርቋሬው፣ልስላሴው፣ብርሃን አንፀባራቂነት፣ማብለጭለጭ ወይም ሸካራነማት ላይ በመቆም ልንገልጸው እንችላለን፡፡ ታዲያ፣ እነዚህን የገጽታ ጥረት በቅብ ውስጥ ስንገልፅ ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሰራሽ መሆናቸውን መረዳት አለብን፡፡ አንዳንዴ በእይታችን በጣም ስለታማ ወይም የሚቆርጥ መስለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ለስላሳ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡



ስዕል 1.9፡ሸካራማነትና ለስላሳማነትን የሚሳይ ስዕል

## 7.ቦታ /ስፍራ/

### ውይይት 3

### ቦታ ማለት ምን ማለት ነው?

ቦታ ከዲዛይን አካላት ባዶ ስፍራን ወይም ክፍት የሆነ የቁሶች ውስጣዊ፣ አካባቢ፣ከላይ ፣ከስር ወይም ከታች የሚገኝ ስፍራ ነው፡፡ በስነ-ስእል ስራ ውስጥ ስለ ስፍራ/ቦታ/ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በቅርጻ-ቅርጽ እና ጠንካራ የሆነ ፎርም ላይ የሚታይ ቀዳዳ ሆኖ የሚታይ ስፍራ ሊኖር ይችላል፡፡ ሆኖም፣ ጠፍጣፋ (ለጥ ያለ) ስፍራ ላይ የተሰራ ክፍት ቦታ እንደ ስዕሉ አካል ይታያል፡፡ ቦታ (ስፍራ) በቀለም ቅብ፣ፎቶ፣ ንድፍ፣ቅርጻ ቅርጽ ስራ ላይ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት አንዱ በመሆን ተመልካች ስዕሉን እንዲረዳና እንዲመለከተው ይረዳል፡፡ በዚህ

ምክንያት እንደ ዕረፍት መውሰጃ/ዐይንን ማሳረፊያ/ ቦታ ተደርጎ የሚያገለግል ነው፡፡አምስት(5) የተለያዩ ቦታዎች አሉ፡፡ እነርሱም፡-

- ፖዘቲቭ ስፍራ
- ነጌቲቭ ስፍራ
- የስዕሉ ስፍራ
- የቅንብራዊ ስፍራ
- የትኩረትነጥብ ስፍራ


1. **ፖዘቲቭ ስፍራ፡-** የሚሳለው ስዕል የያዘው ቦታን የሚያሳይ ሲሆን ለተመልካች እይታ እንዲታይ የተሰራ ስፍራ ሆኖ የስዕል ስፍራ ላይ ትኩረት በማሰብ ይታያል፡፡
2. **ኔጌቲቭ ስፍራ፡-** ክፍት ወይም ባዶ ቦታ በስዕሉ መሀል፣ውስጥ እና አካባቢ ላይ ቀርቶ የምንመለከተው ባዶ ስፍራ ነው፡፡
3. **ጠቅላላ የስዕእሉ ስፍራ፡** ስዕል ከመሳሉ በፊት ሊሳልበት የተዘጋጀ ባዶ ቦታ ማለት ነው፡፡ ይህ ቦታ የትኛውም ንድፍ ሊያርፍበት የቀረበ ቦታ ነው፡፡ ለምሳሌ፤

   ለስእል አመቺ የሆኑ እንደ ወረቀት፣ሰሌዳ፣ጠፍጣፋ ጣውላ፣ብንቫስ ወይም የስዕል ሸራ እና የመሳሰሉት እንደ ጠቅላላ የስዕል ቦታ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

**4.የቅንብር ስፍራ፡-** ቅንጅታዊ ስፍራ የተለያዩ ነገሮችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፤ ዋናውን ስዕል፣አጃቢውን፣በክፍት ስፍራ እና በስእሎቹ መካከል ያለውን ርቀት ጨምሮ ያካትታል፡፡ እንደዚሁም ይህ ስፍራ የስነ-ስዕል /የዲዛይን/ አካላት ቅንብር እና አቀማመት አካቶ የሚታይ ነው፡፡

## 5. የስዕሉ ትኩረታዊ ስፍራ(ግነታዊ ቦታ)

አንድ ሰዓሊ ስዕሉን በሚስልበት ወቅት የተመልካችን ትኩረት የሚስብ ወይም ራሱ ሰዓሊውን ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ /በጥልቀት/ ጊዜዉን ወስዶ እንዲሰራ የሚያስገድደው የስዕሉ አካል ትኩረታዊ ስፍራ ተብሎ ይጠራል፡፡



ስዕል 1.10ስፍራን የሚያሳ ስዕል

## 1.2 የኢትዮጵያ ሙዚቃ እና ባህላዊ ዉዝዋዜ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ማንኛውም የሚደረግ እንቅስቃሴ ውዝዋዜ ሊሆን ይችላል?

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት፤**

**በዚህ የትምህርት ርዕስ መጨረሻ ፤**

- ባህላዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ትገልጻለችሁ፡፡
- የውዝዋዜ አይነቶችን ለይተህ/ሽ ትናገሪያለችሁ፡፡
- የሙዚቃ እና የውዝዋዜ ግንኙነት ለይተህ/ሽ ትገልጻለችሁ፡፡
- የአካባቢህን/ሽ ባህላዊ ውዝዋዜ በተግባር ታሳያለችሁ፡፡

**ተግባር 6**

ሀ. ባህላዊ ሙዚቃ ምንድን ነው?

ለ. ሙዚቃ እና ባህላዊ ውዝዋዜን የሚያመሳስለው ምንድን ነው?

ሐ. ከባህላዊ ውዝዋዜ ዉስጥ የሚታዉቁትን በመዘርዘር ከነርሱ ውስጥ አንዱን በተግባር አሳዩ?

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች ብዙ እንደሆኑ ሁሉ ያላቸውም ባህል ብዙ ነው፡፡ በተለይ የብሔሮች የሙዚቃ ባህልና ውዝዋዜ ከቦታ ቦታ ብዙ ልዩነት ያለቸው እና በቁጥሩም ብዙ ናቸዉ፡፡ ከሀገራችን ከሚኖሩት ብሔር ብሄረሰቦች ውስጥ የኦሮሞ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ወስደን ብናይ የኦሮሞ ብሔር የራሱ የሆኑ በጣም ሰፊ ሕዝብና የዘፈን እና የውዝዋዜ ባህል አለው፡፡

በተለያዩ ኦሮሚያ ክፍሎች ውስጥ የሚኖር እንዴት እንደሚዘፍን እና እንደሚወዛወዝ የራሱ የሆነ አለው፡፡ የሚካሄደው ዘፈን እና ውዝዋዜ ምክንያት እና የሚካሄድበት ጊዜ የራሱ ያለው ሆኖ በበዓል ፣በሰርግ ፣ በለቅሶ እና በመሳሰሉት ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ከዚህ ውጭ የሚሳተፉት

ሰዎችም በተለየዩ እና እድሜ ውስጥ የሚገኙ ሆኖ ወንዶች እና ሴቶች፣ አዋቂዎች እና ልጆች ይሳተፋሉ፡፡ ሁሉም የኦሮሚያ ዞኖች የኑሮአቸው ሁኔታ የሚያሳየው የራሳቸው ዘፈን እና ውዝዋዜ አሏቸው፡፡ ከነርሱም ውስጥ የተወሰኑ ዘፈኖችን እንመልከት፡፡

## የወለጋ ባሕላዊ ውዝዋዜ

ወለጋ የተለያዩ ባህላዊ ውዝዋዜ አለው፡፡ ከነርሱም ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

### ጌሎ

ጌሎ በግል ወይም በቡድን መጫወት ይቻላል፡፡ ግን የሚያሳየው ስሜት ግን ሞቅ ያለ አይደለም፡፡ ይህም የሚፈጽሙ ወጣት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የሚያራሩ ዘፈኖችን ሲዘፍኑ እውን ለማድረግ ሲባል ጌሎ ይዘፈናል፡፡ የክንውኑ ሁኔታ አንገት፣እጅና እግርን በማቀናጀት እየቆሙ ወይም እየተንቀሳቀሱ በማወዛወዝ ነው፡፡

### ኩምኩሜ

የኩምኩሜ ውዝዋዜ በጣም ፈጣንና ሞቅ ያለ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የደስታ ስሜት በሰው ውስጥ ይፈጥራል፡፡ የሚፈጸመው ሁኔታ ደግሞ ጉልበትን በማጠፍ እና አንገትን በማንቀሳቀስ መቀናጀት እንዲችሉ ተደርጎ ወገብ ይዘው ወጣት ሴቶች እና ወንዶች በመቀላቀል ክብ ሰርተው በመዞር ይወዛወዛሉ፡፡



ሥዕል17.፡ የወለጋ ባሕላዊ ውዝዋዜን የሚያሳይ

# የቦረና ባህላዊ ውዝዋዜ

## ሆሀዮ

በቦረና ዞን ከሚታወቁ ውዝዋዜዎች ውስጥ አንዱ ሆሀዮ ይባላል፡፡ የውዝዋዜው ሁኔታ በቡድን ወጣት ወንዶች እና ሴቶች መስመር ይዘው ፊት ለፊት በመሆን ወጣት ወንዶች የተረከዝ እና አንገታቸውን በማቀናጀት ወደቀኝ እና ግራ ያንቀሳቅሳሉ፡፡ ወጣት ሴቶች ደግሞ እጃቸውን ወደኋላ እና ወደ ሰማይ በማንሳት እጅ፣እግር እና አንገታቸውን በማቀናጀት ያወዛውዛሉ፡፡






ሥዕል 18 የቦረና ባህላዊ ዉዝዋዜ የሚያሳይ ስዕል

# የጂማ ባሕላዊ ውዝውዜ

## ኦል ቱሜና ገድ ቱሜ

በጂማ አካባቢ የሚታወቀው ውዝዋዜ አል ቱሜና ገድ ቱሜ ይባላል፡፡ ይህም እንደ ሌሎች የኦሮሞ ባህል በቡድን የሚጫወቱት ነው፡፡ ትኩረቱ እጅ መዘርጋት፣ማጠፍ፣ወደታች ማውረድ፣ወደ ላይ ማውጣት፣እጅና አንገትን በተቃራኒ ማድረግ ፣ እግርን ማጠፍ እና መዘርጋት ላይ ነው፡፡ በወጣት ሴቶች እና ወንዶች የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡ የኦል ቱሜ እና ገድ ቱሜ ስያሜ በክንዋኔዉ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡



ሥዕል 19፡ የጅማ ባህላዊ ዉዝዋዜን የሚያሳይ ስዕል

## የሸዋ ባህለዊ ውዝዋዜ

### ዲቺሳ (ጭፈራ)

የዲቺሳ (ጭፈራ) ክንውን የሸዋ ኦሮሞ ጀግንነቱን የሚያንጸባርቅበት የጀግንነት ዘፈን እና ልበ-ጀግንነትን በማነሳሳት ላይ የሚዘፈን ነው፡፡ ይሄም በወጣትነት እድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ፎሌ በሚባሉት ወጣቶች የሚዘፈን ነዉ፡፡ ይህ ውዝዋዜ ወጣት ሴቶችን አያሳትፍም፡፡ የክንውኑ ሁኔታ ወጣት ወንዶች ሽመልና ከሌላ እንጨት የተሰራ ዱላ እና ጋሻ በመያዝ ወደ ላይ እየተስፈነጠሩ ይዘፍናሉ፡፡ በዱላው እርስ በእርሳቸው ይመታታሉ ከዚያም ከራሳቸው ላይ በመከላከል አየዞሩ ይጨፍራሉ፡፡



ስዕል 20፡ የሸዋ ባህላዊ ዉዝዋዜን የሚያሳይ

### ራጺሳ

በውስጣቸዉ ያለውን የፍቅር ስሜት በዚህ ውዝዋዜ የሚገለጹበት ነው፡፡ የክንውኑ ሁኔታ በሸዋ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ ዘንድ ቢገለጽም ወጣት ወንዶች እና ሴቶች በመስመር ተራ በመያዝ የወጣት ሴቶች ቡድን

እግር፣ደረት እና አንገታቸውን በማቀናጀት እጃቸውን ወገባቸው ላይ በማድረግ ሲያወዛዉዙ፣የወጣት ወንዶች ቡድን ደግሞ እግር፣እጅና አንገታቸውን በማቀናጀት ያወዛዉዛሉ፡፡



ስዕል21፡የሸዋ ባህላዊ ዉዝዋዜ ራጂሳን የሚሳይ ስዕል

## ረገዳ/ዳንስ/

ረገዳ/ዳንስ መወዛወዝ የሚችሉ ወጣት ወንዶች ናቸዉ፡፡ረገዳ /ዳንስ/ ሞቅ ባለ በፍቅር ስሜት ተራ በተራ በማዜም አንገታቸውን ወደ ታች በመምታት በእግር መሬትን እየረገጡ ይደንሳሉ፡፡በረገዳ(ዳንስ) ውስጥ ዜማ የሚያደርጉት ቃላታቸው በሚደንሱበት የስሜታቸውን ታሪክ የሚነሳሳ፣ተራርቀውመቆየታቸዉን የሚገልጽ፣መነፋፈቃቸዉን የሚገልጽ፣ በፍቅራቸው ዉስጥ ክፋት በመካከላቸው ሲፈጠር፣መተያየታቸውን በማጠንከር እየተቀባበሉ ይደንሳሉ፡፡በክንውኑ ውስጥ ድምጽ በሚሰማበት ግዜ ቀስ ባለ ረገዳ/ዳንስ ግጥሙ በሁለት ሁለት መስመር ሲያልቅ ይደነሳል፡፡ አንገት እና እግር ከሚደንሰዉ ሰው ጋር ወደ መሬት ይጎነበሳል፡፡ .



ስዕል 22 የሸዋ ረገዳ/ዳንስ ዉዝዋዜን የሚሳይ ስዕል፡፡

## የቱለማ ሶዶ ባህላዊ እንቅስቃሴ

### ኤቦላላ

የቱለማ ሶዶ በኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ ኤቦላላ ይባላል፡፡ ይህ ስም ዘፈኑ የተወሰደው በአብዛኛው ግዜ ከመደጋገም ከሚጠቀሙባቸው ነው፡፡ የክንውኑ ሁኔታ በሙሉ ሰውነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እግርን በተራ ከእጅ ጋር በማቀናጀት ወደ ላይና ወደታች ያደርጋሉ፡፡ ይህ ውዝዋዜ በሰርግ ጊዜ እና በተለያዩ በዓላት ላይ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች በቡድን ይፈጸማሉ፡፡



ስዕል 23፡የቱለማ ሶዶ ባህላዊ ዉዝዋዜን የሚሳይ ስዕል፡፡

## የአርሲ ባህላዊ ውዝዋዜ

### ትሪ

በአርሲ አካባቢ ታዋቂ የሆነ ውዝዋዜ ትሪ ነው፡፡ የክንውኑ ሁኔታ በወጣት ወንዶች እና ሴቶች የሚፈጸም ሆኖ ወጣት ወንዶች ቡድን 'ሲቄ' የሚመስል ቀጭን ዱላ ወይም ጦር በእጃቸዉ በመያዝ እግራቸውን ተራ በተራ በማንሳት ከዱላው ጋር በማቀናጀት እንዲሁም ዱላውን በመያዝና በመዝለል ይወዛወዛሉ፡፡ የወጣት ሴቶች ቡድን ደግሞ 'ከበላ' ወይም 'ቡንሽ' የሚባለው ከእንጨት እና ከቀንድ የተሰራውን በመምታት ድምፅ ያለው ዜማ በማሰማት ፀጉራቸዉን በመበተንና እንገታቸውን በተከታታይ ያዞራሉ፡፡



ስእል 24፡የአርስን ባህላዊ ዘፈን የሚሳይ

## የባሌ ባህላዊ ውዝዋዜ

### እሽኩሜ

በባሌ አካባቢ ባህላቸውን የሚገለጹበት ውዝዋዜ እሽኩሜ ይባላል፡፡ የእሽክሜ ውዝዋዜ አፈጻጸም ሁኔታ በወጣት ሴቶች እና ወንዶች ቡድን መካከል ሆኖ ሴቶች ወገባቸውን በመያዝ አንገታቸውን እና ደረታቸውን በማንቀሳቀስ በእግራቸው የድምጽ ምት እየተከተሉ በከበሮ እያሞቁ ይወዛወዛሉ/ይጫወታሉ፡፡ የወጣቶች ቡድን ደግሞ እጃቸውን ወደላይ በማድረግ በእግራቸው በመዝለል አንገትና ትከሻን በማቀናጀት የከበሮ ምት በመጠበቅ ወደ ወጣት ሴቶች ፊታቸውን በማዞር ይወዛወዛሉ፡፡ የእሽኩሜ ውዝዋዜ በሠርግ ጊዜ በልዩ ልዩ በዓላት ላይ ይፈጸማል፡፡.



ስእል 25፡የእስኩሜ ባህላዊ ዉዝዋዜን የሚያሳይ ስዕል

## የሐረርጌ ባህላዊ ውዝዋዜ

### ሽጎዬ እና ምሪሳ

የሽጎዬ ባህላዊ ውዝዋዜ የፍቅርን ስሜት ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ነው፡ ፡ የክንውኑ/አፈጻጸሙ ሁኔታ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች በጥንድ ሆነው ወጣት ወንዶች እጃቸውን በመያዝ ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ በአንድ ላይ እንደ ወገብና አንገት ስያንቀሳቅሱ፣ ሴቶች ደግሞ ጸጉራቸውን በመበተን

ይጫወታሉ፡፡ ወንዶች ደግሞ በራሳቸው ምት በመጠበቅ ይጫወታሉ፡፡ የሴቶች ቡድን ደግሞ እነርሱን የሚያዙትን በማስተዋል ከሽጎዬ ውዝዋዜ ቡድን ጋር ይጫወታሉ፡፡ ምሪሳ ደግሞ ከሽጎዬ ልዩ የሚያደርገው የፍቅርን ስሜት በይበልጥ ጀግንነት እና ሞራልን ለማጠናከር የሚወዛወዙበት/የሚጫወቱበት ነው፡፡ ከዚህም ውጪ በሚሪሳ ተሳታፎ ሴቶች አይካተቱም::



ስእል 26፡የሃረርጌ ባህላዊ ዉዝዋዜን የሚሳይ ስዕል

## የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ

### ሀሚሳ

ሀሚሳ ከወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የሀሚሳ ውዝዋዜ ሴት ልጃገረዶች እና ወጣት ወንዶች የሚጫወቱ ሆኖ ሴት ልጃገረዶች እና ወጣት ወንዶች ፊት ለፊት በመቆም የፍቅር መልዕክት ያላቸውን ግጥሞች እያዜሙ በሁለቱም በኩል እርስ በእርሳቸው ከተደናነቁ በኋላ ተራ በተራ አንድ ወጣት ወንድ እና አንድ ሴት ልጃገረድ ፊት ለፊት ወጥተው አብረው ይወዛወዛሉ፡፡ ይህ የሀሚሳ ውዝዋዜ ሁኔታ ወጣት ወንድ ዱላ በመያዝ አንዱን እግር ትንሽ ወደ ፊት በማምጣት ያንን ዱላ ከእግሩ ምት ጋር እያቀናጀ ከመሬት ወደ ላይ እየዘለለ መወዛወዝ ሲጀምር ወጣት ልጃገረዷ ደግሞ ከጓደኞቸው አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዛ የወጣት ወንድን እንቅስቃሴን የሚመስል

በእኩል ምት ከተወዛወዘች በኋላ በመጨረሻም እራሷን ዝቅ በማድረግ ጸጉሯን ወደ ወጣት ወንዱ በመበተን ትጨርሳለች፡፡ በዚሁ አካሄድ የቀሩትም ተራ በተራ ይወዛወዛሉ፡፡

.



ስዕል 27፡የሃሚሳ ባህላዊ ዉዝዋዜን የሚሳ ስዕል

**ሲዳሜ**

ሲዳሜ የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ ሌላኛው ሲሆን ይህ ውዝዋዜ እንደ ሀሚሳ ወጣት ልጃገረዶች እና ወጣት ወንዶች የሚጫወቱት ነዉ፡፡ የስዳሜ ባህላዊ ዉዝዋዜ አካሄድ ወጣት ልጃገረዶችና ወጣት ወንዶች በጥንድ በመሆን የሚጫወቱ ሲሆን አንድ ዋሽንት የሚችል ሰው ከተመረጠ በኋላ የፍቅር ገጥም ለሚሆን ልጃገረዶችና ወንዶች የሚወዛወዙበትን አዘጋጅተዉ ለዋሽንት ተጫዋቹ ከነገሩ በኋላ ሰውየው በዋሽንቱ ሲያጅባቸው ጥንዶቹ ደግሞ ተራ በተራ ከሚያምረው ዘፈን ጋር ይወዛወዛሉ፡፡ሲወዛወዙ ወጣቱ ወንድ ዱላውን በመያዝ ከአንደበቱ የሚያንኮራፋ ድምፅ በማውጣት መወዛወዝ ሲጀምር ሴት ልጃገረዷ ደግሞ ዱላውን/ወገቡን/ በመያዝ ትካሻውን እኩል በመምታት አብረው ይወዛወዛሉ፡፡ በዚህ ውዝዋዜ ውስጥ ቆመው ከተወዛወዙ በኋላ ቀስ በቀስ እያሉ እላያቸዉ ላይ በመቀመጥ ከወገብ በላይ ባለው አካል ወደ ላይ

በማንሳት ይጫወታሉ፡፡ ከዚያም ልክ እላያቸው ላይ እየተቀመጡ ሳሉ በሚያራራ ግጥም እርስ በእርሳቸዉን በማሞጋገስ ዋሽንት ለሚጫወተው ወግ ይነግራሉ፡፡ ሴት ልጃገረዷ ደግሞ ለወጣት ወንድ 'አሪቲ' በመስጠት አብረው ይወዛወዛሉ፡፡



ስዕል 28፡የስዳሜ ባህላዊ ዉዝዋዜን የሚያሳይ ስዕል

## 1.3 የስነ-ቲያትር እና ስነ-ፊልም ልዩነት

### ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት ፣

**ከዚህ የትምህርት ርዕስ በኋላ፤**

የቲያትር እና የፊልም ጥበብ ልዩነት ትገልፃላችሁሉ፡፡

**ድርጊት 4**

1. የቲያትር እና የፊልም ጥበብ ልዩነት ምን ብለህ ታስባለህ/ሽ? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡
1. አንድ ሰዉ ብቻውን በተቀመጠበት ፊልም መመልከት ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? ይችላል ብላችሁ ካሰባችሁ በምንና የት እንደሆነ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት?
2. ትያትር የሚታይበት ቦታ የት ነው?

## 1.3.1. ስነ-ትያትር

በትያትር አዳራሽ መስሪያዎች እና ተዋንያን የሚጠቀሙበት ነገሮች እንደተዋንያን ልብስ፣መብራት፣ጥላ እና ማሳመሪያ እነዚህን በአንድ ላይ በማምጣት የማሳያ ቦታ /የቲያትር መድረክን/ ጨምሮ ትያትር ይባላል፡፡

ከዚህ ውስጥ መታወቅ ያለበት ነገር፤

ሀ. የምናየው ነገር መኖር

ለ. የሚከወነው ነገር መኖር

ሐ. ተግባሩ የሚካሄድበት ቦታ መኖር

ይህም ቲያትር የሚታየው በቲያትር አዳራሽ ነው፡፡ የቲያትር አዳራሽ ለቲያትር አዳራሽ ስራ ተለይቶ እንዴት ቲያትር እንደሚታይበት እንዲመች ተደርጎ የሚሰራ ነው፡፡ ይህ የትያትር መድረክ የቲያትሩን ስራ እውን ለማድረግ ጨለማን ተገን አድርጎ መግቢያ መንገድ እና መውጫ መንገድ ያለው እንዲሁም የዋንያን የስራ ቦታ እና መቀመጫ ቦታ ለተመልካቾች ምቹ የሆነ ቦታ ያለው ነው፡፡ በአጠቃላይ በመድረክ ስራ ላይ ያሉት ሁኔታዎች እንዲሁም በመድረክ እንቅስቃሴ ላይ የሚታየው ሁሉ ትያትር ይባላል፡፡ በስነ ትያትር ውስጥ ተዋንያን በቀጥታ ለተመልካቾች በመድረክ ላይ ያቀርባሉ፡፡ የትያትር መቼት ሲነር ለመፍጠር እንደታሪኩ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ መብራት ድምጽም እንዲሁ ነዉ፡፡



ስዕል 29፡የትያትርን መድረክ የሚያሳይ ስዕል

ተዋንያን በተሰጣቸው ቃለ-ምልልስ ላይ በመደጋገም አንብበው ከያዙ በኋላ መግቢያወና መውጫ መንገድ እንዲሁም በሚወጡበት እና በሚገቡበት እይታ በመድረክ ላይ በማየት በቀጥታ በተመልካቾች ፊት ያቃርባሉ፡፡ አንድ ትያትር ተውቦ ተመልካቾችን የሚስብ ሆኖ በመድረክ ላይ ለመቅረብ በተደጋጋሚ ልምምድ ይደረግበታል፡፡ በዚህ ልምምድ ጊዜ ተዋንያን በመድረክ ላይ የተለያዩ መሳሪያዎችን ለትያትር ስራ የሚውሉ አውቀው የመቼት ተግባሩን በማስተዋል መለማመድ ይኖርባቸዋል፡፡ አንድ ትያትር ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ውስጥ በማለፍ ተውቦ በመድረክ ላይ ለተመልካቾች ይቀርባል፡፡

## 1.3.2. የፊልም ጥበብ /ስነ- ፊልም/

ፊልም እንደ ትያትር ለተመልካቾች የሚቀርብ ሲሆን ተመልካቾች ጋር የሚደርሰው በእስክሪን አማካኝነት ነው፡፡ እስክሪን በካሜራ የተቀዳ/የተቀረጸ ነገርን ያሳያል፡፡ ካሜራ ድምጽ እና ምስልን የሚያሳይ እና የሚቀዳ/የሚቀረጽ በቀጥታ ወደ ሌላ ቦታ ለማስተላለፍ እና

ለማከማቸት የሚችል መሳሪያ ነው፡፡ ይህ ቅንጅት ምስለ ድምፅ ወይም ፎቶ ግራፍ የባላል፡፡

ስነ-ፊልም የፎቶ ቀረፃ መሳሪያ አካሄድ "ሴሉሎስን" በሚባል ላይ መብራትን በመጠቀም የሚሰራ ነው፡፡ ፊልም የመገናኛ ብዙሀን መሳሪያ ሆኖ ዋና የቴክኖሎጂ ዝግጅት ወይም ማምረቻ የሚያስፈልጉ ካሜራ እና የእርታኢ መሳሪያ፣የፎቶ ግራፍ መሳሪያ በእስክሪን ላይ የሚንቀሳቀሱ የሚያሳይ በውስጡ የያዘ ነው፡፡ ፊልም የግለሰብን ፍሬሞች በውስጡ የያዘ ሲሆን በፍጥነት ተከታትለው በሚታዩበት ጊዜ ለተመልካቾች የስሜትን እንቅስቃሴ የሚፈጥር ነው፡፡

በአጠቃላይ የስነ ፊልም እና ትያትር ልዩነት ስነ-ፊልም ካሜራ በመጠቀም የሚያስፈልገው ቦታ ውስጥ በማለፍ የሚፈለገውን ቦታ በመውሰድ ቆርጦ በማውጣት እና አስተካክሎ በመቀጠል የሚዘጋጅ ነው፡፡ ትያትር ደግሞ በመድረክ ላይ በቀጥታ ተመልካቾች ባሉበት ቦታ ይቀርባል፡፡ በፊልም ውስጥ ተመልካች በቀጥታ መገኘት ግዴታ አይሆንም፡፡ ተመልካች በእስክሪን መንገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መመልከት ይችላል፡፡ ትያትር በመድረክ ላይ ይመሰረታል፡፡ ተመልካችም የግድ በቀጥታ መከታተል ወይም መመልከት አለበት፡፡ ፊልም ግን ትኩረቱ ካሜራ ወይም በእስክሪን መስኮት አማካኝነት ይቀርባል፡፡



ስዕል 30፡የሲኒማ አደራሽን የሚሳይ ስዕል

**በአጭሩ የቲያትር እና የፊልም ልዩነት ከዚህ በታች በተቀመጠው ቻርት መረዳት ይቻላል፡፡**

| ትያትር | ፊልም |
|---|---|
| የእምነት ክብረ-በዓላት ከዳዮናይሱስ ላይ የመጣ፡፡ | በ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ተጀመረ፡፡ |
| በቀጥታ ክንዋኔ/ክወና ይታያል፡፡ | በክንዋኔ/ክወና ይቀዳል/ይቀረጻል፡፡ |
| በምዕራባውያን ዓለም ስነ-ስዕል በአሁኑ ግዜ ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሶ የምናየው ይህ መሰረቱ ከግሪኮች ክብረ-በዓል የመጣ ነው፡፡ | ተዋንያንና ተመልካቾች ግንኙነት የሚቀዳው/ የሚቀረጸዉ በካሜራው ይዘትና በቅርበት ላይ በመመስረት ነው፡፡ |
| ከመጋረጃ ግንኙነት ጋር ትልቅ ቁርኝት አለው፡፡ | ከመጋረጃ ጋር በቀጥታ ሳይሆን በቴሌቪዥን አማካኝነት ይገናኛል፡፡ |
| የትያትር ክንዋኔ የራሱ የሆነ ባህሪ አለው፡፡ | ሁሉም ፐርፎርማንስ የተመሳሰለ ባህሪይ አለው፡፡ |
| ፎቶ የተለያየ ሁናቴ ያለው ሆኖ መታየት ይችላል፡፡ | የተለየ ሁኔታ ከውስጡ ይታያል፡፡ |
| በሚታይበት ጊዜ ማንኛውም የሚፈጠረው ስህተት ተዋንያን በዘዴ እና ድንገታዊ ፈጠራን በመጠቀም ያስተካክላል፡፡ | በቀረጻ አካሂድ ውስጥ ደራሲ በተውኔት ፅሁፍ ማስተካከል ይችላል፡፡ |
| ትኩረቱ መድረክ ላ ነው፡፡ | ትኩረቱ በካሜራ መጠን ላይ ነው፡፡ |

# የምዕራፍ 1 ማጠቃለያ

- የዲዛይን ስራ ከስነ-ጥበብ አንድ ሆኖ አንድ የስነ-ጥበብ ባለሙያ የተለያዩ ዘዴን በመጠቀም የተለያዩ አካል ፎርምን በማቀናጀት ሙሉ በሙሉ መልዕክት የሚያስተላልፍበት መንገድ ነው፡፡
- የይዘቶች ስብስብ እንደ ግባት ሆነው የሚያገለግሉ የዲዛይን አካላት ናቸው፡፡
- ከዲዛይን አካላት ውስጥ መስመር አንዱና መሰረታዊ ነው፡፡
- የዲዛይን አካላት ቅርጽ ቁመትና እና ርዝመት እኩል ሆኖ በመስመር የሚገለጽ ነው፡፡
- የዲዛይን አካላት ፎርም ከቅርፅ ጋር ትልቅ ተመሳሳይነት አለው፡፡
- ፍካት/ብርሃን እና ጥላ የዲዛይን አካላት የሚገለፅበት ነው፡፡
- ሸካራማነት እና ለስላሳማነት የአንድ ነገር አካል ጥራት ገጽታ ነው፡ ፡
- ቦታ የሁሉም የስነ-ጥበብ የስራ ማረፊያ ነው፡፡
- የኦሮሞ ብሔር ብዙና ሰፊ የሆነ የራሱ የባህል ዘፈኖች እና ውዝዋዜ አሉት፡፡
- በኦሮሚያ ልዩ ልዩ ዞኖች ውስጥ የሚኖሩ የኦሮሞ ብሔሮች እንዴት እንደሚዘፍኑና እና እንደሚወዛወዝ የራሳቸዉ የሆነ ባህል አላቸዉ፡፡
- በሁሉም የኦሮሚያ ዞኖች የአኗኗራቸውን ሁኔታን የሚገልጹ የራሳቸዉ የሆነ ዘፈን እና ውዋዝዜ አሏቸው፡፡
- በመድረክ ስራ ላይ ሁኔታዎች እና ነገሮች እንዲሁም በመድረክ እንቅስቃሴዎች ላይ ያሉ ሁሉ የሚካሄደው/የሚታየው ትያትር ይባላሉ፡፡
- ትያትር በመድረክ ላይ ይመሰረታል፡፡

- በስነ-ትያትር ስራ ውስጥ ተዋንያን በቀጥታ በመድረክ ላይ ለተመልካች እየተቀያየሩ ያቀርባሉ፡፡
- አንድ ትያትር የተዋበና ሰውን የሚስብ ሆኖ በመድረክ ላይ ለተመልካቾች ለማቅረብ በተደጋጋሚ መጠናትና መለማመድ ይኖርበታል፡፡
- ፊልም ተመልካች ጋር የሚደርሰው በእስክሪን አማይነት ነው፡፡
- የፊልም ትኩረት ካሜራ ላይ ነው፡፡

## የምዕራፍ አንድ መልመጃ

**I.ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆኑትን እውነት፣ ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡**

1. በንድፍ ውስጥ መስመር የተወሰነ ቦታ ብቻ ሆኖ ይታያል፡፡
2. አንድ የዲዛይን ስራ የይዘቶች ስብስብን የሚገልጽ ነው፡፡
3. የንድፍ ፍካት /ብርሃን እና ጥላ/ እና የቀለም አቀባብን ለመስራት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡
4. የቦታ ጥራት የነገሮች አካል ገጽታ ነው፡፡
5. ቦታ የሁሉም የስነ-ጥበብ የስራ ማረፊያ ነው፡፡
6. ዲዛይን ማለት የዕቃ ወይም ስዕላዊ ስራ እቅድ ወይም የስራ ሀደት መመሪያ (ንድፈ-ትልም) ማለት ነው፡፡
7. ባህላዊ ውዝዋዜ እና ባህላዊ ሙዚቃ ልዩነት የላቸውም፡፡
8. የኦሮሚያ ዞኖች ባህላዊ ውዝዋዜ ከቦታ ቦታ የውዝዋዜ ሁኔታ ልዩነት አሏቸው፡፡
9. የኦሮሞ ቱለማ ሶዶ በህላዊ ውዝዋዜ ሀሚሳ ይባላል፡፡
10. ከባህላዊ ውዝዋዜ ከሚገለፅ ውስጥ አንዱ የአልባሳት ባህል ነው፡፡
11. ማንኛውም ብሔር የራሱ ባህላዊ ውዝዋዜ ሊገልፅ/ሊያሳይ ይችላል፡ ፡

12.የፊልም ትኩረት መድረክ ነው፡፡

13.በስነ-ትያትር ስራ ውስጥ ተዋንያን በቀጥታ ለተመልካች መድረክ ላይ ያቀርባሉ፡፡

14.በፊልም ውስጥ ተዋንያን ከመጋረጃ ጋር በቀጥታ ሳይሆን በቴሌቪዥን አማካኝነት ይገናኛሉ፡፡

15.የትያትር ፐርፎርማንስ/ክወና በቀጥታ ይታያል፡፡

## II. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡

1. ከዲዛይን አካላት ውስጥ ዋናውና መሰረታዊ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ) ቅርጽ  ለ)ፎረም  ሐ) ቀለም  መ) መስመር

2. በዲዛይን ስራ ውስጥ ስንት የመስመር አይነቶችን እንጠቀማል?

   ሀ) 3  ለ) 7  ሐ) 7  ሐ) 5  መ) 9

3. በዲዛይን መስመር ስራ ውስጥ እንቅስቃሴ እና አቅጣጫን በመፍጠር ከተቀናጀ በኋላ ደግሞ የፍጥነት ስሜት መፍጠር የሚችለዉ የትኛዉ መስመር ነዉ?

   ሀ) ስያፍ  ለ) አግድም  ሐ) ቋሚ  መ) ሽክርክሪት

4. የሰወን ስሜት የሚረብሽ መስመር ሆኖ ሰውን የሚያነሳሳ እና መጨረሻ የሚያሳይ የቱ ነው?

   ሀ) ጠመዝማዛ  ለ) ስያፍ  ሐ) ዝግዛግ  መ) ቋሚ

5. የመስመሮች ልዩነት ያልሆነ የቱ ነው ?  ሀ) ርዝመትና እጥረት

   ለ) መድመቅ እና መደብዘዝ  ሐ) ለስላሳማነት እና ሸካራማነት

   መ) መልስ አልተሰጠም

6. ከትልቅ ነገሮች ቀለም ያላቸው ከሶስቱም (3) ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ) ብርሃን ለ) ቀለም ሐ) ፍካት(ብርሃንና ጥላ) መ) ጥራት

7. የአንድ አካባቢ ሙዚቃ ወይም የባህል ዘፈን ማንን ይገልጻል?

   ሀ) የአካባቢውን ማህበረሰብ ለ) ዘፋኝ ሐ) ሀገር

   መ) ሁሉም መልስ ነው

8. ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ውስጥ ልዩ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ) ሀሚሳ ለ) ጭፈራ ሐ) እሽኪኬ መ) ፉከራ

9. ከዚህ በታች ከተጠቀሱነት ውስጥ አንድ የባሌ ዞን ውዝዋዜ ነው፡፡

   ሀ) ኤቦላላ ለ) ሀሚሳ ሐ) እሽኩሜ መ) ትርትርስ

10. ከኦሮሚያ ክልል ዘፈኖች ውስጥ ሚሪሳ የየትኛው ዞን ውዝዋዜ ነው?

   ሀ) ከሚሴ ለ) ሐረርጌ ሐ) ራያ መ) ወለጋ

11. ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ውስጥ በአርሲ የሚታወቀው ውዝዋዜ የቱ ነው?

   ሀ) ሀሚሳ ለ) ቲሪ ሐ) ረገዳ/ጭፈራ መ) እሽኩሜ

12. በመድረክ ላይ የሚሰሩ ነገሮች እና ሁኔታዎችን ጨምሮ እንዲሁም በመድረክ ላይ እንቅስቃሴዎች የሚቀርቡ ወይም የሚታዩ ሁሉ ምን ይባላሉ ?

   ሀ) ፍልም ለ) ተዋንያን ሐ) ትያትር መ) መጋረጃ

13. ፊልምን በተመለከተ ትክክለኛው የቱ ነው?

   ሀ) ምንጩ ሀይማኖት ነው ለ) ክዋኔው/ኪንዉኑ በቀጥታ ይታያል

   ሐ) ክዋኔው/ኪንዉኑ ይቀረጻል/ይቀዳል

   መ) ትኩረቱ መድረክ ላይ ነው

14. በስነ ትያትር ውስጥ ሲነር ለምን ይጠቅማል ?

ሀ) መጠለያ ይሆናል ለ) መቼት ይፈጥራል

ሐ) ትያትርን ይገልጻል መ) ትያትር ያስተካክላል/አርቲኦትን

## III. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በተጠየቃችሁ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

1. ከኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ ውስጥ ትሪ እና ሸጎዬ የየትኛው ዞን ውዝዋዜ ናቸው?
2. የከሚሴ ኦሮሞ እና የባሌ ባህላዊ ውዝዋዜ ምን ይባላል?
3. ከየአካባቢያችሁ ባህላዊ ውዝዋዜ ምን እንደሚባሉ እና እንዴት እንደሚጫወቱ ግለጹ፡፡
4. በተለያዩ የኦሮሚያ ዞኖች ባህላዊ ውዝዋዜዎች ውስጥ አንዱን በመምረጥ በቡድን በተግባር አቅርቡ፡፡
5. የመስመሮችን መገኛ በመጠቀም የተለያዩ ስዕሎችን አሳዩ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## የስነ-ጥበብ ፈጠራ ችሎታ

**የዚህ ትምህርት ምዕራፍ ውጤት፤**

**በዚህ ትምህርት ምዕራፍ መጨረሻ ላይ፤**

- የቀለም ቅብ ስራ ሙያ ትረዳለህ/ሽ፡፡
- የእያንዳንዱን የቀለም ቅብ ስራ ፍቺ አካላትን ትርጉም ትለያለህ/ሽ፡፡
- የቀለም ቅብ ስራ አካላት ያላቸውን ጥቅምና የሚያስተላልፉትን መልዕክት ትለያለህ/ሽ፡፡
- የሶልፌጅዮ ትርጉምና ጥቅምን ታውቃለህ/ሽ፡፡
- የሙዚቃ ምት ዓይነቶችን ሰምተህ/ሽ መጻፍ ትችላለህ/ሽ፡፡
- በትዝታና ባቲ ቅኝት አጫጭር ዜማዎችን መጫወት ትችላለህ/ሽ፡፡
- የስነ- ትያትርና የስነ-የፊልም ሃሳብን መጻፍ ትችላለህ/ሽ፡፡
- ለጥሩ የተዉኔት ጽሁፍ ዘዴ የሚረዱትን ነገሮች ትገነዘባለህ/ሽ፡፡

### መግቢያ

የስነ-ጥበብ ስራና ስልት በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ነገሮችን እየተሰሩ የነበሩና እየተሰሩ ያሉ ውስጥ አንዱ የቀለም ቅብ ስራ ነው፡፡ የቀለም ቅብ ስራ ረጅም ታሪክ ያለውና ከስነ- ጥበባት ዘዴየሚሰራበት አንዱ ሆኖ የሰው ልጅ ከጥንት ዓመት ጀምሮ ሀሳቡን፣ ስሜቱን፣ሀዘኑን፣ ደስታውንና ምኞቱን ሲገልፅበት ቆይቷል፡፡ከቀለም ቅብ ስራ ውስጥ ቀለም ያለው ሚና ይህ ነው ተብሎ አይገለፅም፡፡

ቀለም ለቀለም ቅብ ስራ አካላት ወሳኝና ዋናና መሰረታዊ ነው፡፡ ያለ ቀለም የቀለም ቅብ ስራማሰብ አይቻልም፡፡ የቀለም ቅብ ስራን ለመስራት የቀለማትን ንድፈ-ሀሳብ ማወቅና መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ ቀለም አንድ የተዋበ ነገር ለመስራት ትልቅ ቦታ ያለው ነው፡፡

በተጨማሪም፣ ውዝዋዜና የሰውነት እንቅስቃሴና ከዘፈን ወይም መዝሙር ጋር የሚሆን መሆኑን ተምረሃል/ሻል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የሶልፈጅዮ ሳይንስ የሰው የጆሮ ችሎታ በሙዚቃ ማዳመጥ ላይ ያለውና ስለምት ፅንሰ-ሀሳብ የሚያዳብርበት እንዲሁም፣ የትዝታና የባቲ ቅኝቶች የምት ስልትና ጥቅምን ትማራለህ/ሽ፡፡ የስነ-ቲያትርና የስነ-ፊልም ጥበባትን ለማዘጋጀት መጀመሪያ በምናዘጋጀው ላይ ሀሳብ መያዝ አለብን፡፡ የስነ-ትያትር ጥበባትም ሆነ የስነ-ፊልም ጥበባት ሐሳብ ለማዘጋጀት ደግሞ የራሱ የሆነ ሂደት አለው፡፡ የስነ-ትያትር ጥበባትና የስነ-ፊልም ጥበባት ሀሳብ ሁኔታ የምናዘጋጀው በዚህ ርዕስ ስር የተዘጋጀ ነው፡፡

## 2.1. የውሃ ቀለም ቅብና ህትመት ስራ

### 2.1.1. የዲዛይን መሰረታዊ አካላት ድርሻና ጥቅም

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት፤**

**ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፣**

- የቀለም ቅብ ስራ ትርጉም ትናገራለህ/ሽ፡፡
- የቀለም ቅብ ስራ ክፍሎችን ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡
- የቀለም ቅብ ስራ አካላት ጥቅም በቀለም አቀባብ ስራ ውስጥ ያላቸውን ትገልጻለህ/ሽ፡፡
- የቀለማትን ንድፈ-ሃሳብ ትናገራለህ/ሽ፡፡
- የህትመት፣እስቴንስልና ብሎክ ስራ ሁኔታ ትለያለህ/ሽ፡፡

➢ የስቴንስል ህትመትና ብሎክ ከአካባቢያችሁ ከሚገኙ ቀላል ነገሮች ሰርተህ/ሽ ታሳያለህ/ሽ፡፡

**ውይይት 1**

1. በካባቢህ/ሽ ያሉት ሰዎች ቤት በሚገነቡበት ጊዜ ወይም ከሌሎች ነገር ቀለም ሲቀቡ አይተህ/ሽ ታውቃለህ/ሽ?
2. አይተህ የምታውቅ ከሆነ ምን ምን በመጠቀም ይቀባሉ? እንዴትስ ይቀባሉ? በየቡድናችሁ በመወያየት ለክፍላችሁ አቅርቡ?

## 2.1.2. የቀለም ቅብ ስራ ትርጉም

የስነ-ጥበብ ስራ ስልት በተላያዩ ቦታዎች ከተለያዩ ነገሮች እየተሰሩ የነበሩና እየተሰሩ ካሉት ዉስጥ አንዱ የቀለም ቅብ ስራ ነው፡፡ የቀለም ቅብ ስራ ታዋቂና ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ ነው፡፡

ይህ የቀለም ቅብ ስራ ከውስጥ በመቦርቦር ወይም በማለስለስ በቀለም ደግሞ በቀለም በመቀባት የሚሰሩ ናቸው፡፡ ከሚሰሩት ቀለም ደግሞ ቀይ ቀለም፣ቢጫ እና ጥቁር ናቸው፡፡ በይበልጥ ስዕሎች በቀለም ቅብ ተሰርተው የሚታዩ የፈረስ፣አንበሳ፣ጎሽ፣ዝሆን፣አጋዘን አልፎ አልፎ የተወሰኑ በሰው አካላት ተቀብተዉ የተሰሩ ነበሩ፡፡ ቢሆንም ግን አንዳንድ ጥናቶች አሁን እየወጡ ያሉ እንደሚገልፁት የቀለም አቀባብ ከዚህ በፊት ከተገለጹት ዓመታት በላይ የነበሩ በተለያዩ ቦታዎች የተገኙ እንዳሉ ነው፡፡

የቀለም ቅብ ስራ ማለት ቀለም ለመቀባት ሌሎች ነገሮችን በመጠቀም ጠንካራ ገጽታ ያላቸው ነገሮች ላይ ስዕል፣ዲዛይንና የውበት ሙያ የሚሰራበት ነው፡፡ የቀለም ቅብ ስራ በአብዛኛው ቀለምን በመጠቀም በመቀቢያ ጠንካራ ነገሮች ላይ ይሰሩ እንጂ እንደ ቢላዋ፣እስፖንጂ እና የመሳሰሉት መሳሪያዎች ላይ ይሰራል፡፡ በስነ-ጥበብ ውስጥ ቀለም ማለት

ክንዋኔ ያለው የእጅ ስራ ውጤት፣ፍጥረትን የሚገልፅ፣ምትክ የሆነ፣ፎቶ የሚመስል ትርጉማቸዉ ግልፅ ያልሆኑና የመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡
የቀለም ቅብ ስልት ከስነ-ጥበብ ስራ ከሚሰሩባቸው ውስጥ አንዱ ሆኖ እንደ ንድፍና ቅርጻ ቅርጽ ሺዎች አመታትን ያስቆጠረ ነው፡፡ ድሮ የቀለም ቅብ ስራ ይዘት በይበልጥ መልዕክታቸው በሀይማኖት ጉዳይ ላይ ተመስርቶ የተሰራና በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንደ ባህል የሚታይ ነበር፡፡
የቀለም ቅብ ስራ ትልቅ ሃይል ያለው ነው፡፡ የመልእክቱ ሀይል በቀለም ቅብ ስራ የታወቁ ሆነው በስሜታዊ አመለካከት ደረጃ፣ስነልቦና አመለካከት ደረጃ፣በሰው መንፈስ ደረጃ ከሚያሳየው በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ የቀለም ቅብ ስራ በአብዛኛው ከሁለም ነገሮች መሀል ተኮር ያደረገ ነው፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ ገፅ ያላቸው ነገሮች እንደ ወረቀት፣ እንጨት፣የስዕል ሸራ፣ሸክላ፣ፕላስቲክ፣ግድግዳና ከመሳሰሉት ላይ ሊሰራ ይችላል፡፡ እንዲሁም ቅብ ስራ ከፈሳሽ ነገሮች ሆነው እርጥበት እና የአየር ሁኔታ ተቋቁመው ረጅም ጊዜ መቆየት ከሚችሉ የተሰሩ ናቸው፡፡

## 2.1.3 የቀለማት ንድፈ-ሀሳብ


### ውይይት 2

1. ቀለም ምንድን ነው?
2. የቀለም ጥቅም ምንድን ነው?

ቀለም የሚል ቃል አጠቃላይ ስም ሁሉንም ቀለም የሚተካ ሆኖ ቀለም ማለት መልክ ያላቸው ነገሮች በብርሃን ነጸብራቅ አማካይነት በአካባቢያችን ያሉ ላይ በሚያርፉበት ጊዜ የሚፈጠር ነው፡፡ በዓለም ላይ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ የሆኑ በተለያዩ ቀለም የተዋቡ ናቸው፡፡ በዚህ ዓለም ላይ የሚገኙ ፍጥረታት በሺህ የሚቆጠሩ ቀለማት

ተሞልተዋል፡፡ ፍጥረትን አገናዝበን ብንመለከታቸዉ ውበታቸው የሰውን ልብ የሚሰርቁና የሰውን አዕምሮ በመማረክ የተሞሉ ናቸው፡፡ የመሬት አቀማመጥ ፣የሰማይ ዕይታ ፣ የባህር አቀማመጥ፣የጋራዎች አቀማመጥ፣ የሸንተረሮች አቀማመጥ ፣የውሃ ፏፏቴ ፣እንሰሳቶች ፣አዕዋፋት ፣ዛፎችና የመሳሰሉት ውበታቸው ሰውን የሚማርኩ ሆነው ፍጥረት ያጎናጸፏቸው አሏቸው፡፡ የተለያዩ ተክሎች እና አበባዎች ያላቸው መሬት በአፈር ተሸፍና ስላለች በርቀትና ቅርበት ካየናቸው የተለያዩ ቀለም ይታዩናል፡፡ አበባዎች እና ተክሎች አረንጓዴ ቦታ ስላላቸው አረንጓዴ መልክ፤ቢጫ አበባ ያለው ደግሞ ቢጫ መልክና ቀይ እና ጥቁር አፈር ባለበት ደግሞ ቀይ ሆኖ ወይም ጠቁሮ ይታያል፡፡ከዚህ ሌላ ብርሃንና ጥላ የሚታይበት ቦታ አለ፡፡

ስለዚህ፣ ከቦታ አቀማመጥ ጋር የተያያዘ መሬት የተለያየ የቀለምና ቅርፅ ስላላት በሚጎበኝበት ጊዜ ሰውን ያስደስታል፡፡ ቀለም ያላቸው ሁሉ የተለያዩ ውበት ይኖራቸዋል፡፡ በአካባቢያችን ያሉ ተፈጥሮአዊም ሆነ ሰው-ሰራሽ ሆነው የሚታዩን የምንለያቸው በይበልጥ በመልካቸው ነው፡፡ በስነ-ጥበብ ስራ ውስጥ ቀለም አንድ ውብ የሆነ ነገር ለመስራት ትልቅ ቦታ አለው፡፡ እነዚህን ነገሮች በስዕል ወይም ዲዛይን የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም በሚሰራበት ጊዜ መገንዘብ ያለባቸው ነጥቦች ከዚህ በታች ባለው ሁኔታ ተገልፀዋል፡፡

ስዕል 3፡የቀለም ቅብን የሚሳይ ስዕል

## 2.1.4.የቀለማት ምንጭ

### ተግባር 1


1. የቀለም ምንጭ ምንድን ነዉ ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን በመወያየት ለክፍሉ አቅርቡ፡፡
2. የቀስተ ደመና ቀለማትን አሰታውላችሁ ታውቃላችሁ? ስንት ቀለማት አሉት? እነሱስ?

ቀለማት በአከባቢያችን በዓይን አይተን የምንለያቸው ስም ጠርተን የምንለዩዋቸዉ በአይናችን እንደሚታዩን የሚያደርገው የጸሀይ ብርሃን ነው፡፡ ብርሃን ከለሌ አካባቢያችን ያሉትን ቀለማት መለየት አንችልም፡፡ ብርሃን የለም በምንልበት ጊዜ ወይም በማይታየን ጊዜ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የቀለም ምንጭ ብርሃን ነው፡፡ ከፀሐይ ብርሃን የሚገኘው የተለያዩ ሞገዶች ተቀናጅተው በተለያየ ፍጥነት የሚርገበገብ ነው፡፡

ቀለማት እስፔሰክትረም እና ያስቨከተረም ትርጉም ከማየት በፊት ፕሪዝም ምን እደሆነ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ፕሪዝም ብርሃንን ማስተላለፍ የሚችል እንደ ውሃ ወይም የውሃ ጠብታ መስታወት እና የመሳሰሉት ማለት ነው፡፡ የብርሃን ጨረር ፀሀይ በማንኛውም ጊዜ ቀለም በውስጡ ይዞ ይሄዳል፡፡ ግን ይህንን ቀለማት ለመለየት እና ማየት የምንችለው አንዱ በፕሪዝም በመጠቀም ነው፡፡ ለምሳሌ ውሃ በአፋችን ሞልተን ወደ ፀሐይ ብንረጭ በፊት ለፊታችን የተለያዩ ቀለማት እናያለን፡፡ ከዚህ ላይ ምን እንረዳለን ብንል የፀሐይ ጨረር የተለያዩ ቀለማትን ከውስጡ ይዞ እንደሚሄድ ነው፡፡ ብርሃን ያላቸውን ነገሮች ከውስጣቸዉ ማስተላለፍ የሚችሉ እንደ ፕሪዝም ውጪ ሌሎች ነገሮች ውስጥ መተላለፍ አይችልም፡፡ የፀሐይ ብርሃን በማንኛውም ጊዜ ከምንጫቸው በመነሳት

በትክክለኛ አቅጣጫ የሚሄዱ ናቸው፡፡ የብርሃን ጨረር ተጠማዞ ቢያልፍ ኖሮ ጥላ የሚባል ነገር ምንም አይፈጠርም ነበር፡፡ ግን ይህ የፀሐይ ብርሃን ጨረር በፕሪዝም ውስጥ በሚያልፉበት አቅጣጫቸውን ለውጠው በተለያዩ ማዕዘን በመበተን ነጭ ወረቀት ላይ በሚያርፉበት ጊዜ ልዩ መልክ ይፈጥራሉ፡፡ይህ ጨረር እስፔክትረም በመባል ይታወቃል፡፡

እስፔክትረም ማለት የፕሪዝም ቀለማት ወይም የውሃ ጠብታ ውስጥ ተጠማዞ ማለፍ የሚፈጠር ሰባቱ (7) ማለት ነው፡፡ ከፀሐይ ብርሃን እንደ ሞገድ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ ይህ እስፔክትረም እንደ ቀስተ-ደመና ሰባት (7) የተለያዩ የቀለማት መልክ በውስጡ አለው፡፡እነሱም"VIBGYOR" በመባል ይታወቃሉ፡፡ "VIBGYOR" የቀለማትን የፊደል ምትክ በእስፔክትረም ውስጥ በማለፉ ሰባቱ ከእንግሊዘኛ ፊደላት የተወሰዱ ናቸው፡፡ እነዚህ እያንዳንዳቸው ፊደላት ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ቀለም ምን ምን እንደሚተኩ እና ይህ የቅደም ተከተል ስም የተሰየመው ከዚህ በታች ከተቀመጠው ምሳሌ ላይ ስላለ በትክክል አወቀህ/ሽ ተመልከት/ቺ፡




ስዕል 4፡በፕሪዝም ዉስጥ ዉስጥ እያለፈ ያለዉን የሚሳይ ስዕል፡፡

VIBGYOR" ማለት ከታች ወደ ላይ በሚነበብበት ጊዜ ፤

1. 'R' ማለት 'Red' ቀይ
2. 'O' ማለት 'Orange' ብርቱካናማ
3. 'Y' ማለት 'Yellow' ቢጫ
4. 'G' ማለት 'Green' አረንጓዴ
5. 'B' ማለት 'Blue' ሰማያዊ
6. 'I' ማለት 'Indingo' አምራዊ
7. 'V' ማለት 'Violet' ወይንጠጅ

ረጅም ወይም ትልቅ ሞገድ ያላቸው ቀለማት ትልቅ ሆነው የሚታዩትን ነገር ወይም ሩቅ ላይ ያላቸው ነገሮችም ወደ እኛ በማቅረብ ያሳዩናል፡፡ እኝህ ቀለማት ከቀይ ወደ ወይንጠጅ በሚሄዱበት ጊዜ በቅደም ተከተል የሞገድ ፍጥነታቸው እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ለምሳሌ አንድ ቀይ ቀለም ያለው ቢጫ ቀለም ካለው ነገር በርቀት ላይ ወደ እኛ ቀርቦ በእስፔክትረም ውስጥ ያሉ ቀለማት ሰባቱን (7) ብናቀላቅል ንፁህ ነጭ የሆነው የፀሐይ ብርሃን ይሰጠናል፡፡ ፀሐይ ያለው ቀለም ወይም መልክ ነጭ የሆነውን የተለያዩ ቀለም ይዛ ወይም ተለውጣ የምትታይ ልትመስለን ትችላለች፡፡ ግን አይደለም እንደዚህ አስመስሎ የሚያሳየን በምድር አካባቢ ያለው ነጸብራቅ እንጂ ፀሐይ መልኳን አትቀይርም፡፡ ቀለማት በሰው ሰራሽ እስፔክትረም (ለቅብ) የሚውሉ ሰባቱን (7) ካደባለቅናቸው ንፁህ ነጭ መልክ የሆነ ሳይሆን የደፈረሰ ወይም የተበከለ ይሰጠናል፡፡

## 2.1.5. የቀለም ግንኙነት

**ውይይት 3**

1.በአካባቢ የሚገኙ ቀለማት የሚታይብህ/ሽ ለማየት ምን ምን ታስባለህ/ሽ እነሱም እነማን ናቸው?

1. አንድ ነገር የቀለም መልክ ይዞ እንዴት ይታይብሃል/ሻል? በየቡድናችሁ እየተወያያችሁ ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

በአካባቢያችን የሚታዩ ቀለማት ለማየት ሶስት(3) ትላልቅ የሆኑ ነገሮች ያስፈልጉናል:: እነርሱም፡-

- ✓ ብርሃን
- ✓ ገፅታ (ቀለም የሚያንፀባርቅበት ነገር)ና
- ✓ ዐይን ናቸው

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሶስት (3) ነገሮች አንዱ ቢጎድል ወይም ቢደበቅ ኖሮ በአለም ላይ የሚታዩ ማናቸውንም ነገሮች ማየት አንችልም፡፡ እስካሁን የቀለማት ንድፈ-ሃሳብ ላይ እንደምንረዳው ቀለማት በሁለት መንገድ ይታያሉ እነርሱም፡


- ✓ የብርሃን ጨረር ቀለማት፣የተፈጥሮ ቀለማት እና ሰው-ሰራሽ ቀለማት

### 1. የብርሃን ጨረር ቀለማት (የተፈጥሮ ቀለማት)

ኢሳክ ኒወቶን ባካሄደው ጥናት የቀለማት ምንጭ ሁሉ ብርሃን እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ ብርሃን ከሌላ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቀለምን ስም


መጥራት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በጨለማ ውስጥ ያለ መልክ ሁሉ አንድ ይሆናል እነሱም ጥቁር ብቻ ነው፡፡

በብርሃን የሚታዩ ቀለማት የሚባሉ በብርሃን ጨረር ቀለማት በፕሪዝም ውስጥ በተለያዩ አቅጣጫ ተጠማዘው በእስፔክትረም ውስጥ ያሉ ቀለማት ማለት ነው፡፡ በብርሃን የሚታዩ ቀለማት ከሰው ሰራሽ ቀለማት ልዩነት አላቸው፡፡ ሶስቱ (3) መሰረታዊ ቀለማት በብርሃን የሚታዩ፤ ቀይ፣አረንጓዴ እና ሰማያዊ ናቸው፡፡




ስዕል 7፡የተፈጥሮ ቀለማት ስዕል


የእነዚህ ቀለማት ድምር ቀለም ወይም ንፁህ ነጭ ብርሃን የሆነ ይሰጣል




ስአዕል 8፡የመሰረታዊ ቀለማትን የሚያሳ ስዕል


መሰረታዊ ቀለማት በብርሃን የሚታዩ የኤሌክትሮኒስ መሳሪያዎች እንደ ቴሌቪዥን፣ኮምፒተር እና የመሳሰሉት ብቻ ውስጥ በማቀናጀት ማየት እንችላለን፡፡ ሶስቱ መሰረታዊ ቀለማት በብርሃን የሚታዩ እየአንዳንዳቸው ተራ በተራ ቢቀናጅ የሚሰጡት መልክ፡-

ቀይ+ አረንጓዴ= ቢጫ




ስእል 9፡ የብጫ ብርሃን ቀለም እንዴት እንደሚፈጠር የሚያሳይ ስዕል

ሰማያዊ+ ቀይ = ማጄታ





ስእል 10፡ የማጀንታ ብርሃን ቀለም እንዴት እንደሚፈጠር የሚያሳይ ስዕል

ሰማያዊ + አረንጓዴ= ሰያን




ስእል 12፡ የሲያን ብርሃን ቀለም እንዴት እንደሚፈጠር የሚያሳይ ስዕል

ቢጫ + ወይን ጠጅ + ውሃ ሰማያዊ = ጥቁር




ስዕል 12፡በብርሃን ደረጃ የጥቁር ቀለም ግኝትን የሚያሳይ ስዕል

# ሰው-ሠራሽ ቀለማት

**ልምምድ 6**

ሰው-ሰራሽ ቀለም ማለት ምን ማለት ነው?

ሰው-ሰራሽ ቀለም ማለት የሰው ልጅ በአካባቢው ከሚገኙ የማንኛውም ቀለም ሊሰጡን የሚችሉ ነገሮች ጨምቆ፣አደባልቆ፣ቀላቅሎ ለቅብ ስራ የሚጠቀመው ቀለም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ሰው-ሰራሽ ቀለም ከተለያዩ ነገሮች ላይ ሊሰራ የሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ከቅጠላት፣ አበባዎች፣ የዛፍ ፍሬዎች፣ ስራ ስር፣ አመድ፣ ከሰል የተለያዩ ቀለም ካላቸው አፈራት እና ሌሎች በውስጣቸው ቀለም ይዘው ከሚገኙ ከማንኛውም ነገር ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ እነኚህን ቀለማት እንደ ፍላጎታችን በማደባለቅ የትኛውም ለቅብ የተዘጋጀ ስፍራ ላይ መቀባት ስለምንችል ለቅብ የሚያገለግሉ ቀለማት ተብለው ይታወቃሉ፡፡ በራሳችን ጨምቀን፣ቀላቅለን የምናመርታቸው ቀለማትም እንደ ሌሎች የቀለማት ዝርያ መደብ/ደረጃ አላቸው፡፡ ይህም ደረጃ በሶስት ትላልቅ ስፍራ ይከፈላል፡፡ እነርሱም፤


1. አንደኛ ደረጃ ቀለማት
2. ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት
3. መካከለኛ (ሶስተኛ) ደረጃ ቀለማት

## ሀ. አንደኛ ደረጃ ቀለማት (ንጥረ ቀለማት)


አንደኛ ደረጃ (ንጥረ ቀለማት) በተፈጥሮ ከልተገኙ በስተቀር በመደባለቅ እና በመቀላቀል አይገኙም፡፡ ስለዚህም አንደኛ ደረጃ በማለት እንጠራቸዋለን፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ቀለማት ለሺዎች ቀለማት መፈጠር ምክንያት በመሆናቸው እና እነሱን ደግሞ ከሌሎች ቀለማት ደባልቀን የማናገኛቸው ስለሆነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንዳቸውን ከሌላው ቀለም ጋር በመደባለቅ የምንፈልገውን የትኛውንም ቀለማትን መፍጠር እንችላለን፡፡ ስለዚህ እነዚህን ቀለማት በተፈጥሮ ከሚገኙ ነገሮች ላይ

የምናመርታቸው እንጂ ስናደባልቅ የምናገኛቸው አይሆኑም፡፡ አንደኛ ደረጃ ቀለማት በቀለማት ቻርት ላይም እኩል የሆነ ርቀት ጠብቀው የሚቀመጡ ሆነው፣ብዛታቸው ደግሞ ሶስት ናቸዉ፡፡ እነሱም፤

1. ቀይ
2. ቢጫ
3. ሰማያዊ



ለቅብ የሚውሉ ቀለማት ሁሉ በአንድ ላይ ሲቀላቀሉ ደግሞ ሶስቱ ያልሆነ ግርጫማ (የደፈረሰ) ቀለም ይሰጣል





ስዕል 13፡የአንደኛ ደረጃ ቀለማትን የሚሳይ ስዕል

## ለ. ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት

ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ንጥረ-ቀለማትን (መሰረታዊ ቀለማትን) በማደባለቅ የሚገኝ ሆኖ እኩል በሆነ ብዛትና መጠን ሁለት ሁለቱን በመደባለቅ የምናገኛቸው ይሆናል፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ቀለማት ተደባልቀው የሚገኙት ቀለሞች ብዛታቸው ሶስት (3) ናቸዉ፡፡

እነሱም፡-

1. ብርቱካን
2. አረንጓዴ
3. ወይን ጠጅ



## ሁለተኛ ደረጃዎች ቀለማት የሚፈጠሩበት ሁኔታዎች

ቀይ + ቢጫ = ቡርቱካን

ቢጫ + ሰማያዊ = አረንጓዴ

ሰማያዊ + ቀይ = ወይን ጠጅ

እነኚህ ቀለማትም በ ዑደት ላይ ሲመጡ እኩል የሆነ ርቀት ይቀመጣሉ፡፡




ስዕል 14፡የሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ዑደት የሚሳይ ስዕል

### ሐ. መካከለኛ (ሶስተኛ ደረጃ) ቀለማት

ሶስተኛ ደረጃ ቀለማት መካከለኛ ቀለም ተብለው ይጠራሉ፡፡ ምክንያቱም በቀለማት ዑደት ላይ በመሰረታዊ ቀለማት እና ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት መካከል ስለሚገኝ ነው፡፡ መካከለኛ ቀማት በሁለት መንገድ መፍጠር እንችላለን፡፡ እነሱም፡-

1. ሁለት መሰረታዊ (አንደኛ ደረጃ) ቀለማትን ብልጫ ባለው (እኩል ባልሆነ መንገድ) በመደባለቅ መፍጠር፡፡
2. ቀጣዩ ሶስተኛ ደረጃ ቀለማትን መፍጠርያ ዘዴ ደግሞ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ቀለም እና ሌላ አንድ መሰረታዊ ቀለም እኩል በሆነ መንገድ ሲደባለቅ ነው፡፡

በነዚህ መሰረት የፈጠሩት ቀለማት ብዛት ደግሞ ስድስት ናቸው፡፡ ስድስቱም የሶስተኛ ቀለም አይነቶች በሁለት የመካከለኛ ቀለም መፍጠሪያ መንገድ ሊገኙ ይችላሉ፡፡

**የሶስተኛ ደረጃ ቀለማት አፈጣጠር ፡-** ሁለቱም ዘዴዎች በአንድ ላይ እንመልከት

- ቀይ + ቡርቱካናማ = ቀይ- ብርቱካናማ
- ብዛት ያለው ቀይ + አነስተኛ ቢጫ = ቀይ-ብርቱካናማ
- ቀይ + ወይን ጠጅ = ቀይ- ወይን ጠጃማ
- ብዛት ያለው ቀይ + አነስተኛ ሰማያዊ = ቀይ- ወይን ጠጃማ
- ብጫ + አርንጓዴ = ብጫ- አርንጓደያማ
- ብዛት ያለው ብጫ + አነስተኛ ሰማያዊ = ብጫ- አረንጓደያማ
- ብጫ + ቡርቱካን = ብጫ- ብርቱካናማ
- ብዛት ያው ብጫ + አነስተኛ ቀይቀለም = ብጫ -ብርቱካናማ
- ሰማያዊ + ወይን ጠጅ = ሰማያዊ- ወይን ጠጅ
- ብዛት ያው ሰማያዊ + አነስተኛ ቀይ ቀለም = ሰማያዊ- ወይን ጠጅ
- ሰማያዊ + አረንጓዴ = ሰማያዊ- አረንጓዴ
- ሰማያዊ በብዛት + አነስተኛ ብጫ ቀለም = ሰማያዊ - አረንጓዴ





ስዕል 2.11፡የሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ዑደት የሚሳይ ስዕል

## 2.1.6 የቀለማት ዑደት/ ቻርት

የቀለማት ዑደት/ቻርት አንዳንዴ ክብ የሆነ የቀለማት ማሳያ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህ የቀለማት ዑደት/ቻርት ክባዊ ቅርፅ ባላ 360 ዲግሪ በሚሽከረከር ቻርት ላይ የሚቀመጥ ሆኖ የቀለማት ግንኙነት አልያም ጥምረት ጠብቆ የሚሰራ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ቻርት ቀለማት ያላቸው ሕብረት፣የመቀላቀል ግንኙነት፣በቀለማት መካከል ያለውን የደረጃዎች (1ኛ 2ኛ እነ 3ኛ ደረጃ) ልዩነት እና የቀለማቱ ዝምድና ወይም ተቃራኒነትን በአንድ ስፍራ የሚያሳይ ቻርት ነው፡፡ ይህ የቀለማት ቻርት ለሰዓሊም ሆነ ለሌች እጅግ በጣም አስፈላጊ የሚያደርገው ቀለማት ያላቸውን አብሮ የመሄድ ባህርይን ለመገንዘብ ነው፡፡

## 1. ተቃራኒ ቀለማት

ተቃራኒ ቀለማት ማለት በቀለማት ዑደት ማሳያ/ቻርቱ ላይ ትይዩ በሆነ አቅጣጫ ተቀምጠው የሚታዩ ናቸው፡፡ ተቃራኒ ቀለማት አጠገብ ለአጠገብ ብንቀባ የዐይናችን እይታ አረፍ ብሎ እንዳይቆይ አልያም እንዲርገበገብ በማድረግ እይታችን ከበድ የሚል ስሜት እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡ ስለዚህም ቅባዊ ስዕል ወይም ዲዛይን ስንሰራ ተቃራኒ ቀለማት በማከታተል ባይሆን ይመረጣል፡፡ እርስ በእርስ ሲደባለቁም የተረሸ/የደፈረሰ የቀለም ዝርያን በመፍጠር ይታወቃሉ፡፡ እነዚህን ቀለማት እስኪ እንመልከታቸው፡- ብጫ ከወይን ጠጅ ጋር፣ቀይን ከአረንጓዴ ጋር፣ሰማያዊን ከብርቱካናማ፣ብጫ አረንጓደያማን ከቀይ ወይን ጠጃማ ጋር እና ሰማያዊ ወይን ጠጃማ ከብጫ ብርቱካናማ ጋር ማለት ነው፡፡




ስዕል 16፡ተቃራኒ ቀለማትን የሚሳይ ስዕል.


**ልምምድ 1**

በመጀመሪያ የቀለማትን ቻርት ስላችሁ ቀለማትን ከቀባህ/ሽ በኋላ እንደገና በስዕል 16 እንደተቀመጠው ተቃራኒ የሆኑትን ለብቻቸው ከቀባህ/ሽ በኋላ ያጋጠሙህን/ሽን ችግሮች እና ከስራችሁ ላይ ምን እንደተረዳችሁ ለክፍላችሁ ተማሪዎች ተራ በተራ ግለጹ፡፡

## ትይዩ የሆኑ ቀለማት

ትይዩ ቀለማት የሚባሉት በክብ መልክ የተቀመጡ የቀለም ዑደት/ ቻርት ላይ ተከታትለው የሚወጡ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡ ቀይ፣ቀይ-ብርቱካናማ ፣ ብርቱ ካናማ ፣ቢጫ-ብርቱካናማና ቢጫ ናቸው፡፡



ስዕል 2.13፡ ተቃራኒ ስዕሎችንየሚሳይ ስዕል

## 2.1.7. የቀለማት ሙቀት መለኪያ /ቴምፕሬቸር/

የቀለም የሙቀት መጠን/ቴምፕሬቸር በሚባልበት ጊዜ ሞቃታማና ቀዝቃዛማ ቀለም በእጃችን በምንነካበት ጊዜ ማለት አይደለም፡፡ ሰውነታቸውና የሰው አእምሮአቸው የሚፈጥሩት ሁኔታና ስሜት ማለት ነው፡፡ ቀለም ጉልበት አለው፡፡ ቀለም የሰውን አእምሮ በፍጥነት የመቀየር ችሎታ አለው፡፡ በሚያሳዩት የሙቀት መጠን(ቴምፕሬቸር) ላይ በመመስረት ቀለማት በሁለት ትልልቅ ቦታ ይከፈላሉ፡፡ አነርሱም፡-

ሀ. ቀዝቃዛማ ቀለማት
ለ. ሞቃታማ ቀለማት

### ሀ. ቀዝቃዛማ ቀለማት

ቀዝቃዛማ ቀለማት ማለት በእጃችን ስንነካ የሚቀዘቅዝ ማለት አይደለም፡፡ ስሜቱ በአእምሮአችን ላይ ይፈጠራል ማለት ነው፡፡ ያሉት ቀዝቀዛማ ቀለማት ስድስት (6) ናቸው፡፡ እነርሱም

ከአንደኛ ደረጃ ቀለማት አንድ አለ፡፡ እርሱም ፡

ሰማያዊ

ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ሁለት አሉ፡፡ እነርሱም ወይን ጠጅና አረንጓዴ

ከሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ሶስት አሉ፡፡ እነርሱም

- ✓ ሰማያዊ ወይን ጠጅ
- ✓ ሰማያዊ አረንጓዴ
- ✓ ቢጫ አረንጓዴ

ብርዳም ቀለማት የውሃ አካል፣ የክረምት ወቅት እና ከመሳሰሉት ጋር ይመሳሰላል፡፡

ብርድ ወይም ቅዝቃዜ በሰው ውስጥ መፍጠር፣ ለድብርት መጋለጥ በአእምሮ ላይ ሚና ይፈጥራል፡፡


- የተረጋጋ ስሜት፣ዝምተኝነት እና የመሳሰሉትን ይፈጥራል፡፡
- የወንዶች ቀለማት ነው፡፡

## ለ. ሞቃታማ ቀለማት

ሞቃታማ ቀለማት ማለት በእጃችን ስንነካ ያሞቀናል ወይም ያቃጠለናል ማለት አይደለም፡፡ በአእምሮአችን ላይ የሚያስከትሉት ስሜት ማለት ነው፡፡ ሞቃታማ ቀለማት ስድስት ናቸው፡፡ እነርስም፡
ከአንደኛ ደረጃ ቀለማት ውስጥ ሁለት አሉ፡፡ እነርሱም፡ ቀይ እና ብጫ
ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ውስጥ አንድ አለ፡፡ እርሱም፡ ብርቱካን
ከሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ውስጥ ሶስት አሉ እነርሱም፡-

- ቀይ- ወይን ጠጅ
- ቀይ -ብርቱካን
- ቢጫ -ብርቱካን

- ከፍተኛ ሙቀት በሰው ውስጥ ይፈጥራል፡፡
- ሩቅ ላይ ያሉትን ነገሮች አቅርቦ ያሳየናል፡፡
- ሞቃታማ ቀለማት ከእሳት አካል፣ከቮልካኖ ከበጋ ወቅት እና ከመሳሰሉት ጋር ይመሳሰላሉ፡፡
- የሰውን ስሜት ይቀሰቅሳሉ፡፡
- የሴቶች እና ህጻናት ቀለማት ናቸው፡፡





ስዕል 18፡የቀለማትን ተምፕሬቸር የሚሳይ ስዕል

**ልምምድ 2**

**የቀለማትን ቴምፐሬቸር ስዕል የሚያሳይ ስዕል 18 ላይ እንደተገለጸው አስመስለህ ከሰራሽ/ህ በኋላ ቅባ/ቢ፡፡ እንዲሁም ከዚህ ስራ ያገኘኸውን/ሽዉን እውቀት ለክፍል ተማሪዎች ግለፅ/ግለጪ፡፡**


## 1.1.7. የምናያቸው የቀለም ፍጥረት ሁኔታ

የፀሀይ ብርሃን ወይም እስፔክትረም የተለያየ ቀለማትን ከውስጡ እንዳለ ተምረችኋል፡፡ ይህ በአይናችን ያየነው ቀለም ቀይ ወይም ሰማያዊ ብለን የምንለያቸው የሚመነጨው ከፀሀይ ብርሃን ነው፡፡ አንድ ነገር ባህርይው ለብቻው ያለው ሞገዶች ከውስጡ ይዞ በሚያስቀርበት ጊዜ ሎሎችን ደግሞ በማንጸባረቅ ያሳያቸዋል፡፡ የጸፀሐይ ብርሃን ጨረር በቀለም የተቀቡ አካላትን ላይ ሲያርፍ ሞገድ ያላቸው አካላት የአቶማቸው ግንባታ ጋር የሚዋሃደዉን ከላይ በማንፀባረቅ ሌሎችን የማይዋሀደዉን መጦ ያስቀራል፡፡ ለምሳሌ፣ ቀይ መልክ ያለው ልብስ ሎሎች ቀለማትን በመምጠጥ የቀይ ቀለም ብርሃንን ያንጸባርቃል፡፡ እንዲሁም የጸሀይ ብርሃን የተለያዩ ቀለማት ያለው ሰማያዊ ወይም አረንጓዴ ቀለም መልክ ያለው ላይ ሲያርፍበት ሌሎች የቀለማት መልክ ሞገድ በመምጠጥ ሰማያዊና አረንጓዴ ቀለም ወደ ላይ በመንጸባረቅ ይታያሉ፡፡




ስዕል 5፡ስዕሎችን እንዴት እንደሚታዩ የሚገልጽ ስዕል

ይህ ማለት አንድ ቀለም መልክ ያለው ነገር የሚታየው ነገር ቀለማት በብርሃን ጨረር ውስጥ ያሉትን በውስጡ በማስቀመጥ የራሱ ቀለም የሆነ በማንጸባረቅ ያሳያል፡፡ ጥቁር መልክ ሰባቱ እስፔክትረም ቀለማትን እንዳለ በማሳመን ጥቁር የሆነ መልክ እንዲታይ የሚያደርግ ሲሆን ነጭ ቀለም ደግሞ ብርሃን ሲያርፍበት ሁሉም የፀሃይ ብርሃን ቀለማትን መልስ በማንፀባረቅ ነጭ መልክ ይዞ እንዲታይ ያደርጋል፡፡.



ስዕል 6፡የነጭና ቀይ ቀለም መታያ ሁኔታን የሚገልጽ

# ለቀለም ቅብ ሥራ የሚየስፈልጉ ነገሮች

- ቀለም (የውሃ ወይም የዘይት)
- ቀለም መቀቢያ ወይም ብሩሽ
- የቀለም ሸራ
- እዝል
- ፓሌት (ቀለም ማደባለቂያ ዕቃ)
- ውሃ ወይም ዘይት እና የመሳሰሉት

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ውስጥ ቀለም ዋናው የቀለም አቀባብ ስራ ለመስራት ምርጫ ወይም ምትክ የሌለው ነው፡፡

## ሀ. ለቀለም ቅብ ስራ የሚያስፈልጉ የቀለማት አይነቶች

የቀለም አቀባብ ዓይነቶች በተለያዩ ቀለም ይሰራል፡፡ የቀለም አቀባብ የሚሰሩ ከጥንት አመት ጀምረው የተለያዩ ነገሮችን በቀለም አቀባብ ስራ ውስጥ ስሜት፣ሐሳብና ሊያስተላልፉ የሚፈልጉትን መልዕክት ለማስተላለፍ እንዲመች አድርገው የቀለም ቅብ ስራ እየተጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ አንድ ባለሙያ የቀለም ቅብ ስራ ከመስራቱ በፊት የሚሰራውን ነገር ለማወቅ ወይም ንድፉን ማዘጋጀት እንዳለበት የቀለም ዓይነት ከንድፉ ጋር የሚሄድና ሀሳቡን ለመግለፅ የሚመቸውን ለይቶ ማወቅ አለበት፡፡ ይህ ማለት ለቀለም ቅብ ስራ ለመስራት የሚውሉ ሁሉም የአንድ አርቲስት መልእክት ወይም ሀሳብ እኩል ማስተላለፉ ላይ ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የተወሰኑ መሳሪያዎች የቀለም ቅብን ልንሰራባቸው የሚችሉ እና በቀላሉ በአካባቢ የሚገኙ ከዚህ በታች ያሉት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- ✓ ፓስተል
- ✓ ኪራዮን

- ✓ የተለያየ ቀለም ያለው እርሳስ
- ✓ የዘይት ቀለም
- ✓ የውሃ ቀለም




ስዕል 19፡ፓስቴልን የሚሳይ ስዕል




ስዕል 20፡ክራዮንን የሚሳይ ስዕል

## ሀ. የውሃ ቀለማት

የውሃ ቀለማት ቅብ ታሪኩ ከድሮ ዘመናት ጀምሮ ሰዎች ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑን ብዙ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ የውሃ ቀለም የሚል ስያሜ ያገኘው ቀለሙ ውሃን በመጠቀም የሚቀጥን/የሚበጠበጥ/ በመሆኑ ነው፡፡ ይሄን ለመረዳት ደግሞ በሰሜን የኢትዮጵያ ክፍል የተሰሩ የሀይማኖታዊ ስዕላት ላይ ማየት ይቻላል፡፡ የውሃ ቀለም አቀባቡ ከብርሃን ወደ ጥላ የሚቀባ ነው፡፡ ምክንያቱም የማንቀባባቸው ስፍራ ነጭ ቀለም ያለው

ከሆነ የምንጠቀምባቸው ቀለማት ላይ ብርሃናማ ቦታ ለመፍጠር ነጭ ቀለምን የምንጠቀም ይሆናል፡፡ ቅባችን ብርሃንና ጥላ ሳይጠብቅ የተሳለ ከሆነ የምንፈልገውን ስሜት መልዕክት ሀሳብ ላያስተላልፍ ይችላል፡፡ እንዲሁም በውሃ ቀለም ቅብ ውስጥ ልንጠቀመው ከሚገባ ነገሮች አንዱ ቀለሞቹን የምንቀባበት ቅደም ተከተል ነው፡፡ ምክንያቱም የቀባነው ቀለም ለማጥፋት አስቸጋሪ ነው፡፡ የስእሉን ውበት የሚያጠፋ ነው፡፡ የውሃ ቀለምን የምንቀባበት የአቀባብ ዘዴዎች በሁለት (2) ይከፈላል፡፡ እነሱም እርጥብ በእርጥብ ላይ የአቀባብ ዘዴ እና ደረቅ ስፍራ ላይ ቀለሙን በመቀባት የሚከናወን ነው፡፡ በደረቅ ወረቀት ላይ የምንቀባው የውሃ ቀለም ቅብ የተለያዩ ፍካት ለመፍጠር ይረዳል፡፡ ለምሳሌ ድንጋያማ ምድርን፣የተለያዩ ብርሃንና ጥላ ያላቸው የመሬት አቀማመጥና የመሳሰሉት ስፍራዎች ላይ የሚታዩ ፍካትን በምስል ላይ ማሳየት እንችላለን፡፡ የትኛውንም የውሃ ቀለም ቅብ ለመቀባት የምንጠቀመው ብሩሽ በጣም ለስላሳ እና የቡሩሽ ጫፍ ውሃና ቀለምን በውስጡ መሸከም የሚችል መሆን አለበት፡፡



ስዕል 21፡በዉሃ ቀለም ቅብ የተሰራ ስዕልን የሚያሳ

## ልምምድ 3

**የውሃ ቀለም በመጠቀም የሚከተለውን ሥዕል ሠርታችሁ አሳዩ፡፡**



### 2.1.8. የቀለም አቀባብ አካላት

#### ተግባር 1

1. የቀለም ቅብ ስራ አካላት ማለት ምን ማለት ነው?

2. የቀለም ቅብ ስራ አካላት ምን ምን እንደሆኑና ጥቅማቸው በስነ-ጥበብ ውስጥ ያላቸው በቡድን ተወዩበት፡፡

የቀለም ቅብ ስራ አካላት የመሰረታዊ ግንባታ የቀለም ቅብ ስራ ዘርፍ አንዱ ነው፡፡ በሌላ ትምህርት ላይ የስነ-ጥበብ አካላት ሰባት (7)

እንደሆኑ ተምረሃል/ሻል፡፡ ግን፣በስነ-ስዕል ስራዎች ዓይነት እንደ የቀለም ቅብ ስራና ንድፍ ውስጥ ፎርም አያስፈልግም ወይም ይቀራል፡ ፡ ስለዚህ የቀለም ቅብ ስራ አካላት ስድስት (6) ናቸው፡፡እነርሱም፡-

- ቀለም
- ፍካት(ብርሃን እና ጥላ ቶን)
- መስመር
- ቅርፅ
- ቦታ
- ለስላሳነት ወይም ሸካራነት

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት አካላት ውጪ የቀለም ቅብ ስራ መስረት በፍጹም አይታሰብም፡፡ እየአንዳንዳቸው በየቦታቸው የየራሳቸው መልዕክት እና ለየብቻቸው የሚያስተላልፉት መልዕክት አላቸው፡፡ ግን በአጠቃላይ በአንድ ላይ በሚቆሙበት ጊዜ ወይም ሲቀናጁ ደግሞ ሙሉ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡

### 1. ቀለም

ከቀለም ቅብ ስራ ውስጥ ቀለም ዋናው ስለሆነ ምትክ የሌለው ነው፡፡ ቀለም ከቀለም ቅብ አካላት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ስለሆነና ደረጃ /ቶን/ የተመልካቾችን ስሜት በዚያ ስራ ላይ ያላቸውን የሚያቀናጅ ነው፡፡ እንዲሁም ስሜትን የሚያነሳሳ ወይም የሚያረጋጋ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰዎች በቀለም ቅብ ስራ ዉስጥ የሚሰሩት በቀለም ልዩነት ወሰን የለውም፡፡ ስለ ቀለም ለማወቅና ለመጠቀም የቀለም ንድፈ-ሀሳብ ማወቅ


በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይ የቀለም አቀባብ ስራ ለሚሰሩ ሰዎች በጣም ያስፈልጋቸዋል፡፡

## 2. የብርሃንና ጥላ ደረጃ /ቶን/

**ድርጊት 2**

በቀለም ቅብ ዉስጥየብርሃንና ጥላደረጃ/ቶን ምን ማለት ነዉ? እንደ አቀማመጣቸዉ ጎን ለጎን በያሉላችሁ በዝህ ላይ ተወያዩ፡፡

ቶን ማለት ብርሃናማነት ወይም ብኘርታማነት ቀለም ነው፡፡ ቶን/የብርሃንና ጥላ ደረጃ ዝርግ ቦታ ወይም ለጥ ያለ ቦታ ያላቸው ላይ ፎርም ለመሳል ይረዳል፡፡ የቶን ልዩነት ፎርም የሆኑ ነገሮች ቀለም በሚሰሩበት ጊዜ በእጅ መጨበጥ/መንካት የሚቻለው መስሎ እንዲታየን ያደርጋል፡፡እንዲሁም በጥልቅና በመራራቅ ወይም የምት ድግግሞሽ እንዲፈጠር ይረዳል፡፡ የተለያዩ የቶን አይነቶች ለቀለም ቅብ ይህ ነው የማይባል አስተዋፅኦ አለው፡፡ እየአንዳንዱ የቀለም ቅብ ስራ የተወሰነ ቶኖች ስላለው ሌሎች ደግሞ ሙሉ በሙሉ የተለያዩ ቶኖች ያላቸው አሉ፡፡ ቶን የሚታየው በቫሊዩ /እስኬል/ ደረጃ ላይ ነው፡፡ የጠቆረው ቶን በእስኬል ላይ በጣም የሚጠቁር ሲሆን በብርሃን ደግሞ በጣም ብሩህ ይሆናል፡፡ በቀለም ቅብ ስራ ውስጥ ከፍተኛ ጨለማ በጥቁር ሲገለፅ ከፍተኛ ብርሃን ደግሞ በነጭ ቀለም ይገለፃል፡፡ ስለዚህ በቀለም ቅብ ውስጥ እንዲጠቁር ወይም እንዲነጣ በማድረግ ሁለቱን በአንድ ላይ በማቀላቀል የቀለም ቅብ ስራ መስራት ይቻላል፡፡



ስዕል 1፡የቀለማትን ኻልዩ እስኬል የሚሳይ ስዕል

## 3. መስመር

የንድፍ ስራን ለመስራት መስመርን መሰረት አድርገን እንደምንነሳ በቀለም ቅብ ስራ ውስጥም በመስመር ላይ እናተኩራለን፡፡ መስመር ምልክት ወይም የቀለም መቀቢያ /ብሩሽ መነሻ ሆኖ ሁለቱ የዲዛይን አካላትን በማገናኘት የሚፈጠር ነው፡፡ መስመር በስነ-ጥበብ ስራ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች እንገለገልበታለን፡፡ ቅርፅ፣ ፓተርን፣ ፎርም፣ ግንባታ፣ እድገት፣ ጥልቀት፣ምት፣እንቅስቃሴና የስሜት ደረጃ ለማሳየት ይረዳል፡፡ አንድ የቀለም ቅብ ስራ የሚሰራ ሰው የተለያዩ የመስመር አይነቶችን ለይቶ መጠቀም አለበት፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰው የመሬት አቀማመጥ የቀለም ቅብ ለመስራት የአግድም መስመሮችን በትክክል መመልከት አለበት፡፡

## 4. ቅርፅ

ማንኛውም የስነ-ጥበብ ስራ የቅርፅ አካላትን የመስመር እና ቦታ የያዘ በውስጡ ያካትታል፡፡ ቅርፅ ክብ የሆነ ቦታ መስመሮች በሚገናኙበት

ጊዜ ይፈጠራል፡፡ አርቲስቶች በሁሉም ነገር ውስጥ እንዴት ቅርፅ እያዩ እና እራሳቸውን ማለማመድ አለባቸው፡፡

## 5. ቦታ

ቦታ ማንኛውም በስነ-ጥበብ ስራ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነ እና በቀለም ቅብ ስራ ውስጥ እንደ ትልቅ ግብአት የሚያገለግል ነው፡፡ በስነ-ጥበብ ስራ ጊዜ ውስጥ ስለ ቦታ ስናወራ ስለ ቦታ ሚዛን ፖዘቲቭ ወይም ነገቲቭ ማሰብ አለብን፡፡ፖዘቲቭ የሚባለዉ ቦታ የቀለም ቅብ ስራ የተፈለገ ቦታ ሲሆን፣ነገቲቭ የሚባለዉ ቦታ ግን ነጻ አካባቢ የሚሰራበት ነገር ወይም መካከል የሚሰራበት ነገር የሚቀርበት ማለት ነው፡፡ስለዚህ አንድ አርቲስት ስራ በሚሰራበት ጊዜ ሁለቱን ሚዛኖች በመጠበቅ እንዴት የተመልካቾችን ሃሳብ እንደሚስብ አውቆ መስራት አለበት፡፡ ለምሳሌ ፣የቀለም አቀባብ ከሰው አንገት በላይ በጎን አቅጣጫ (የፊት ቦታ ወደ ነገቲቭ) ዞሮ የሚሰራ ወደ ተመልካቾች ፊት ዞሮ ከተሰራ ይበልጥ ሰውን ይስባል፡፡

## 6. ሸካራማነት እና ለስላሳነት

### ውይይት 2

ሸካራማነት ወይም ለስላሳማነት ከቀለም ቅብ ስራ ውስጥ እንዴት ይሰራል ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን ተወያዩበት፡፡

የቀለም ቅብ ስራ ስልት ትክክለኛ የሸካራማነት እና የለስላሳማነት ስራ ለመፍጠር ይረዳል፡፡ ይህም በቀለም ቅብ ስራ ውስጥ እንደ ፓተርን ወይም እንደ መቀቢያ መስመር እንዲፈጠር ሆኖ ይገለጻል፡፡ አንዳንድ ቅብ በተለይ የዘይት ቀለም ቅብ ወፍራም ስለሆነ በስዕል ሸራ ወይም ገበታ ስራ ላይ ሲውሉ ለዚያ ስራ ትልቅ የሆነ ጥልቀት ይሰጣል፡፡

እንዲሁም ደግሞ ሸካራማነት እና ለስላሳማነት ለቀለም ቅብ ስራ ለሚሰሩ አርቲስቶች በስራ ዉስጥ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ለምሳሌ በሚያንጸባርቀዉ ገጽታ ወይም በአለታማ መሬት የተሸነ የቀለም ቅብ ስራ ታግዞ ሸካራማነትና ለስላሳማነት ካላቸዉ ፍጥረታት ከተሰሩ ለማሳየት ትንሽ ሊከብድ ይችላል፡፡ ስለዚህ አርቲስት ሻካራማነት ወይም ለስላሳማነት እንደዚህ ነገር ለመፍጠር ሌላ የዲዛይን አካላትን እንደ መስመር ፣ቀለም፣ ቶን ወይም ቫሊዩ እና የመሳሰሉት ላይ መመርኮዝ ወይም መታገዝ የግድ ይሆናል፡፡



.

ስዕል 2፡የዘይት ቀለም ስራ ሸካራማነትና ለስላሳማነትን የሚሳይ ስዕል፡

# የዘይት ቀለሞች

የዘይት ቀለም የሚባለው መጠሪያ ስም ያገኘው ከራስ ማቅጠኛ በመነሳት ነው፡፡ ለዚህ የቀለም አይነት የሚያገለግሉ ማቅጠኛ ፈሳሽ ዘይቶች/ቅባት/ ናቸዉ፡፡

የዘይት ቀለም ቅብ ስራ ብዙ ጊዜ ከጥላ ወደ ብርሃን ይቀባል፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ማቅጠኛ ፈሳሽ ቁስ የዘይት ቀለሙ በቶሎ የማይደርቅ ስለሆነ እና ሰዓሊያችን የቀለም ቅብ ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የዘይቱን ቀለም እዛው የቀለም ቅብ ስራ መስሪያ ሰሌዳው ላይ ቀለሙን እያዋሀዱ እንዲሰሩ ስለሚያግዛቸው ነው፡፡

እንዲሁም የዘይት ቀለም ቅብ ከሌላው የሚለየው አንዱ ባህሪ በስህተት አስቀድመን የቀባነውን ቀለም በሌላ ቀለም መቀየራችን እና ስናቀጥነው ከዘይት ሌላ እንደ ጋዝ ቅባት አኳራጅ መጠቀም መቻላችን ነው፡፡



ስዕል 22፡በዘይት ቀለም ቅብ የተሰራ ስዕልን የሚያሳ

**ልምምድ 3**

1. የውሃ ቀለምን በመጠቀም የምትፈልገውን ምስል ሰርተህ አሳዩ?
2. የዘይት ቀለም በመጠቀም የምትፈልገወን ምስል ሰርተህ አሳዩ?

## 2.1.2.የህትመት አሰራር ሂደት

የህትመት አሰራር ዘዴዎች ብዙ ናቸው፡፡ ይሁን እና በአሰራራቸው እና በሚሰጡት ጠቀሜታ ላይ ተመርኩዘን የተወሰኑትን ብቻ በዚህ ክፍል እንመለከታለን፡፡ ምክንያቱም የህትመት ስራዎች ከቀላል ህትመት ስራ እስከ ከባድ የማሽን ህትመት ስራ የሚያካትት በመሆኑ ነው፡፡

### 2.1.2.1 የህትመት አይነቶች

እንደሚታወቀው ህትመት ማለት አንዴ ተዘጋጅቶ ዲዛይን ወይም ቅርፅ በተደጋጋሚ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በማባዛት ስንሰራ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዲዛይኑ አሰራር ላይ በመመርኮዝ የህትመት አይነት መጠሪያ ሂደቱ ከቀላል እስከ ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም የህትመት አይነቶች ብዛት ሊኖራቸው የሚችል እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን በአካባቢያችን የምናገኛቸው ማተሚያ እቃዎች እና አቅሞች (በተማራችሁው እውቀት) ላይ በመመርኮዝ ከዚህ በታች ያሉትን አይነቶች እናያለን፡፡እነርሱም፡-

1. ቀጥተኛ ህትመት (እንዳለ ማተም)
2. የእስቴንስ ህትመት

#### 1.ቀጥተኛ ህትመት (እንዳለ ማተም)

እንዳለ ማተም ማለት ካላይ የምናትመው ነገር እንደ አስፈላጊነቱ ሳቀይረው ወይም በተፈጥሮ እንዳለ ስናትመው ነው፡፡ ይህ ህትመት ዘዴ ከሌሎች የህትመት ዘዴዎች በተሻለ ቀላል እና በፍጥነት ምንፈልገውን አካል በብዛት የምናትምበት መንገድ ነው፡፡

ለዚህ ህትመት ከሚያስፈልጉት አካለት መካከል፣ቅጠል፣አበባ፣የዛፍ ፍሬ የእጅ እና የእግር መዳፍ፣ልብስ፣ድንጋይና የመሳሰሉትን ቀለም በማስነካት የምናትምበት ነገር ላይ በማተም የሚሰራ ህትመት ነው፡፡

## ልምምድ 4

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተል በማንበብ ከዛፍ ቅጠሎች የምትፈልገውን ዲዛይን ከሰራችሁ በኋላ ምን እንደተገነዘባችሁ በክፍል ውስጥ ግለፁ፡፡

ለዚህ ህትመት ስራ የሚያስፈልጉት ነገሮች፤

- የዛፍ ቅጠል
- መደመጫ
- ጠፍጣፋ መስታወት/ስንደምጥ የማይቆረቁር/
- ቀለም
- እስፖንጅ /ብሩሽ/
- የሚታተምበት ነገር/ወረቀት፣ክላሴር እና የመሳሰሉት/

### የህትመት አሰራር ዘዴ

- የምንፈልገውን የቅጠል ዲዛይን በመምረጥ ማዘጋጀት
- ቅጠሉን በመዘርጋት ቀለም መቀባት ወይም የምንፈልገውን የቅጠሉን ገፅ ቀለም መንከር እና ሁሉም የሚፈልገውን የቅጠሉን ገፅታ ሳይበዙ ቀለሙን መደረብ፡፡
- የተቀባውን ቅጠል እንዳይተጣጠፍ በመጠበቅ የተዘጋጀው ማተሚያ (ወረቀት፣ክላሰር እና ሌሎች ለጥ ያሉ ነገሮች) ላይ በማስተኛት መደመጥ
- ስንዳምጥ የምንፈልገው የዲዛይኑ ክፍል እንዳይበላሽ መጠንቀቅ አለብን
- ከተደመጠ በኋላ ቅጠሉን በአግባቡ ተጠንቅቀን ማንሳት
- ከህትመቱ በኋላ የታተመው የቅጠሉ ዲዛይን ለማየት እንደአስፈላጊነቱ በመደጋገም ማተም

- የሚፈለገው የህትመት ዲዛይን ከመጣልን በኋላ ያተምነው እንዲደርቅ አመቺ የሆነ ቦታ ላይ ማስቀመጥ



ስዕል 23. ቀጥተኛ ህትመት የሚያሳይ ስዕል፡፡

**መልመጃ 5**

ከቅጠል የሚያምር የልብስ ዲዛይን /ፓረ,ተርን/ ወይም ድግግሞሽ ያለውን ህትመት ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

## 2.የእስቴንስል ህትመት

የእስቴንስል ህትመት ተጀመረበት አገር በሮማ ሲሆን ከጊዜ በኋላ እውቅናን ያገኘው በአሜሪካን አገር ውስጥ እንደ ሆነ ታሪክ ያሳያል፡፡ እንደ ስነ-ጥበብ እስቴንስል ማለት አንድ ዲዛይን ከተዘጋጀ በኋላ እንደአስፈላጊነቱ ከውስጥ ቀዶ/ቆርጦ በማውጣት ሌላ የህትመት ወረቀት ላይ የሚታተም የህትመት አይነት ነው፡፡ እስቴንስል ከወረቀት፣ ፕላስቲክ፣ልብስ እና የመሳሰሉት መሳሪያዎች በመጠቀም የምንፈልገውን ዲዛይን ልንሰራ እንችላለን፡፡


## ሀ. ወረቀት በማጠፍ ቆርጦ የተፈለገውን ዲዛይን መስራት


ለዚህ ስራ የሚያስፈልጉ ነገሮች

ለዲዛይኑ የሚያስፈልጉ መሳሪያ (ወረቀት፣ልብስ እና የመሳሰሉትን) ማዘጋጀት


- መቁረጫ (መቀስ እና መቁረጫ)
- የሚታተምበት
- ወረቀት
- ቀለም
- ልብስ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- መቀቢያ
- ማጣበቂያ

አሰራር







ወረቀቱን ሰያፍ/ስላሽ/ ማጠፍ




ስያፍ የታጠፈውን ወረቀት እኩል በሆነ ቦታ ማጠፍ




አሁንም ወረቀቱን እንደመጀመሪያው በደጋሚ ማጠፍ



የተጣጠፈውን ወረቀት ጫፍና ጫፍ ላይ እንደምንፈልገው ዲዛይን በእርሳስ ወይም ማርከር ማስምር፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ የተሰራውን ዲዛይን መስመሩን በመጠበቅ በታጋጀው መሳሪያ ቆርጦ ማውጣት፡፡










**መልመጃ 6**


በተማርከው የእስቴንስል መስሪያ ዘዴ ከተረዳህ በኋላ ከዚህ በታች ያሉትን ቅደም ተከተል በመጠበቅ ስራ፡፡

## ለ. የተዘጋጀው ዲዛይን ከውስጡ ቆርጠን በማውጣት ማተም


ይህ የእሴትን ህትመት የሚዘጋጅበት አዴ አስቀድመን የምንፈልገውን ዲዛይን ወይም ስዕል ከሳልን በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ የስእሉን አካል ከውስጡ ቆርጠን በማውጣት ነው፡፡ ስለዚህ የተሰራውን ዲዛይን በቅብ ከማተማችን በፊት ተቆርጦ የሚወጣውን እና ሳይቆረጥ የሚቀረውን




የስዕሉ አካል አስቀድመን በመወሰን ሊሆን ይገባል፡፡ ካልሆነ የምንፈልገው ዲዛይን በምናትምበት ጊዜ ሊመጣልን አይችልም፡፡ የተዘጋጀውን የእስቴንስል ዲዛይን ለማተም ያዘጋጀነው ስፍራ ላይ በመዘርጋት ቀለም ስንቀባ ስንረጭበት በምንፈልገው ስዕል ይታተማ ማለት ነው፡፡ የዚህን የእስቴንስል ህትመት ዘዴ ከዚህ በታች የፊደላት ዘዴ አቀራረፅ ማየት /መረዳት/ ይቻላል፡፡





የፊደላት ቀርፅ ከላይ እንዳየነው መቅረፅ




የተቀጋጀውን የፊደላት ቅርፅ ከላይ እንደሚያየው ቆርጦ ማውጣት




ተቆርጦ የወጣውን የፊደሉን ቅርፅ በቡርሽ ወይም በስፖንጅ በጥንቃቄ መቀባት




በጥንቃቄ የተጠቀምነውን የእስቴንስል ወረቀት ማንሳት




በመጨረሻም የስራው ውጤት ይህን ይመስላል፡፡

## 2.2.የሶልፌጅዮ ልምምድ በትዝታና በባቲ ቅኝት

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት**

**ከዚህ የትምህርት ርዕስ በኋላ፡**

-የሶልፌጅዮ ትርጉምና ጥቅም በመለየት ትናገራለህ/ሽ

-የተለያዩ የኖታ ዓይነቶችን ታነባለህ/ሽ

-የትዝታና ባቲ ቅኝቶችን ለይተህ ትገልጻለህ/ሽ

### 2.2.1. ሶልፌጅዮ

ድርጊት 1   ሀ.ሶልፌጅዮ ምንድነዉ?

ለ.ሶልፌጅዮ ከዉስጡ ምን ምን  ይይዛል?

ሐ. ሶልፌጅዮ  በሙዚቃ ዉስጥ ያለዉ ጥቅሞች ምን ምን ናቸዉ?

ሶልፌጅዮ የሚል ቃል ከጣሊያን ቋንቋ ሶል…ፋ ከሚል የሙዚቃ ድምጽ ስያሜ የመጣ ስሆን ትርጉሙ የሰዉ ልጅ  የጆሮ ችሎታ ሙዚቃ ሳይንስ  ማዳመጥ ያለዉና በምት ላይ ግንዛቤዉን የሚያዳብርበት ነዉ፡፡ ሶልፌጅዮ ምት ወይም ሪትምን በመጠቀም ዜማ ወይም የድምጽ ጣዕም በመለየት  ጆሮአችንን  እንድናለማምድ  ይረዳናል፡፡በሙዚቃ  ኖታ የተጻፉትን ምቶች እጅ በማጨብጨብ፤በእግር መሬት በመምታት፤ወይም በድምጻችን የምት ዋጋ እንዳላቸዉ ካነበብን ሶልፌጂዮን እየተማርን ነን ማለት ነዉ፡፡የተለያዩ የምት ምልክቶች በጆሮአችን ሰምተን ከጻፍን ሶልፌጅዮ መማር ሊሆን ይችላል፡፡ሙዚቃ ለመጻፍም ይሁን ለማንበብ ሶልፌጅዮ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

የተለያዩ ዘፈኖች እንቅስቃሴ ዉዝዋዜዉን ካየነዉ ሰዎች ከሚያደርጉት እጅ በማጨብጨብና ከበሮ በመምታት የሚያደርጉት ዉዝዋዜ እንደ ምሳሌ ብንወስድ ከዉስጡ ሶልፌጅዮ አለዉ፡፡

### 1. የሶልፌጅዮ ጥቅም

ሶልፌጅዮ እንደ ሌሎች ትምህርት በሂደት ወይም በልምምድ ይማራል፡ ፡የሶልፌጅዮ ሚና በሙዚቃ ሳይንስ ዉስጥ የሚጫወተዉና የሙዚቃ ችሎታን ለማዳበር የሚያበረክተዉ አስተዋጽዎ ከፍትኛ ነዉ፡፡ .እንደሚታወቀዉ በሙዚቃ ዉስጥ ከፍተኛ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በሙዚቃ ዉስጥ የተለያዩ ዘፈኖችና መዝሙሮች ተዉበዉና ተቀናጅተዉ የሰዉን ስሜት የሚስቡና ተነሳሽነት በሰዉ ዉስጥ የሚፈጥሩ ለሁላቸዉም መሰረታዊ መመዘኛዉ ሶልፌጅዮ በዉስጡ ያካተተ መሆኑ ነዉ፡፡

የኖታዎች የቆይታ ጊዜ ምሳሌዎች ከታች የተዘረዘሩትን ተመልከት፡፡



1 2 3 4 1 2 3 4 1 2 3 4

## 2.ኖታዎችን ማንበብና ምታቸዉን መለማመድ

ኖታዎችን ስናነብ ወይም ስንለማመድ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እንለማመዳለን፡፡የተለያዩ ኖታዎችና እረፍቶች እንዳሉ የተለያዩ

ምቶች አሏቸዉ፡፡ስለዝህ ኖታዎች ድምጽ ያሏቸዉ ስሆኑ የተለያዩ እረፍቶች ደግሞ የተለያዩ የቆይታ ጊዜ አሏቸዉ፡፡


ስለዝህ ኖታዎችና ዕረፍቶች እንደ ቆይታ ጊዜያቸዉ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ እናነባቸዋለን፡፡ኖታዎችን ስናንብ ወይም ስንለማመድ በእጃችን ጠረጴዛን በመምታት ወይም በእግራችን መሬትን በመምታት የምት ሂደት ቋሚ ፍጥነት እንለማመዳለን፡፡

**ድርጊት** 8 1. ከዚህ ሥር የተፃፉትን የኖታ ምቶች ከዝህ በፊት እንደተማራችሁ እርስ በርስ በማሰታወስ ለማነበብ


ሞክር /ሪ፡፡

**ድምጽ ያላቸዉ ኖታዎችን መለማመድ**


1.





2.ኖታዎች ነጥብ ከጎነናቸዉ ስኖር ደግሞ ባላቸዉ ዋጋ ላይ ግማሽ ዋጋ በመጨመር ይነበባሉ፡፡





.



**ማሳሰቢያ፡**ከላይና ታች ያለዉ መስመር የኖታዉ አካል ሳይሆን ማንበብ እስከሚችሉ ድረስ የቆይታ ጊዜያቸዉን ለመለካት እንዲቀል ብቻ ነዉ፡፡

3.ዕረፍቶች ወይም ድምጽ የሌላቸዉ በአፋችን ዝም በማለት ዋጋቸዉን በመለካት ማንበብ አስታዉስ፡፡









I.እጅህን በማምታት ወይም ጠረጴዛን በመምታት "ታ"ወይም "ላ"በማለት ከዚህ በታች ያሉትን ምቶች ተለማመድ፡፡


1.




2.




3.







ምሳሌ 2

1.





2.



3.






3.

4. II.ከዚህ በታች ያላቸዉ ኖታዎች ግንኙነት ተመልከት/ቺ


1.




2.





3.




4.




5.




6.



7.




8.




### III.ኖታዎችና ዕረፍቶችን በማደባለቅ ለማንበብ ተለማመድ/ጂ


1.




2.




3.




4.





5.




6.



7.



8.



10.



## 2.2.2. የኢትዮጲያ ቅኝት

የሀገራችን ሙዚቃ እስኬሉ ፔንታቶኒክ በመባል ይታወቃል፡፡ፔንታቶኒክ ከ ግሪክ ቋንቋ የመጣ ሲሆን ፔንታ ማለት በግሪክ ቋንቋ አምስት ማለት ስሆን ቶኒክ ማለት ደግሞ ሙሉ ድምጽ ማለት ነዉ፡፡ፐንታቶኒክ የሀገራችን ሙዚቃ ቅኝቱ በአንድ ኦክታቭ ዉስጥ አምስት ድምጽ ያለዉ ነዉ፡፡

**የሀገራችን ሙዚቃ የድምጽ ቅኝት ሁኔታ**

ቅኝት ማለት የድምጽ አወቃቀር ከወፍራም ወደ ቀጭን ወይም ከቀጭን ወደ ወፍራም ሕጋዊ በሆነ መልክ በተከታታይ የተስተካከለ ማለት ነዉ፡፡

ከሀገራችን ቅኝቶች ከተወሰኑት ዉሰጥ ጥቂቶቹ ከዚህ በታች

1.ትዝታ

2.ባቲ


### ሀ. የትዝታ ቅኝት

የትዝታ ቅኝት ሜጀርና ማይነር ማነር በመባል በሁለት ቦታ ይከፈላል፡፡ የትዝታ ሜጀር አወቃቀር ከሰባቱ የዓለም የሙዚቃ ድምጾች ላይ በመነሳት አራተኛ እና ሰባተኛ ድምጾችን በማዉጣት በቀሩት በአምስት

ድምጾች እንጫወታለን፡፡እንዲሁም ትዝታ ማይነርን ደግሞ በተጨማሪ ሶስተኛና ስድስተኛ ድምጾችን በግማሽ ድምጽ ወደ ኋ ላ በማስመለስ እንጫወታለን፡፡

ለምሳሌ፣ ትዝታ ሜጀር C D E G A C


ይሄንን ከዝህ በታች ባለዉ ፒያኖ ወይም ትንሽ ኪቦርድ ላይ ድምጹን ተለማመድ/ጂ




የትዝታ ሜጀር አወቃቀር ከዝህ በታች ባለዉ ሁኔታ ይመስላል፡፡

c d $e^b$ g $a^b$ c

ይሄንን ከዝህ በታች ባለዉ የሙዚቃ መሳሪያ ላይ ድምጻቸዉን ተለማመድ፡፡




## የትዝታ ማይነር ልምምድ

- ከዝህ ስር የተጻፈዉን ዜማ ከአስተማሪዎቻችሁ ጋር በማዜም ተለማመዱ፡፡
- ☞ በትዝታ ሜጀር ላይ ያተኮረ እንደ ከዝህ በታች ተጽፎ ባለዉ በትንሽ ኪቦርድ ላ ተለማምዱ፡፡

1.




2.










## ለ. የባቲ ቅኝት

የባቲ ቅኝትን እንደ ትዝታ ባቲ ሜጀርና ማይነር ብለን በሁለት ቦታ እንከፍላለን፡፡የባቲ ሜጀር ስንመሰርት ከሰባቱ የሙዚቃ ድምጾች ዉስጥ ሁለተኛና ስድስተኛ ድምጽ እንመሰርታለን፡፡ባቲ ማይነርን ስንጫወት ሶስተኛና ሰባተኛ ድምጽን በግማሽ ድምጽ በመቀነስ እንጫወታለን፡፡


ለምሳሌ፣1.ባቲ ሜጀር C E F G B C

እርሱንም ከዝህ በታች እንደተገለጸዉ በኪቦርድ ላይ ተለማመድ/ጂ፡፡




ምሳሌ 2. D $F^{\#}$ G A $C^{\#}$ D

ምሳሌ 3.c $e^b$ f $g^b$ c




ምሳሌ 4.e $g^b$ b a b $d^b$ e

**የባቲ ልምምድ**

**በባቲ ማይነር ላይ ያተኮረ ከዝህ በታች እንደተገለጸዉ በሙዚቃ መሳሪያ በመታገዝ ተለማመድ፡፡**




2.



**ድርጊት 9፡**ከዝህ በታች ፊደላትን መነሻ በማድረግ C ና G ክሌፍ ላይ የትዝታና ባቲ ሜጀርና ማይነር መስርት/ቺ፡፡

1. A
2. $A^b$
3. G
4. F
5. $B^b$

## 2.3.ባህላዊ ዉዝዋዜ

**ድርጊት** 10. ሀ. ባህላዊ ዉዝዋዜ በምን ዓይነት ሁኔታ ይከናወናል?

ለ. በአከባቢያችዉ ባህላዊ ዉዝዋዜ መቼ መቼ ነዉ የሚካሄደዉ?

በስነ-ተግባር ዉስጥ ዉዝዋዜ የሰዉ እንቅስቃሴና ምት ላይ በመመስረት ተመልካቾችን ለማዝናናት የሚገለግል ሆኖ ለማህበረሰብ ጉዳይና ባህል የሚገልጽ እንድሁም የአርቲስት ስበትና የራሱ የሆነ ስነ-ስርዓት ያለዉ ነዉ፡፡ ከዝህም ዉጪ ዉዝዋዜ ከግል እንቅስቃሴ እስከ ቡድን በመሆን ማሳየትን ይጨምራል፡፡ በተጨማሪም ዉዝዋዝ የሚሰራዉ ተመልካቾች በሌሉበት ግዜ በራሳቸዉ በማዝናናት እና ተሳትፎ ለማድረግ እንድሁም ተመልካቾች ባሉበት በማሳየት ለማዝናናት ስራ ላይ ይዉላል፡፡

### ዉዝዋዜና የሰዉነት ቁመና

ዉዝዋዜ በምንወዛወዝበት ጊዜ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠዉ የእንቅስቃሴ አቅጣጫ የሚስብ አካል የሚካሄድበት ነዉ፡፡ይህ ማለት የሰዉነት አካል ወይም ሙሉ ወይም በአንድ ጎን በማዞር፣በማጠፍ፣በመዘርጋት፣መዝለል እና መገልበጥን ያካትታል፡፡እነኝህን በማቀናጀት የእነቅስቃሴ ሁኔታበመቀየርና በመድገም ከምት ጋር ሰዉን በሚስብ መልክ እና ሰዉን ማዝናናት የሚችሉ ዉዝዋዜ ይወዛወዛል፡፡

በዚህ መልክ ዉዝዋዜ በተደጋጋሚ የሚታዉ በሌላ ቦታ የሚወዛወዘዉ ላይ ልዩነት በመኖር ባህል ሆኖ አንድን ብሄር ከሌላዉ ልዩ የደርጋል ማለት ነዉ፡፡ለምሳሌ፣የሸዋን ዉዝዋዜ ወስደን ብናየዉ የክንዉኑ ሁኔታ ደግሞ ወጣት ወንዶችና ሴቶች በተራ ሰልፍ ይዘዉ የሴቶች ቡድን እግር፣ጡትና አንገት በማስማማት እያንቀሳቀሱ እጃቸቸዉን ደግሞ ወገብ

ላይ በማድረግ በፍጥነት በሚወዛወዙበት የወጣቶች ቡድን ደግሞ እግር፣ እጅና አንገታቸዉን በማስማማት ይወዛወዛሉ፡፡

በዉዝዋዜ ዉስጥ የሚደረገዉ የአካል እንቅስቃሴ በመደጋገም ለረዥም ጊዜ ልምምድ በማድረግ በይበልጥ እንዲጎለበትና እንዲሰፋ በማድረግ ይቻላል፡፡

## ዉዝዋዜ በማህበረሰብ ዉስጥ  ያለዉ ጥቅም

ማንኛዉም ማህበረሰብ ልዩ የሆነ የራሱ ዉዝዋዜ አለዉ፡፡ህዝብን በማገናኘትና በማያያዝ ዉስጥ ዉዝዋዜ መንገድ በመሆን የሚሰጠዉ ጥቅም በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡

ከዉዝዉዜ ጥቅም ዉስጥ ጥቂቶቹ፡-

-የህብረተሰብን ግንኙነትና አንድነትን ለማጠናከር

-የመረዳዳትን ስሜት በማህብረብ ዉስጥ መፍጠርና ማሳደግ

-የአንድን ብሔር ለማቆየትና ማንከባከብ

-ህይማኖት፣አመለካከትን፣ህግና የአንድን ማህበረሰብ እሴት ለመግለፅ

በተጨማሪም ዉዝዋዜ በሚወዘወዝበት ጊዜ እያንዳንዱ የሰዉነት ክፍል እንቅስቃሴ ስለሚያደርግ የሰዉነትን ጤንነት ጥንካሬ ለመጨመር ትልቅ ሚና ጫወታል፡፡

## 2.4.የስነ-ትያትርና ስነ-ፊልም ሃሳብ መፃፍ

**የመማር ብቃት ቢያንስ ተማሪዎች መጎናጸፍ ያለባቸዉ**

**በዚህ የትምህርት ርዕስ መጨረሻ ላይ፡**

-የስነ-ትያትርና ስነ-ፊልም ሃሳብ መፃፍ ምን ማለት እንደሆነ ትገልፃለህ/ሽ፡፡

-ጥሩ የተዉኔት ፅሁፍ ዘዴ ለመጻፍ የሚረዱ ትለያለህ/ሽ፡፡

-አንድ ጽሁፍ በምን ዉስጥ ማለፍ ያለበትን ቅደም ተከተል ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡

**ድርጊት11**

1.የስነ-ትያትርና የስነ-ፊልም የሚሆን ሃሳብ አንድ ጸሐፊ ወይም ደራሲ ከየት ያገኛል ብለህ ታስባለህ/ሽ?ከጓደኞችህ/ሽ ጋር ተወያይተህ/ሽ ለእርስ በርሳችሁ ግለጹ፡፡

2.አንድ መመዘኛዉ ሙሉ የሆነ የተዉኔት ጽሁፍ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

መጻፍ ማለት አንድ በአእምሮአችን ዉሰጥ የተፈጠረዉን በጽሑፍ መግለጽ ማለት ነዉ፡፡ይህ ማለት ሃሳቡን ትርጉም በጽሁፍ መልክ መግለጽ ማለት ነዉ፡፡አንድን ነገር በሚንጽፍበት ጊዜ ጽሁፋችን ከዝህ በታች ባሉት ቅደም ተከተል ዉስጥማለፍ አለበት፡፡

-ከመጻፍ በፊት

-ተርታ ማስያዝ

-በድጋሚ መጻፍ

-ማሰተካከል

-ማተም

የተዉኔት ጽሁፍን መጻፍ ስንጀምር ከዝህ በታች ያሉትን ማወቅ አለብን፡፡

-ከየት ወደ የት ይሄዳል?

-ከማን ጋር መሰራት አለበት?

-በምን ያህል ፍጥነት መሰራት አለበት?

-ምን ልሆን ነዉ?

-የተዉኔት ጽሁፍን ለመጻፍ ሃሳብን ከየት እናገኛለ?

በስነ-ትያትርና ስነ-ፊልም ፕሮዳክሽን ስራ ዉስጥ የተዉኔት ጽሁፍ ሃሳብ መጻፍ ዋናዉ ነዉ፡፡ከትያትር አካላት ዉስጥ በጣም አስፈላጊና ወደ ተግባር የሚቀይረዉ ሆኖ ተዉኔት ለመገኘት የግድ መቅረብ ያለበት ጽሁፍ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል የዝህ ጽሁፍ ስም የተዉኔት ጽሁፍ ይባላል፡፡የተዉኔት ጽሁፍ ቁልፍ ትትርም ቢሆን ፊልም ሌላኛዉ ተቃራኒነት ነዉ፡፡ተዋንያን ሊደርሱ የሚፈልጉትን ግብ መኖር አለባቸዉ፡፡ግን ያለሙትን ግብ ሃሳብ ለመድረስ ተቃራኒነቱ በብዙ ክርክር የበዛበት ዉስጥ ማለፍ የግድ ይላል፡፡ተቃራኒነት ከዉስጡ ከለለበት ታሪኩ የማይጥምና አሰልቺ ይሆናል፡፡

የስነ-ፊልምም ሆነ የስ-ትያትር መሰረታዊ ታሪክ እንደ ዘገባ፣መጽሀፍ፣ገጠመኝ፣ ከፊልም፣ከትያትር ቤት፣ከአነጋገር፣ሰዎች ከሚጣሉበት ነገር፣ከተለያዩ ስዕሎች፣ ከግለሰብ ሰዉ፣ከተለያዩ ሙዚቃ፣ሰዎች ከሚጫወቱት ጭዉዉት፣በአንድ አከባቢ ከሚኖሩ ህብረተሰቦች የኑሮ ሁኔታ፣የአንድ ሰዉና ህብረተሰብ ኑሮ ሁኔታ እና ከመሳሰሉት ይገኛል፡፡

የስነ-ፊልም የተዉኔት ጽሁፍ ትኩረቱ ካሜራ ላይ ሲሆን የትያትር ትኩረት ደግሞ መድረክ ነዉ፡፡ይህ ማለት የስነ-ፍልም ተዉኔት ጽሁፍ ለካሜራ ቀረጻ እንዲመች ተደርጎ ይጻፋል፡፡የስነ-ትያትር ደግሞ እንደ ትያትር መድረክ የሚመች ሆኖ ይጻፋል፡፡

## 2.4.1. ጥሩ የተዉኔት ጽሁፍ ለመጻፍ የሚረዱን ዘዴዎች

ጥሩ የተዉኔት ጽሁፍን ስናነብ የመጀመሪያዉ ገጽና ሃሳብ ማወቅ ይቻላል፡፡እንደተዉ ቃላቶች ተቀናጅተዉ በወረቀት ገጽ ተጽፈዉ ታሪኩ የተቀናጀዉ ሁኔታ፣የተዋንያን ታሪክ ጥንካሬ፣በድራማዉ ጥንካሬ ጥሩ የተዉኔት ጽሁፍ ለመጻፍ የሚረዱን ናቸዉ፡፡

1.ዋና ሃሳብ ትልቅ ሃሳብ ማለት ምን ማለት ነዉ? ትልቅ ሃሳብ ማለት ዋና የምንጽፈዉ ሃሳብ ማለት

ነዉ፡፡የሚንጽፈዉ ዋና ሃሳብ ለማግኘት የሚንጽፈዉን በማህበረሰብ ዉስጥ በመግባት ጥናት ማድረግ ነዉ፡፡

2. ሃሳብን ማስፋፋት

3.መጫወት(ባለዉ ጨዋታ ዉስጥ መሳተፍ)

4.የራስን አከባቢ ዓለም ማየት

5.ከሰዎች ጋር ጥያቄና መልስ ማድረግ

በተለይ ጥሩ የበሰለ ቃለ-ምልልስ ለማግኘት የሚናደርገዉ የጥያቄና መልስ ዘዴ ከፍተኛ ቦታ ይኖረዋል፡፡ከዝህ በታች ያለዉን ምሳሌ አስተዉል፡፡ እንዲሁም አንድን የተዉኔት ጽሁፍ ሃሳብ የተዉኔቱ ጅማሬ አካሂድ በህጉ እንድጀመር ከዝህ በታች ባለዉ ምሳሌ መረዳት ይቻላል፡፡

## አፈፃፀም አንድ

## አንደኛ ምልከታ

ቦታዉ ትምህርት ቤት ዉስጥ የተማሪዎችእረፍት ጊዜ ነዉ፡፡ሊበን እና ለልሳ በጥላ ስር ይታያሉ፡፡

**ሊበን፡**ማን ነህ አንተ?

**ለሊሳ፡**ማወቅ ለምን አስፈለገህ?

**ሊበን፡**ማወቅ ፈልጌ ነዉ

**ለሊሳ፡**እኔን ማሰር አትችልም፡፡ይህንን ለማድረግ ነዉ አይደል?

**ሊበን፡**ለምን እርሱን አደርጋለሁ?

**ለሊሳ፡**እኔ ብቻዉን መንገድ ላይ የሚኖር ሰዉ ነኝ፡፡ብታደርግም አይቸግረኝም፡፡

**ሊበን፡**ለምን መንገድ ላይ ትኖራለህ?

**ለሊሳ፡**ከዝህ በላይ የማዉቀዉ ነገር የለኝም፡፡ራሴን አጥቼ ራሴን መፈለግ በመንገድ ወጣሁ መሰለኝ ሳስብ፡፡

**ሊበን፡**ስለ ምን?

**ለሊሳ፡** ስራ ማግኘትና ማጣት ያ አባቴ ያለዉ ነገር፡፡

**ሊበን፡** አባትህ ከቤት አባረረህ?

**ለሊሳ፡** ወደ ትምህርትና ስራ እንዲመለስ ይፈልጋሉ፡፡

**ሊበን፡**እድሜህ ስንት ነዉ?

**ለሊሳ፡** አስራ ስድስት፡፡ ብያንስ እድሜህ በቂ ነዉ አባቴ እንደሚለዉ፡፡

**ሊበን፡** እርሱ ለምን ያንን ለማለት ፈለገ?

ይሄንን ቃለ-ምልልስ አስተዉል

ተዉኔት መጻፍ የራሱ ህግ እንዳለዉ እና ዕንዴት እንደሚጻፍ በመከተል ፊልምም የራሱ የሆነ ህግና ፎርማት አለዉ፡፡ምክኒያቱም ፊልም በካሜራ ዓይን ትልቅ ትኩረት ስለሚሰጥ የቀረጻዉ ስራ ከካሜራ ጋር እየተስማማ ይሄዳል፡፡

ስለዝህ ለፊልም ሃሳብ መጻፍ ዉስጥ የፊልም ሃሳብ እንደ ተዉኔት መጻፍ በአዕምሮዉ የፈጠራ ችሎታን በመጠቀም አዉጥቶ አዉርዶ በጽሑፍ ዓለም ዉስጥ ለማሰተላለፍ የፈለገዉን የፊልም መልዕክት ወደ ፊልም ቀይሮ በመፃፍ ሃሳቡን ይገልጻል፡፡በዚህ ሂደት ዉስጥ ፊልም መጻፍ ከዚህ በታች በቀረበዉ ፎርማትን በመከተል ይጻፋል፡፡

ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረበዉ ምሳሌ እንዴት የፊልም ጽሁፍ እንደሚፃፍና የፊልም ሃሳብ ምን እንደሆነ ይገልጻል፡፡

**የምስል መጥራት እና የድምጽ እየጎላ መሄድ /Fade In**

**ዉስጥ-ክፍል-ቧት**

*ቦታዉ አባ ቶላና ሀዳ ቤት ነዉ፡፡አባ ቶላ ከ ሃዳ ቶላ ጋር ይነጋገራል፡*
*፡*

**አባ ቶላ**

ያ ልጅ ቤትን ትቶ ሄዴ አሉ አይደል?እዚያ ገባ የሚል አልተሰማም?

**ሃዳ ቶላ**

ምን ይሰማል ብለዎት ነዉ፣ምንም የተሰማ ነገር የለም፡፡

**አባ ቶላ**

ጥላዉ ራሱ መድሃኒት ነበር፡፡የእርሷ ማቃጠል ከቤት አወጣ፡፡

**ሃዳ ቶላ**

ተቃጥያለዉ አባ ቶላኮ! ዛሬ መድረሱ ራሱ...*(ያዳሺ ትገባለች)*

**ያዳሺ**

ልጆች ቤቶች!

**ሃዳ ቶላ**

ማነዉ?ግቡ!ያዳሺ አንቺ ነሽ ለካ? ጊቢ ወደ ዉሰጥ!

**አባ ቶላ**

እኛ ስላንቺ ስናወራ መጣሽ...ጊቢ ወደ ዉሰጥ!

**ያዳሺ**

ስለ እኔ ታወራላችሁ ማለት ነዉ?

**ሃዳ ቶላ**

አዎ!ይህ ሽማግሌ ስምሽን ሁሌ ያነሳል፡፡

**አባ ቶላ**

መልካምም ብሆን፣ክፉም ብሆን በህይወት ያለዉ እንዴት ማዉራት ይቀራል?ይህ ልጅ ሆዱን ቆርጦ ካንቺ ተለየ?እዚያ ገባ የሚል የሰማሽዉ የለሽም?

**ያዳሺ**

አደራ ስሙን አታንሱብኝ፣እዚያ ገባ የሚባለዉ አይሰማ፣ምን በደለኝ?

**አባ ቶላ**

ኤረ ተይ! ጥላዉ ራሱ መድሐኒት ነበር..

**ያዳሺ**

**እርሱ ምን ጥላ አለዉ?ከእርሱ ጋር መኖር እሳት ነዉ፡፡ይሄዉ እርሱ ከሄዴ በኋላ ከችግሬ በቀር እንደ እርሱ የሚያቃጥለኝ የለም፡፡ እስቲ ተነስቼ ልግባ…በሰላም ዋሉ!**

*(ትወጣለች፡፡ሃዳ ቶላ እርሷን ለመሸኘት ትወጣለች፡፡ከአባ ቶላ ራቅ ብለዉ ድምጻቸዉን ዝቅ በማድረግ ከእርሷ ጋር ያወራሉ፡፡)*

**ያዳሺ**

**እነማ አባ ቶላን ፈርቼ እንጂ የሆነ ነገርን ተቸግሬ ነዉ ሃዳ ቶላኮ!**

**ሃዳ ቶላ**

**ምን ተቸገርሽ ታዲያ? ምን ላግዝሽ?***(በርህሩህነት ስሜት)*

# የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

- የቀለም አቀባብ ማለት ለቀለም በሌሎች ነገሮች በመታገዝ ጠጠራማ ገጽታ ባላቸዉ ላይ ስዕል፣ዲዛይንና ሙያ ዉበት የሚሰማበት ነዉ፡፡
- በቀለም አቀባብ ስራ ዉስጥ ቀለም ዋናዉና ምትክ የሌለዉ ነዉ፡፡
- ቶን/ቫልዉ የቀለም ብርሃማነትና ደብዛዛማነት ነዉ፡፡
- በአከባቢያችን ያሉ ቀለሞች/መልኮች በዐይናችን አይተን ስም ጠርተን የምንለያቸዉ ለዐይናችነ እንድታይ የሚደርገዉ የፀሐይ ብርሃነ ነዉ፡፡
- ይህ እስፔክትረም እንደ ቀስተ-ደመና ቀለማት ሰባት የተለያየ መልክ በዉስጡ ይይዛል፡፡እነርሱም ስማቸዉ “VIBGYOR” በመባል ይታወቃሉ፡፡
- እኝህም ቀለማት ከቀይ ወደ ወይን ጠጅ በሚሄዱበት ጊዜ ሞገዳቸዉ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡
- የአንድ ነገር ባህርይ በግሉ ሞገዶችን ከዉስጡ ሰምጦ ሲያስቀር ሌላን ደግሞ በማንጸባረቅ ያሳያል፡፡
- ሶልፌጅዮ ትርጉሙ የጆሮ ማዳመጫ ችሎታ ሳይንስ ሆኖ ጆሮአችን እንዴት ምቱን ጠብቆ እንደሚጫወት የሚያጎለብትና የሚስረዳ ትምህርት ነዉ፡፡
- የሶልፊጅዮ ሚና/ድርሻ በሙዚቃ ሳይንስ ዉስጥ ያለዉ ለሙዚቃ ችሎታ ትልቅ ድርሻ አለዉ፡፡
- ቅኝት ስንል የድምጾች አደረጃጀት ከወፍራም ወደ ቀጭን ወይም ከቀጭን ወደ ወፍራም የተደረደሩ ማለት ነዉ፡፡

- መጻፍ ማለት የትርጉሙን መጀመሪያ በመጠቀም መግለጽ ማለት ነዉ፡፡
- በስነ-ትያትርና ስነ-ፊልም ማምረቻ ስራ ዉስጥ የተዉኔት ሃሳብ መጻፍ ዋና ነገር ነዉ፡፡
- የስነ-ፊልም ተዉኔት ትኩረቱ ካሜራ ላይ ሲሆን የስነ- ትያትር ደግሞ መድረክ ላይ ነዉ፡፡

## የምዕራፍ ሁለት መልመጃ

### I. ከዚህ በታች ባሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነዉን እዉነት ትክክል ያልሆነዉን ደግሞ ሃሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

1. ለጥላ/ዣንጥላ መፈጠር ምክኒያት የሆነ የብርሃነ ጨረር ተጠማዞ አለማለፍ ነዉ፡፡
2. የብርሃነ ጨረር ሁልጊዜ ከምንጬ ተነስቶ ሲሄድ እኩል በሆነ ፍጥነት ይሄዳል፡፡
3. ረጅም/ትልቅ ሞገድ ያላቸዉ ቀለማት ነገሮችን ትናንሽ ሆነዉ እንዲታዩ ያደርጋል፡፡
4. ሲር አሳክ ኒዉቶን ብርሃን የሁሉ ቀለማት ምንጭ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
5. ብርሃን የቀለማት ሁሉ ምንጭ ነዉ፡፡
6. ተቃራኒ ቀለማት ገጽ ለገጽ ያሉትን ካቀላቀልን ዉብ የሆነ ቀለም ይሰጡናል፡፡
7. ቀዝቃዛ የሆኑ ቀለማት በእጃችን ስንነከካ የሚቀዘቅዙብን ወይም የሚበርዱብን ማለት ነዉ፡፡
8. የባቲ ቅኝት ስንሰራ 3ኛና 6ኛን ድምጽ እናወጣለን፡፡

9. ሙዚቃ በመጫወት ዉስጥ ሶልፌጂዮ ትልቁ የጀርባ አጥንት ነዉ፡፡

10..ባቲ ማይነር በኦሮሚያ ክልል ዉስጥ በአብዛኛዉ እንጠቀምበታለን፡፡

11.ዉዝዋዜን ለማሳየት የባህል ልብስ ብቻ ያስፈልገናል፡፡

12.መጻፍ ማለት ስነ-ትያትር በማቀናጀት ማቅረብ ማለት ነዉ፡፡

13.ጥሩ ተዉኔት ተዉኔቱ በዚያ ጊዜ ስናነብ ማወቅ እንችላለ፡፡

14.የስነ-ትያትር ተዉኔት ትኩረቱ ካሜራ ላይ ነዉ፡፡

15.ተዉኔትን በሚንጽፍበጽ ጊዜ ዉስጥ ማስተካከል የመጀመሪያ ስራ ነዉ፡፡

## II. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ

1. በድሮ ዘመን ዋሻ ላይ ያልተሰራበት ቀለም የትኛዉ ነዉ?

   ሀ. ቀይ ለ.ቢጫ ሐ.አረንጓዴ መ.ጥቁር

2. በድሮ ዓመት የቀለም አቀባብ ስእሎች ዉስጥ በይበልጥ በዋሻ ላይ እየተሰራ

   የነበረ የየትኛዉ ቀለም አቀባብ ስእል ነዉ፡፡

   ሀ. ፈረስ ለ.አንበሳ ሐ.ጎሽ መ.ሁሉም መልስ ናቸዉ

3.ቀለም አቀባብን ስራ ለመስራት የሚዉል የትኛዉ ነዉ?

   ሀ. መቀቢያ/ብሩሽ ለ.ቢላዋ ሐ..ስፖንጅ መ.ሁሉም መልስ ናቸዉ

4. በቀለም አቀባብ ስራ ዉስጥ ወሳኝ አካልና መተኪያ የሌለዉ የትኛዉ ነዉ?

   ሀ.መስመር ለ.ቀለም ሐ.ቅርጽ መ.ቦታ

5. ከዚህ በታች ባሉት ዉስጥ ብርሃንን ከዉስጡ የሚያሳልፍ እንደ ፕሪዝም የሚገለግዉ የቱ ነዉ?

6. ቀስተ-ደመና ስንት ቀለሞች አሉት? ሀ.5 ለ.3 ሐ.7 መ.9

7. በአከባቢያች የሚታዩብን ቀለማት ለማየት ከዚህ በታች ባሉት ወሳኝ ያልሆነ የትኛዉ ነዉ?

   ሀ. ብርሃን ለ.ገጽታ ሐ.ዐይን መ.መልስ አለተሰጠም

8. ሰዉ-ሰራሽ የሆኑትን ቀለማት ለማዘጋጀት የማያገለግል የትኛዉ ነዉ፡፡

   ሀ.ቅጠል ለ.ከሰል ሐ.አፈር መ.መልስ አልተሰጠም.

9. ከዚህ በታች ባሉት ዉስጥ ሞቃታማ ቀለም ያልሆነ የቱ ነዉ?

ሀ. ሰማያዊ ለ.ቀይ ሐ.ብርቱካን መ.ቀይ-ብርቱካን

10. ከዚህ በታች ያሉትን ስንደመር ዉጤታቸዉ ን ምረጥ/ጪ



11.ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ዉስጥ ባቲ ሜጀር የትኛዉ ነዉ?

ሀ. A B $C^{\#}$E $F^{\#}$ A

ለ.F A $B^{b}$C E F

ሐ. F $A^{b}$ $B^{b}$C $E^{b}$ F

መ. $E^{b}$ F $A^{b}B^{b}$ $C^{b}$ $E^{b}$

12. C,D, E, G, A, C የተጻፈዉ የሙዚቃ ቅኝት ምን ይባላል?

ሀ. C ባቲ ማይነር ለ. C ባቲ ሐ. C ማይነር

መ. C ትዝታ ሜጀር

13. C, $E^{b}$, F, G, $B^{b}$, C የተጻፈዉ የሙዚቃ ቅኝት ምን ይባላል?

ሀ. C ባቲ ሜጀር ለ. C ትዝታ ማይነር

ሐ. C ባቲ ማይነር መ. C ትዝታ ሜጀር

14. ለስነ-ትያትርና ስነ-ፊልም መሰረተ ሃሳብ የሚሆነዉ ከየት ይገኛል?

ሀ. ከዘገባው ለ. ከተሌ ገጠመኞች

ሐ. ከተለያዩ መጽሐፍ መ.ሁሉም

15. ከዚህ በታች ካሉት ዉስጥ ጥሩ የተዉኔት ዘዴ መጻፍ ያልሆነ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ተራ ማስያዝ ለ.ዋና ሃሳብ ሐ.ሃሳብ ማስፋፋት መ.ሁሉም

## III.ትክክለኛ መልስ የሆነዉን ሰርተህ አሳይ/ዪ

ሀ. የዉሃ ወይም የዘይት ቀለም አቀባብ ቀለም ማግኘት የሚትችሉትን በመጠቀም ተለያዩ ስእሎችን በመሳል ኣሳዩ፡፡

ለ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሙዝቃ ድምጾች መነሻ በማድረግ ትዝታ ሜጀርና ማይነርን ሰርተህ ኣሳይ/ዪ

ሀ. D

ለ. $E^b$

ሐ. E

ሐ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሙዝቃ ድምጾች መነሻ በማድረግ ባቲ ሜጀርና ማይነርን ሰርተህ ኣሳይ/ዪ

ሀ. G

ለ. A

ሐ. $A^b$

# ምዕራፍ 3

# የታሪክ እና የባህል ነባራዊ ሁኔታ

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤት፤**

**በዚህ ትምህርት ምዕራፍ መጨረሻ ላይ፤**

- የኦሮሞ ሙዚቃ ታሪክ ትርጉም እና ጥቅም ትረዳለህ/ሽ::
- የኦሮሞ ብሄር ዘፋኞች እና ተወዛዋገሮች ታዉቃለህ/ሽ፡፡
  - ✓ የቀለም አቀባብ ሙያ ምንነት እና ሃገር በቀል ፅሑፍ ታደንቃላችሁ፡፡
  - ✓ የቀለም ቅብ አሰራር እን መልእክቶችን ታውቃላችሁ፡፡
  - ✓ ሃገር በቀል እውቀት በስነ-ትያትር እና ስነ ፊልም ታሳያላችሁ፡፡

## መግቢያ

በሁለተኛ ምዕራፍ የምት አካሄድ፣ ትዝታ እና ባቲ ቅኝት በሙዚቃ መማር ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የአንጋፋ ዘፋኞች እና ተወዛዋገሮች ታሪክ ትማራላችሁ፡፡

በጥንት ዘመን ሰዎች ቀለም በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች በመጭመቅ ወይም በማድቀቅ እያዘጋጁ፤ ለረዥም አመታት እየተገለገሉበት ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- በቀለም ቤታቸውን በማሳመር እና የቀለም አቀባብ ስራዎችን እየሰሩበት ነበር፡፡

ማንኛውም ብሄር ከሌላ ብሄር የሚለየዉ የራሱ የሆነ የሙያ ባሕል አላቸዉ፡፡ ይህ ማለት በእውቀቱ እና በችሎታው የእለት ተእለት ኑሮ የሚያካሄድበት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የአንድ ብሄረሰብ ሃገር በቀል እውቀት ይባላል፡፡ በዚህ ርዕስ የኦሮሞ ህዝብ ዋና እውቀት የምትማሩ እና ክንውን /አፈጻጸም/ ሁኔታ በስነ-ትያትር የምተዩ ይሆናል፡፡

## 3.1 የኦሮሞ ዘፋኞች እና ተወዛዋዦች የሙዚቃ ታሪክ

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት፡

ከዚህ የትምህርት ርዕስ በኋላ፡

- ✓ የኦሮሞ ዘፋኞች ታሪክ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ታዋቂ የኦሮሞ ዘፋኞች እና ተወዛዋዦች የሆኑትን ትዘረዝራላችሁ፡፡

**ድርጊት**

ሀ. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታዋቂ ዘፋኞች እና ተወዛዋዦች አሉ?

ለ. የምታውቋቸውን ታዋቂ የሆኑ የኦሮሞ ዘፋኞችን ዘርዝሩ?

ሐ. ከነዚህ ዘፋኞች ሙዚቃ ውስጥ በመውሰድ በተግባር አሳዩ?

ኢትዮጵያ የረዥም አመት ታሪክ በለቤት የሆነች ሃገር ሲትሆን፣ የብሄር ብሄረሰቦቿ ታሪክ እና ባህል፣ሙዚቃ ያላቸው ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ የፖላቲዊ ፣ማህበረሰብዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር በአንድ ወገን የበላይነት ለረጅም ዓመታት ስለነበር ከዚህም የተነሳ ታሪክ እና እውነተኛ ሁኔታዎችን ለትውልድ ተጨባጭ እና ታማኝ የሆነ መረጃ ባለማስቀመጣቸዉ ብዙ ዋቢ/ማስረጃ የሆኑ/ መፅሐፍቶች የሉም፡፡ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ብሄርብሄረሰቦች እንደ ፍላጎታቸው እና ባህሪያቸው በተለያዩ ግዜ በአስተዳደር ስርዓት፣

ማህበረሰብአዊ እና ባህላቸውን ለማበልጸግ ሙዚቃ በተለያየ ሁኔታ እየተጠቀሙ እንደ ነበር ይነገራል፡፡

የኦሮሞ ሙዚቃ ታሪክ ከሌሎች ብሄር ዘፋኞች እና ተወዛዋዦች የተለየ አይደለም፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ሰፊ፣ባህል ያለው እና የተለያዩ የአስተዳደር ስርዓቶች አልፈዉ እዚህ የደረሰ ነው፡፡ የሙዚቃው ታሪክ ከባህሉ ጋር የተያያዘ ሆኖ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ እዚህ ደረሷል፡፡ ሙዚቃን መፍጠር፣ማሳደግ እና መንከባከብ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ውስጥ የዘፋኞች እና የተወዛዋዦች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ዘፋኞች የህዝብ ድምፅ ከመሆን አልፎ ህዝብ እንዲቀሰቅስ፣ባህሉን እንዲያጠናክር፣ልማድን እነዲያጠናክር እና ታሪኩን እንዲያስታውስ ይሰራሉ፡፡ የኦሮሞ ዘፋኞች እና ተወዛዋዦች የህዝብ ነቀፋ እና ቅሬታ በማነሳሳት አስመስለው በብሔረሰቡ በማድረስ ውስጥ ዋልታ እና ሀይል ሆነው እንደነበሩ ከታሪካቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ዘፋኞች እና ተወዛዋዦች በኦሮሞ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸውን ጥቂቶቹን እንያቸው፡-

## ድምጻዊ ወሰኑ ዲዶ

በዘመናዊ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ከነበሩት የኦሮሞ ድምጻውያን አንዱ ወሰኑ ዲዶ ነው፡፡ ይህ ድምጻዊ ከ1930 ዓ.ም. ጀምሮ ዘፋኞችን ማሲንቆን እየተጠቀመ በመዝፈን ይታወቃል፡፡ “በአፋን ኦሮሞ ከሚዘፍኑ ድምጻውያን ቀድሞ በሬድዮ ላይ የዘፈነ“ በማለት የሚገልጹ አሉ፡፡ እሱም እየ ዘፈነ በነበረበት አመትም ዘፈን በሸክላ እየተቀዳ ነበር፡፡ “አለም መነረግስታቲ ብራ ዴሞና“ የሚል እና ማሳን ጋማ ላፋን ባቱ“ የሚል ዘፈን የዘፈነው ወሰኑ ዲዶ ነው፡፡ በአገር ደረጃ ባህልን በማሳየት ውስጥ በሀገር ፍቅር ትያትር በአፋን ኦሮሞ እና በአማርኛ እየሰራ ነበር፡፡ ህዝብን እየቀሰቀሰ ከዘፈነው ዘፈን ውስጥ ጥቂቱ፡-

*ሳንጋ አፋ ጀናን ኦፍኔ ባና ሸገር*

*ካን ሻኒን ብታታ ኩን ሻንተማን ብታ ገሪኒ*

*አባንስ ዮ ዱሌ ኢልማ ጅሩ ሂን በዱ መቃን*

*ያ አላማ ቃዌ ታአን ቶላ ላማኒኒ*

*ላባኒን ኒ ኢያ ማሬ ዮ ዱሌ ጀባን ጋፋ ቢያ*

በማለት አባት በአገር ግዜ ቢሞትም ልጅ እርሱን እንደ ሚተካ እና ትግልን እንደሚያስቀጥል በዘፈኑ እየገለጸ ነበር ከዚህም ሌላ ያ ማንሲቆ በማለት ከማሲንቆ ጋር እየተነጋገረዘፈነው ዘፈን በህዝብ ዘንድ ትልቅ ፍቅር አግኝቷል፡፡ አንጋፋው መሲንቆ በመጫወት የሚታወቀው ለገሰ አብዱ ወሰኑ ዲዶ ለእርሱ ተምሳሌት እነደሆነ ይናገራል፡፡

**ድምጻዊ ለገሰ አብዲ**

ለገሰ አብዲ በ1931 እ.ኤ.አ. በሰሜን ሸዋ አቡቹ ወረዳ ያያ ቀጨማ የተወለደ ሲሆን ለኦሮሞ አርት እና በኢትዮጵያ ውስጥ ማሲንቆ በመጫወት ትልቅ ቦታ ያለው ሰው እና ታዋቂ የኦሮሞ ዘፋኝ ወይም ድምጻዊ ነው፡፡ ድምጻዊ ለገሰ አብዱ ከአባቱ ከአቶ አብዱ ዳዲ እና ከእናቱ ከወይዘሮ ፎሌ ጉደታ የተወለደ እና ብቸኛ ልጅ ነው፡፡ ለገሰ ለማስንቆ ፍቅር ጨዋታ እድሜው በ20ኛዎቹ ቤት በነበረበት ጊዜ ወደ ሸገር በመሄድ በሀገር ፍቅር ትያትር መዝፈን ጀመረ፡፡ ሀገር ፍቅር ትያትር ፣ብሔራዊ ትያትር አዳራሽ መዘጋጃ ቤት ባህላዊ አዳራሽ፣ፖሊስ ኦርኬት ስራ፣ክቡር ዘበኛ እና በሌሎች ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሰርቷአል፡፡ ድምጻዊ ለገሰ አብዲ በዘፈኑ የሰውን ልብ የሚያነሳሳ በመባል ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም በ1970 እ.ኢ.አ. ውስጥ ለጓደኞቹ እንደ ደምሴ ደስታ፣ለማ ገብረ ህይወት፣አየለ ይማሙ ጋር በመሆን በግላቸው የሀገር ባህል ሙዚቃ ቡድን የተባለ በመመስረት በሙዚቃ ለአርት እድገት ከፍተኛ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በተለያየ

ግዜ በውጭ አገር እንደ ኬኒያ፣ሱዳን እና ደቡብ ኮሪያ በመሄድ የኦሮሞ ባህል እና ዘፋኞችን በማሳየት ከፍተኛ አድናቆት አግኝቷል፡፡ በአጠቃላይ ድምጻዊ ለገሰ አብዲ ከባድ ተጽእኖ በነበረበት እና በአፋን ኦሮሞ በተቀየረበት ጊዜ በዚህ ውስጥ በማለፉ ከስልሳ (60)አመት በላይ ለኦሮሞ አርት እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

### ድምጻዊ አሊ ሸቦ

ድምጻዊ አሊ ሸቦ ወዶ ከተወዳጁ ኦሮሞ ድምጻውያን ከሆኑ ከአፍረን ቀሎ ልጆች አፈረን ቀሎን ከመሰረቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ነው፡፡ አሊ ሸቦ ለቋንቋችን እና ባህላችን እድገት ላይ ደክሞ የማያውቅ ለቋንቋ እና ባህል ትግል ከጀመረ ቀን እስከ አሁን ያለበት እና የኦሮሞን ዘፈን አቀናጅቶ የኦሮሞን ድምጻውያን በመርዳት ይታወቃል፡፡ የአፈረን ቀሎ ኪነት በመመስረት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ /ጥረት/ አድርጓል፡፡ አሊ ሸቦ በጓደኞቹ ዘንድ ከበሬታ እና ፍቅር በማግኘት እንዲሁም በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡

### ድምጻዊ አሊ ቢራ (ክቡር ዶክተር አሊ ቢራ)

አሊ መስከረም 29 1950 እ.ኢ.አ. በድሬ ደዋ ከተማ ረገአሬ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ተወለደ፡፡ አሊ ቢራ (አሊ መሀመድ ሙሳ) ዘፋኝ፣ ሙዚቀኛ፣ገጣሚ እና የኦሮሞ ህዝብ የሚኮራበት ነው፡፡ እድሜው 13 ሲሆን በአፈረን ቀሎ ኪነት የኦሮሞን ባህል ለማሳደግ በድብቅ ይሰራ ከነበረ ጋር ተቀላቀለ፡፡ ከዚህ የተነሳ አሊ ቢራ የሚል ስም አገኘ፡፡ የሀይለ ስላሴ መንግስት ይህንን ኪነት በ 1965 እ.ኢ.አ ዘግቶ የዚህን ኪነት አባሎች በከፊል እስር ቤት አስገባ፡፡ አሊን ተሰዶ ወደ ሸገር ገባ፡፡ አሊ ወደ ፊንፊኔ ከገባ በኋላ የተለያዩ የዘፈን ስራ መስራት ጀመረ፡፡ አፋን ኦሮሞን ጨምሮ አማርኛ ፣አረብኛ፣የሐረር ቋንቋ እና ሱማልኛን መዝፈን ይችል ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በተለያዩ ሰዎች ዘንድ እንዲደነቅ

እና እንዲወደድ አደረገ፡፡ አሊ ከክብር ዘበኛ ቡድን ጋር በመቀላቀል በተለያዩ አካባቢዎች የመሄድ እድል አግኝቶ ችሎታውን ማሳየት ችሏል፡፡ በትልቅ መድረኮች እንደ አገር ፍቅር ትያትር እና ራስ ትያትር እየዘፈነ ነበር፡፡ አሊ በስራው በዘፋኝነት እና ሙዚቀኛነት በመቀጠል የመጀመሪያው አልበም 1971 እ.ኢ..አ. አወጣ፡፡ ይህም በኦሮሞ ዘፈን ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ተወዳጅ ዘፈኖች እንደ "ህን ያድን፣አሳበላሆ፣አማሌሌ፣አባ ሬኔ ካና ና ገመቹ" አወጣ፡፡ አልበሙም የሱዳን ቋንቋ ዘፈኖች እንደ "አል ሀቢቢ ዌን" የአረሪ ዘፈን እንደ "ይደንቃል" ከውስጡ" ያለው ነበር፡፡ በ1988 እ.ኢ..አ. በሎስአንጀለስ አርትስ አካዳሚ ለመማር ወደ የኤስ. ኤ. ሄክ በ1990 እ.ኢ..አ. ከተመረቀ በኋላ በ1992 እ.ኢ..አ. ከኢትዮጵያ ውጪ በመሆን የመጀመሪያን ሁለት አልበም ለቀቀ፡፡ ይህም በአለም ላይ እንዲታወቅ አደረገው፡፡ አሊም ብዙ ኮንሰርቶችን በተለያዩ አገራት ውስጥ አካሂዷል፡ ፡

በ 1995 እ.ኢ..አ. ቶሮንቶ አፍሪካን ሜሪት ሽልማት (Toronto African Merits Award) አግኝቷል፡፡ በ 2010 እ.ኢ..አ ደግሞ ከጅማ ዩኒቨርስቲ የክቡር ዶክተሬት አግኝቷል፡፡

### ድምጻዊት ሀሎ ዳዌ

ድምጻዊት ሀሎ ደዌ በድሬ ደዋ ከተማ ተወልዳ አደገች፡፡ ድምጻዊት ሀሎ ዴዌ በ15 አመቷ ወደ አርት ስራ እነደገባች ይነገራል፡፡ ከ40(አርባ አመት) በኋላም የተለያዩ ዘፈኖችን ለግሏ 10 (አስር) ካሴት፤ከሰዎች ጋር ደግሞ 13 ካሴት በአጠቃላይ 23 ካሴት ዘፈኖችን ሰርታለች፡፡በዚያን ጊዜ በድሬደዋ ከተማ አአፈረን ቀሎ በኋላ የተመሰረተው ቢፍቱ ቢየ ቱኛ የሚል ኪነት ውስጥ ዘፈን ጀመረች፡፡

ባለፉት ስርአቶች ውስጥ በኦሮሞ ብሄር እና አፋን ኦሮሞ ላይ ተጽእኖ ይደርስ በነበረበት ከመነሳት ሀሎ ደዌ በዚህ አርት ስራ ውስጥ እንድትገባ መነሳሳት እፍረት በነበረበት ግዜ ሬድዮ ይሰብራል ተብሎ በነበረበት በቋንቋዋ በመኩራት መድረክ ላይ ወጥታ የኦሮሞ ብሄር ማንነትን በማሳየት ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውታለች፡፡ህይወቷን በሙሉ ለኦሮሞ እና በኦሮሙማ ጉዳይ ላይ እራሷን ሰጥታ እየሰራች ነበረች፡፡ ሀሎ ደዌ ዘፈኖችን እንደ ዋል ሆራ ዋራ ኬሳኒ ቴሱምት ጉዶን ሸገር፣ ባቡራ ያገኤን ዱፋ ና ኤግ ያ ሻማረማሪ በማለት ለተወዳጀቿ እና አድናቂዎቿ ተሰሚነት በማግኘት በብዙ አድማጮች ጆሮ ውስጥ አለች፡፡ ሌሎች ብዙ ዘፈኖች አሏት፡፡ ሀሎ በምስራቅ ኢትዮጵያ ብትኖርም በዘፈኖቿ በምእራብ ያሉትንም በማዜም ትታወቃለች፡፡

## ድምጻዊት እልፍነሽ ቀኖ

ድምጻዊት እልፍነሽ ቀኖ በምእራብ ኦሮሚያ በምስራቅ ወለጋ ዞን በነቀምቴ ከታማ ሲኑጉቶ በሚባልበት ቦታ ተወለደች፡፡ አርቲስት እልፍነሽ ቀኖ በ1969 እ.ኢ.አ. ወደ ትግል ተቀላቀለች፡፡ ከዚያ በኋላ የአርትን ስራ እነደጀመረችው ይነገራል፡፡ በትግል ዘፈኖች የምትታወቀው እልፍነሽ ፍቅርን አስመስላ የህዝብን ጭቆና እየገለጸች ነበረች፡፡ ከዚያ በኋላ በደርግ መንግስት ከነቀምቴ ከተማ ተባርራ ወደ ፊንፊኔ ከተማ በመሄድ እዛው የዘፈን ትግሎችን ቀጠለች፡፡ በአርት ስራ ውስጥ ከባድ ተጽእኖ በእርሷ ላይ ይደርስ እነደነበር እና ጸጉሯን በተሰባበረ ጠርሙስ በመላጨት በእስር ቤት መንገላታት እና ዘፈንን የመዝፈን መብት እስከ ማጣት ደርሳለች፡፡ በዚያ ውስጥ በማለፍ እስከ አስር(10) ካሴት ማውጣት ችላለች፡፡ እልፍነሽ ጌረርሳ (ቀረርቶ) የምትወድ ሲሆን ከቀረርቶዋ መጀመሪያ ውስጥ ሴት ከወንድ ጋር እኩል መሆኗን የሚገልጽ ከዚህ በታች ተገልጻል፡-

ጌራር ጌራር ጀቴ

አን ማላን ጌራራ

ገረረ ጌረሪ ጀቴ

አኒ ማለን ገረራ

አኖ ያዳን ዬለላ

ጌረሬ ማል ናሆንፉ

ዮን ዲሴ ነን ኮልፉ

ዩን ገረረ ማል ቀባ

ኤሳ ኮቱ ሙዳ ቀባ

ገደር ጉባን ላፉሬ

ዱበርቱማን ፋፉሬ

ጭቴን ናማት ሀፉሬ

ጀዴን እት ደሬካ

ፎን ማዲቱ ና ፎሬካ

ዮ ድር ራፌ ካኤ

አናቱ ቴላት ሀፉሬ

ሚታ ካን ራጂ ራጃ

አንኩሮን ቡቄ ራጃ

ፋርሶን ድንቻ ራጃ

ላፍትካ ህን እጃጁ

ካን ኦሮሚያን ራጃ

ናዴን ሀሬዳ ህን በስቱ

ካን ሀደ ሬኤት ራጃ

ዱርብ ዱር ህን ጌረርቱ

ካ እልፌ ቀኖ ራጃ

## ድምጻዊት አልማዝ ተፈራ

ድምጻዊት አልማዝ ተፈራ ለረጅም ዓመታት በአፋን ኦሮሞ ዘፈን እንደነበረች በኦሮሞ ሙዚቃ ውስጥ ትልቅ ስራ በመስራት የምትታወቅ ነች፡፡ ከአፋን ቀሎ ባንድ ምስረታ ጀምሮ በኦሮሞ ሙዚቃ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡ ድምጻዊት አልማዝ ተፈራ እንደ ኦሮሞ ድምጻውያን ትልቅ አስተዋጽኦ ከአደረጉት እንደ እነ አደም ሀሩን፣ከዲር ሰይድ፣አሊ ሽቦ፣ሀሎ ዳዌ ጋር ረጅም ታሪክ አላት፡፡

## ድሚጻዊ ኡስማየሁ ሙሳ

በ1967 እ.ኢ.አ. ከአባቱ ከሙሳ ከእናቱ ፋጡማ አብደላህ ተወለደ፡፡ በምስራቅ ኦሮሚያ አካባቢ በአረማያ ከተማ ተወለደ፡፡ ኡስማዩ ሙሳ የነጻነት ታጋይ የኦሮሞ ዘፋኝ ሆኖ ለኦሮሞ ህዝብ ታጋይ ጀብዱነት እየፈጠረ ከነበሩት አንዱ ነው፡፡ ኡስማይ ከልጅነቱ ጀምሮ የሙዚቃ ፍቅር አለው፡፡ የመጀመሪያው አልበም በትግል/ነጻነት ላይ ያተኮረ ጅማሪ ሆኖ ይህ ዘፋኝ በትግል/ነጻነት ላይ ያተኮሩ ዘፈኖች በማውጣት ስም አግኝቷል፡፡

በሀሳብ ላይ አቋም በመያዝ በአጠቃላይ ኡስማዩ ሶስት አልበም ካወጣው "ቢሊሱማ ፊ አሚሚን፡ አ አ ፋ አጄቻነ ድበት ኑሂን ዴቢሱ አሬ ኑተኢ ያ ረቢ ኑሞና ዬ ገምታን ጂራኔ" ከሚባሉት ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ድምጻዊ እና ገጣሙ ኡስማዬ ሙሳ የአካል እና የአእምሮ ግፍና ጭቆና ይደረስበት እንደነበር እና በዘዋይ እስር ቤት ባህር ዳር 1999 እ.ኢ.አ አረፈ፡፡

ድምጻዊ ሀይሉ ዲሳሳ

ድምጻዊ ሀይሉ ዲሳሳ በምዕራብ ኦሮሚያ ዞን ቀለም ወለጋ ተወለደ፡፡ ሀይሉ ከዚህ አለም እስከተለየ ድረስ የኦሮሞ ባህል እና አርትን እየአንጸባረቀ እና እየአደነቀ ሲጫወት ነበር፡፡ አፋን ኦሮሞ ለመጻፍ እና

በጥሩ ድምጽ እያቀነቃነ በመዝፈን የተለያዩ ድራመ፤ፊልም እና ትያትር በመስራት ታሪካዊ የሆነ ነገር እየሰራ ቆይቷል፡፡ ሀይሉ ይህን ሁሉ ሲሰራ የቆየ እና በኦሮሞነቱ ተጽእኖ ይደረግበት የነበረ ሲሆን ይህን ሁሉ ችሎ በመርታት ነበር ህይወቱ እስከ መጨረሻ ይገልጻል፡፡

የሀይሉ ዲሳሳ ከሚታወቅበት ዘፈን ውስጥ የተወሰነው "ጌረርሳ (ቀረርቶ) ያ ወረ በዳ ያ ፊነኮ ነጋዴን ያደበርቱ ያደመ ኮ አመ ያ መሪ ሸጌ ቲያ" እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ድምጻዊ ኤቢሳ አዱኛ

ድምጻዊ ኤቢሳ አዱኛ በምስራቅ ኦሮሚያ ዞን በቄለም ወለጋ ከተማ በደንቢ ዶሎ ተወለደ፡፡ ኤቢሳ አዱኛ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ የሆነ ጋታት በመጫወት ባህላዊ የአፋን ኦሮሞ በማስተማር ይታወቃል፡፡ይህ ድምጻዊ ህዝቡን ለትግል እና ለነጻነት የሚያነሳ ነው፡፡ እሱ የሚያምንበት የፖለቲካ ደረጃ አገር ከወጣ በኋላ አገር ውስጥ የነበረ እና ይህ ድምጻዊ በዚያን ግዜ በዘፈኑ የጦርነት ትግልን የሚደግፍ እያወጣ መዝፈኑን ቀጠለ፡፡ በዚህ ምክንያት ለአዳጋ በመጋለጥ ነሀሴ 24 በ1988 እ.ኢ.አ. በፊንፊኔ ከታማ ሽሮ ሜዳ በሚባል ቦታ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ተገደለ፡፡ ድምጻዊ ኤቢሳ አዱኛ ደፋር (ጀግና) ርህሩህ ሰው የሚያምነውን የሚናገር እና የማይፈራ እንደነበር ይነገራል፡፡

## ድምጻዊ ሃጫሉ ሁንዴሳ

ድምጻዊ ሀጫሉ ሁንዴሳ በአጭር ግዜ ውስጥ ተወዳጅ እና ትልቅ ስምን ከአተረፉ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሀጫሉ ኦሮሞ እንደሌሎች የኦሮሞ ድምጻውያን የህዝቡን ጥያቄ በሚመለከተው ላይ ግጥም እና ዜማን በማቀናጀት በህዝብ ጆሮ ዘንድ መታወቅ ችሏል፡፡ ይህ የራሱ ስራ በሌሎች ብሄረሰቦች ዘንድ ቶሎ ብሎ ከመታወቅ አልፎ ከዘፈን ውጪ ብርቱና በድፍረት መናገር ባለበት ሁሉ ስለ ኦሮሞ ህዝብ በግልጽ

በመናገር ይታወቃል፡፡ ከተወሰኑ ቀናት ከመገደሉ በፊት ከህዝብ ዘንድ ፍቅር እና እውቅና ባለው ለመግለጽ “አን ኦሮሞፍ ቀሊዳ“ ትርጉሙም እኔ ለኦሮሞ ውድ ነኝ ብሎ ገለጸ ነበር፡፡ ሶስተኛውን አልበም እየሰራ እያለ ሰኔ 29 በ 2020 እ.ኤ.አ. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተገደለ፡፡ ሀጫሉ ለእውነተኛ ትግል እና ነጻነት ከሚደረጉት ውጪ ኦሮሞን ለማጠንከር የአደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ቀዳሚያን አርቲስቶች የኦሮሞ ባህል እና ሙዚቃ በማሳደግ ውስጥ ትልቅ ዋጋ እስከ ህይወት መሰዋህትነት የወጡ እና ዛሬም ያሉ ብዙ ናቸው፡፡

ድርጊት 2

ሀ. የኦሮሚያ ክልል ተወዛዋገሮች ታሪክን በማጥናት ለክፍል አቅርቡ፡፡

ለ. ከዚህ በላይ ካሉት የአንድ የሙዚቃ ድምጻዊ ዘፋኝ በመምረጥ በተግባር አሳይ፡፡

ሐ. የአካባቢያችሁን ባህላዊ ውዝዋዜ በቡድን በመለማመድ ለክፍለችሁ አቅርቡ፡፡

## 3.2 ባህላዊ ጌጣጌጦች

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት

ከዚህ ትምህርት ርእስ በስተመጨረሻ፡

- የተወሰኑ የኦሮሞ ነ,ማህበረሰብ ባህላዊ ጌጣጌጦችን ትገልፃላችሁ፡፡
- የባህላዊ ጌጣጌጦችን ጥቅም ትለያላችሁ፡፡
- ባህላዊ ጌጣጌጦች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ጊዜ ትለያላችሁ፡፡

**ውይይት 3**

ባህላዊ ዕቃዎች ምንድን ናቸው? ምን ምን  እንደሆኑ ዘርዝሩ፡፡

ባህላዊ መሳሪያዎች ለምን አገልግሎት ይውላሉ

የኦሮመ  ማህረበረሰብ ባህሉን ለማስተዋወቅ የተለያዩ ባህላዊ ዕቃዎችን ይጠቀማል፡፡ ስለሆነም በተለያዩ ጊዜ የኦሮሞ ማህበረሰብ ስጠቀምባቸው የኖረ ባህላዊ መሳሪያዎች ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ከለቻ፣ ቦኩ፣ ጫሬጬ፣ ስንቄና የመሳሳሉት ናቸው፡፡

### 1. ቦኩ

ቦኩ በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ህገ ደንቦችን ተግበራዊ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ባህላዊ መሳሪያ ነው፡፡ ቦኩ ቅርፁ የሰው ልጅ የእርበታ አከላትን የሚመስል ነው፡፡ በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ ከቦኩ ጠቀሜታዎች የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ህጎችን ለማስከበር
- አለመስማማትን ለመፍታት



ስዕል 3.1. የቦኩ ስዕል



## 2. ከለቻ

ከለቻ በግነባር ላይ የሚታሠር ሆኖ የሚስሩትም ወንዶች ናቸው›› በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ህግን መጣስ ወይም የማይወደድ ነገር መስራት በጣም አስነዋሪ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ አይነት ድርጊት በሚፈፀምበት ጊዜ ይህን ባህላዊ ዕቃ በማውጣት አምላክን ይለምናሉ፡፡



ስዕል 3.2፡ የከለቻ ስዕል

ልምምድ2

ከላይ ያለውን የከለቻ ስዕል በመመልከት በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ነገሮች አስመስላችሁ በመስራት ለክፍል አቅርቡ፡፡

## 3. ስንቄ

በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ስንቄ ህግን ለማስፈፀም ይተቅማል፡፡ ስንቄ የሚሰራው ከቀጭን የእንጨት ዘንግ ነው›› ስንቄ የሚያዘው በሴቶች ሲሆን ለሴቶች ሊሰጥ የሚገባውን አክብሮት ያሳያል፡




ስዕል 3.3፡ የስንቄ ስዕል

ተግባር 3

ስንቄ መቼ እንደሚያዝ፣ በማናንና ለምን እንደሚያዝ ተላላቆችን በመጠየቅ በቡድን ሆናችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡

## 4. ጫሬቤ

ጫቤቤን የሚጠቀሙት ሴቶች ሲሆኑ ቅርፁም የሴቶች የእርበታ የሰውነት ክፍል ይመስላል፡፡ በመሆኑም በወንዶች ጥቅም ላይ አይውልም፡፡ ነሌላ በኩል ጫቤቤ የአቴቴ ስነስርዓት ከሚተገበርባቸው መሳሪያዎች አንዱ ነው፡፡



ስዕል 3.4. የጫቤቤ ስዕል

ተግባር 4

ጫቤቤ መቼ እንደሚያዝ፣ በማናንና ለምን እንደሚያዝ ተላላቆችን በመጠየቅ በቡድን ሆናችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡

## 3.3 በሀገር በቀል እውቀት ስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልምን ማሳየት

**መግቢያ**

ማንኛውም ማህበረሰብ ከሌላኛው ማህበረሰብ የሚለየው ነገር ይኖረዋል፡፡ ይህ ማለት አንድ ማህበረሰብ ለአኗኗሩ አመች የሆኑ እውቀት እና ችሎታ ፈጥሮ ኑሮውን ለመግፋት የሚጠቀመው እምቅ ዘዴ አለው ማለት ነው፡፡ ታድያ ይህ ችሎታው አገር በቀል እውቀት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ ይሁንእና በአንድ አገር ውስጥ የተለያዩ ብሄሮች በማህበረሰቡ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ርዕስ ውስጥ አገር በቀል የኦሮሞ ብሄር ስነ-ትያትር እና ስነ ፊልም አሰራር ዘዴውን ትማረላችሁ፡፡ ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት

**ከዚህ የትምህርት ርዕስ መጨረሻ ፡-**

- የሀገር በቀል እውቀት ምንነትን ትገልጻላችሁ
- በኦሮሞ ሀገር በቀል ስነ ትያትር እና ስነ-ፊልም እውቀቶችን ታሳያላችሁ
- የማህበረሰብህ አገር በቀል እውቀት ውስጥ ያለውን ድርሻ ትገልጻለህ

**የግንዛቤ ጥያቄ 4.**

1. ሀገር በቀል እውቀት ማለት ምን ማለት ነው ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡
2. የኦሮሞ ብሄረሰብ ያለውን ሀገር በቀል እውቀት እርስ በእርስ ተነጋገሩበት፡፡

   ሀገር በቀል እውቀት ማለት ፡- አንድ ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ለመምራት ስንጠቀምበት የቆየ እና አሁንም የምንጠቀምበት

እውቀት ነው፡፡ ይህ ማለት የአንድ ማህበረሰት ፈጠራ እነደ ሰው አኗኗር ውስበስብ ስለሆነ ይህ ነው ብለን የምንለየው አይደለም፡፡

የእለት ተእለት የሰው ልጅ አኗኗር የሚገናኝ ስለሆነ ከህብረተሰብ እንቅስቃሴ ለይተን ማየት የምንችል አይደለም እንዲሁም ኑሮአቸውን ለማከናወን የሚጠቀሙበት ፈጠራ ወይም የተስማሙበት ነገር እንደ የቤተሰብ መመሪያ፣ባህል፣በአሎች፣የባህል ቁሳቁስ (እቃዎች)፣ የቤት አሰራር ፣የአለባበስ ዘይቤ፣የምንጠቀምበት የምግብ አይነቶች እና አንድ ማህበረሰብ ያለውን መልካም እሴት ያቀፈ ነው፡፡

እነዚህ ፈጠራዎች በአይን በማይታዩ ደረጃግን በተግባር የምናውቃቸው ሲሆኑ ወይም የማህበረሰብ ፈጠራዊ እንደ የባህል ምግብ፣ባህላዊ ልብሶች፣ ስነ ህንጻ፣የተለያዩ የቤት እቃዎች፣የማህበረሰቡ እሴቶች፣የባህል አካባበር እና የመሳሰሉት ማህበረሰብ አብሮ ማህበረሰብአዊ አኗኗሩን የሚያሳይበት ነው፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ፣በደስታው፣በሀዘኑ፣ እንደህብረተሰቡ ስፋት እና ጥበት የሚጠቀምበት አካላዊ እንቅስቃሴ ለምሳሌ፡- በሸጎዬ፣ጌሎ፣ቀረርቶ፣(ጌረርሳ)፣ጥፈራ፣ረገዳ፣ትሪና የትኛውም ባህላዊ እንቅስቃሴ ለይ የሚታዩትን የያዘ ነው፡፡

የኦሮሞ ብሄር የሚተዳደርበት ስርአቶች፣ገዳ ስርአት፣የዋቄፈና እምነት፣ከባህሎች መሀል እሬቻ፣እንደዚሁም የጋብቻ ስርዓት ጨምሮ የተለያዩ ቁሳቁሶች ይጠቀሙበት የነበረ እና አሁን ድረስ እየተጠቀሙበት ያለ ነው፡፡ በዚህ ርዕስ ውስጥ እንዲታወቅ የተረለገው ሀገር በቀል እውቀት ምንነት ላይ በማተኮር የማህበረሰቡን ስነ-ትያትር ፈጠራን በመጠቀም እየተዝናናን እንድናስተምር፡፡ ተማሪዎች ሀገር በቀል እውቀት ብቃት ከኦሮሞ ብሄረሰብ ከተማሩ በኋላ የእውቀት ውስጥ የራሳቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ ወይም እንድትወጡ ነው፡፡

ከኦሮሞ ሀገር በቀል እውቀቶች መካከል አንዱ ደግሞ የኢሬቻ በዓልን ወደ ትያትር በመቀየር እናያለን፡፡

## ኢሬቻ

በአገራችን ውስጥ የሚከበሩ ብዙ አመታዊ ክብረ በአሎች አሉን፡፡ ኢሬቻ ደግሞ ከኦሮሞ አመታዊ ክብረ በአሎች አንዱ እና ትልቁ ነው፡፡ ኢሬቻ ከትንሽ እስከ ትልቅ እርጥብ ሳር እና አበባ በመያዝ ተራራ እና ወንዝ (መልካ እና ቱሉ) ላይ በመገናኘት ዝናብን የምታዘንብ አምላክ፣ በሰላም እንኳን ከክረምት ወደ ጸደይ አወጣህ አገራችንን ሰላም አድርግልን በማለት አምላክን በማመስገን እና እንዲደረግላቸው የሚፈልጉትን ደግሞ ከአምላክ የሚጠይቁበት አመታዊ ክብረ በአል ነው፡፡ ይህ አመታዊ ክብረ በአል እጅግ በጣም በብሄሩ፣በአገራችን እና በአለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ተከታታይ እና እውቅናን ያተረፈ ነው፡፡

ለዚህ የኢሬቻ ስነ-ስርዓት ከቤታቸው ወጥተው ወደ ሚመለከው (ወንዝ) ሲሄዱ የራስ ስነ ምግባር እን አካሄድ ያለው ነው፡፡ ይህን ስርዓታዊ አካሄድ በትያትራዊ መልኩ ሲቀርብ ከዚህ በታች የተጻፈውን የመስላል፡፡

## የኢሬቻ የተውኔት ትዕይንት

ኢሬቻ የሚሄዱ ሰዎች በማለዳ ተነስተው የባህል ልብሳቸውን በመልበስ፣ በተለያዩ ማጌጫዎች በመዋብ ለምለም ሳር እና አበባዎች ይዘው በመሰባሰብ ሲጓዙ ይታያሉ፡፡ እናቶች እና ኮረዳዎች ከፊት ለፊት፣የአገር ሽማግሌዎች በመከተል እና ወጣቶች ደግሞ ከጀርባቸው በመከተል ወደ መልካው ይወርዳሉ፡፡

ሴቶች

*ኦ.....ያ መሬሆ.........መሬሆ (2)*

*መሬሆ...........መሬሆ (2)*

ያ ዋቀ ኡማ ሁንዳ መሬሆ

ኦኦ...........ያ መሬሆ

መሬሆ............... መሬሆ (2)

ያ ዋቀ ለፊ ኡምቴ መሬሆ

ኦ........... ያ መሬሆ

መሬሆ............መሬሆ(2)

ያ ዋቀ መልካ ኢ.ምቴ መሬሆ

ኦ...........ያ መሬሆ

መሬሆ...........መሬሆ (2)

ያ ዋቀ ኦዳ ኡምቴ መሬሆ

ኦ-------ያ መሬሆ

መሬሆ .............መሬሆ(2)

ያ ዋቅ ኦዳ ሮባ መሬሆ

ኦ-----ያ መሬሆ

መሬሆ-----መሬሆ (2)

ያ ዋቅ ኦዳ ብለ.ቅ መሬሆ

ኦ..........ያ መሬሆ

መሬሆ ----------መሬሆ(2)

ያ ዋቅ ኦዳ ቢ.ስል መሬሆ

ኦ .........ያ መሬሆ

መሬሆ...........መሬሆ (2)

ያ ዋቅ ኦዳ ቡልቱም መሬሆ

ኦ .........ያ መሬሆ

መሬሆ...........መሬሆ (2)

ያ ዋቅ ኦዳ ነሚ መሬሆ

*አ .........ያ መሬሆ*

*መሬሆ...........መሬሆ (2)*

*ያ ዋቅ ነመ ኡምቴ መሬሆ*

*አ .........ያ መሬሆ*

*መሬሆ...........መሬሆ (2)*

*ያ ዋቅ ቱሉ ኡምቴ መሬሆ*

*አ .........ያ መሬሆ*

*መሬሆ...........መሬሆ (2)*

*መር.ጋ ቀበኔሲ ከዳኔ መሬሆ*

*አ .........ያ መሬሆ*

*መሬሆ...........መሬሆ (2)*

*መልካ ቡኔ ሲከደኔ*

*አ .........ያ መሬሆ*

*መሬሆ...........መሬሆ (2)*

*ጂዳ ቀበኔ ሲከደኔ መሬሆ*

*መሬሆ...........መሬሆ (2)*

*ኢሬቻ አሬ ኬኛ*

*አ..........ያ መሬሆ*

*መሬሆ..........መሬሆ (2)*

**አባቶች** (አቦቲ)

*ገቢሳ ሆሆ*

*ሮቤ ቢየ ገቢሴ*

*ገቢሳዮ ሆ ሆ*

*ሮቤ ቢ.ያ ገቢሴ*

*ኦሮሞ ኮረማ ቀሌ*

*ኮርማ ቢያ ፎሌ*

*ሮባ ቢያ ገቢሴ*

*ገሲሳዩ ሆሆ*

*ሮባ ቢያ ገቢሴ*

*ኦዳ ሮባ ያ ቱማ ኮ*

*ነ ቱምሲ ሜ*

*ኦዳ ሮባ ያ ቱማኮ*

*ነ ቱምሲ ሜ*

*ኦዳ ሮባ ያ ቱማኮ*

*ነ ቱምሲ ሜ*

*ከለቻፉ ጫሌቡሌያ ቱ ማኮ*

*ነ ቱምሲ ሜ*

*ሀዩ ብያ ያ ቱማ ኮ*

*ነ ቱምሲ ሜ*

**የወጣቶች**

*ያ ኦሮሞ ሲፉ ገልቴ አዳቲ*

*ኬሰቲ አባቱ ጀ ቤፉታኦ ያዳን*

*ያአባ ቢያ ሲፍ ገልቴ አዳቴ*

*ኬሳቲ አባቱ ጀቤፈታን የዳን*

*መልካ ኤርጋ ገሀኒ ቦዳ ጃርሶሌ ኒ ኤቢሳ*

**የሽማግሌዎች ምረቃት** *ሀዩ ያዋቃ*

**ዋቃ ኡማ ዋቃ ኡመማ**

**ቶከቻ ዋቃ ዲባ**

**ሊም ገረ ተሊላ**

**አባ ዱባ ፊ ጃላላ**

ከን ሲ ኡሜ ሂንጅሩ

ከን ሲ መሌ ኡመሜ ሂንጅሩ

መን ነጋን ኑ ቡልቼ ነጋንኑ ኦልቻ

**ከስፒ የሚቀበሉት** ኦልቻ ዋቃ

**የሽማግሌዎች ምረቃት**ህማ ኑራ ቀቢ

**ከስር የሚቀበሉት**ቶላ ኑራ ቀቢ

**ከስር የሚቀበሉት**ቀቢ ዋቃ

**የሽማግሌዎች ምረቃት**ህማ ኑራ ቀቢ

**ከስር የሚቀበሉት**ቀቢ ዋቃ

**የሽማግሌዎች ምረቃት**ከን በረናን ኑ ጌሴ በረ ዱፋን ኑ ገሂ

**ከስር የሚቀበሉት**ገሂ ዋቃ

ወደ መልከው (አንዙ) ከደረሱ በኋላ አባ ገዳዎች አስቀድመው ይመርቃሉ፡፡ ከዝያም ሁሉም በቅደም ተከተል የኢሬቻውን ስነ-ስርዓት በማከናወን እየአዜሙ ይመለሳሉ፡፡

## የኢትዮጵያ ትያትር፤የፊልም በለሙያዎች እና ሥራዎቻቸው

በተለያዩ ሀገራት ውስጥ የትያትር ጥበብ መነሻው የማህበረሰቡ ሥነ-ቃል እና የማህበረሰቡ አኗኗር ዘዴ ላይ በመመስረት እያደገ መጣ፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ የትያትር ጥበብ እድገት እንደ ሌሎቹ የአለም ሀገራት (እንደነ ግሪክ እና ሮም) በቀጥታ የማህበረሰቡ ሥነ-ቃል ላይ የተመሰረተ አጀማመር ባይኖረውም የወደኋላ እድገቱ የማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት የሕይወት ውጤት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የእትዮጵያ ዘመናዊ ትያትር በውጭ ሐገር በቆዩት ኢትዮጵያዊ በጅሮንድ ተክለሐዋሪያት ተክለማሪያም በተባሉ በ1913 ዓ.ም. የአውሬዎች ታሪክ

ላይ የተመሰረተ “የአውሬዎች ኮሜዲያ መሳለቂያ” (ፋቡላ) የተሰኘ ተውኔት በማዘጋጀት ቀረበ፡፡ በማስቀጠል የኢትዮጵያ የትያትር ጥበብ በተፈሪ መኮንን እና በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ተጀመረ፡፡ በ 1917 ዓ.ም. ከውጭ ሀገር በመጡ መምህራኖች በተጠቀሱ ትምህርት ቤቶች የትያትር ጥበብን በማስተማር ማሰራት ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ እንደነ ዮፍታሔ ንጉሴ ፤ መላኩ በጎሰውና ሌሎች የትያትር ጥበብን ማስፋፋት ጀመሩ፡፡

የትያትር ቤቶች መከፈት ለትያትር ጥበብ እድገት ትልቅ መሰረት የጣለ ነበር፡፡ ከነዚህ ትያትር ቤቶች መካከል ሐገር ፍቅር በ 1941፤ ብሔራዊ ትያትር 1956፤ ራስ ትያትር እና የሕፃናትና ወጣቶች በመከፈት ትያትርና ፊልሞች መታየት ጀመሩ፡፡ በዚህ መሰረት በርካታ ሰዎች ሞያውን እየተቀላቀሉ መጡ፡፡

በዚህ ሂደት እንደነ ጠጋዬ ገብረመድህን (ጠጋዬ ሮበሌ ቀዌሳ)፤ መንግስቱ ለማ፤ መላኩ አሻግሬ፤ ደበበ እሼቱ፤ ወጋዬሁ ንጋቱ፤ ሓይማኖት አለሙ የመሳሰሉ ባለሞያዎች ለሀገራችን የትያትርና ፊልም እድገት ከፍተኛ ሚና ተጨውተዋል፡፡

በተጨማሪም የትያተር ጥበብ ትምህርት ክፍል በአዲስ አበባ ዩኒቨረሲቲ በ1970 በመከፈት የትያትር ጥበብ በለሙያዎችን በማፍራት የትያትር ጥበብ ሙያዉ እዉቅና እንዲያገኝ ሆነ፡፡

በተያያዘ ሁኔታ ከኃይለስላሴ ዘመን ጀምሮ የአፋን ኦሮሞ ትያትር ጥበብ በተወሰኑ የኦሮሞ ታጋይ ወጣቶች በ 1958 ዓ. ም. ተፅፎ መታየት ተጀመረ፡፡ በኃይለስላሴ ጊዜ ከተመደረከ ተውኔት አንዱ “ትምህርት” የተሰኘ በ ማሞ መዘምር የተፃፈ ነበር፡፡ በደርግ ዘመን ደግሞ “በረ

ቢራን በሪተ" የተሰኘ ተውኔት 1967 ዓ.ም. በ ኃይሌ ፊዳ የተፃፈ ሲሆን ቀስ በቀስ የአፋን ኦሮሞ ተውኔቶች እያደገ መጣ፡፡

በ 1983 ዓ. ም. መጨረሻዎቹ ቆረኖ የተሰኘ ተውኔት ከእንግሊዝኛ ወደ አማሪኛ በ አቦነህ አሻግሬ ተተርጉሞ በ ዲማ አበራ ደግሞ ወደ አፋን ኦሮሞ ተተረጎመ፡፡ ይህ ተውኔት በሞቱማ አሰፋ፣ ማርታ ስለሺና ዲማ አበራ ተመድርኳል፡፡ በ 1984 ዱከናን ዱበ የተሰኘ ተውኔትነ ጀናን በ ዳባ ወዬሳ ተፅፎ በ ተስፋዬ መኮንን ተዘጋጅቶ ለተመልካች ቀርቧል፡፡ በ 1985 ጂልቢቤ የተሰኘ ተውኔት እንዲሁም ሉክሉክሳና ጉሌ ቡላ በ ፈይሳ ያደሳ ተፅፈውና ተዘጋጅተው ለህዝብ ቀርበዋል፡፡ በ1986 ሁሉቆ የተሰኘ በ አብዱናስር ሀጂ፣ በ 1987 ዳዊቲ ጂሬኛ በሙሉጌታ ነጋሳ ተፅፎ በ ዲማ አበራ የተዘጋጀ፣ በ 1992 ጉማ የተሰኘ በ ሙሉጌታ ነጋሳና ዲማ አበራ፣ ፋንዶፍቲቾ ገዶ በ ህንሴኔ መኩሪያ፣ ሞርኪ በ ሞቱማ አሰፋና አባ መኮ የተሰኘ በ 2010 በ ሌባባ ጀማል ተፅፎ በመዘጋጀት በተላያዩ መድረኮች ቀርበዋል፡፡ በዚሁ 2010 ጎዶ ጢቂ የተሰኘ ከአማሪኛ ባቢሎን በሳሎን ከተሰኘ ተውኔት በ ከበደ ዉድነህ ተተርጉሞ በ ፍቅር አምሳሉ ተዘጋጅቶ ለተመልካች ቀርቧል፡፡ እንደዚሁም በ 2014 ሚለ በከር የተሰኘ በ ወቢ በርኬሳ ተፅፎ ለህዝብ በመቅረቡ የአፋን ኦሮሞ ትያትር ጥበብ እየተስፋፋ መምጣት ችሏል ፡፡

በፊልም እድገት ደግሞ ሰንመለከት ሂሩት አባቷ ማነዉ የተሰኘ ፊልም በ ኢላላ ኢብሳ እና ጉማ ተፅፎ ለመታየት በቅቷል፡፡.

እንዲሁም የአፋን ኦሮሞ ፊልም እያደገ በማምጣቱ ለምሳሌ፡ ኤላ የተሰኘ በአብራሃም ጃለታ ፣ሚጡ በቢቅላ አስፋዉ፣ ለፋፊ ለፌ በጂማ ገለታ፣ ጋዲ ሂሬ በሜላል ገመቹ፣ ዋዳ በአንድነት አለሙ፣ አሳንቲ በኪይሪያት ዩሱፍ፣ዳንዲ ወልመራ በአማኑኤል አባገሮ፣ ሐቀ ደበ

በገመቹ ደጉሼ፣ጃተኒ ጅሬኛ በዬይስ ብሩ፡ ከሌ ኢሰ ከሌሳ በኤሊያስ ክፍሌ፣ጢቂ በሴና ሰለሞን፣ራዊ በገለተሳ ነገሪ፣ሞኣ በቤኪ ሁማ፣ሳመሎ በያዲ ብርሃኑ፣ ሚዳመ በሂርኮ ሁንዴ፣ሚልኪ በቶለሳ ድንገታ፣ጨንጨለ ጃለላ በዳዲ ሃይሉ፣ለፌ ሐርሜ በደጀኔ፣አማና በገመዶ እና የመሳሰሉ የፊልም በለሙያዎችና ሥራዎቻቸዉ በጥቂት የተጠቀሱ ሲሆን ሌሎችም የአፋን ኦሮሞ ፊልሞች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሰረት የፊልም በለሙያዎች ሙያዉንም በመቀላቀል የፊልም ጥበብ በእድገት ጎዳና ላይ ነው፡፡

የትወና ጥበብን በማስተዋወቅ በማህበረሰብ እውቅና እያገኙ የመጡ አንጋፋ በለሙያዎችን ስንመለከት ጥቂቶቹ፤ ሙሉጌታ ባልቻ፤ ታደሰ ጨኪ፤ ብርሃኑ አድማሱ፤ አበበች አጀማ፤ የሺ ረጋሳ፤ ሁምኔቻ አሰፋ፤ ኦሊ ነጋ፤ ዳዲ ቱፋ፤ ታምራት ከበደ፤ ጂማ ገለታ፤ ምንትዋብ ሀይሉ፤ ሀዊ ሀይሉ፤ አባቦ ወርቂና፤ ፍቅር አምሳሉ፤ ዳባ ገርበባ፤ ቀልቤሳ መገርሳና ሌሎች የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በ አሁኑ ጊዜ የፊልምና ትያትር ጥበብ ባለሞያዎች በተለያዩ አካባቢዎች ጥበቡን እያሳደጉ ይገናሉ፡፡

### *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ*

1. የትያትር እድገት መሰረት እምነትና ስነ-ቃል ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ ሐ
2. የትያትር ጥበብ ታሪክ መነሻው ኢትዮጵያ ነው፡፡ ሐ
3. የኢትዮጵያ ዘመናዊ ትያትር በበጅሮንድ ተክለሐዋሪያት ተክለማሪያም ተጀመረ፡፡ እ
4. በ አፋን ኦሮሞ የተፃፈ የመጀመሪያው የትያትር ተውኔት ጉማ ይባላል፡፡ ሐ

5. በማሞ መዘምር የተፃፈ የትያትር ተውኔት በረ ቢራን በሪተ ይባላል፡፡ ሐ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1. ኤላ የተሰኘ የአፋን ኦሮሞ ፊልም በማን ተፃፈ?

ሀ. ገመዶ ለ. አብርሃም ጃለታ ሐ. ጂማ ገለታ መ. ሁሉም

2. በ ሚላል ገመቹ የተፃፈ ፊልም የትኛው ነው?

ሀ. ለፋፍ ለፌ ለ. መቲወን ሐ. ጋዲ ሂሬ መ. ጢቂ

3. ከሚከተሉት የሴት ተዋኒያን አንጋፋ የሚበሉት የቶቹ ናቸው?

ሀ. አባቦ ወርቂና ለ. የሺ ረጋሳ ሐ. አበበች አጀማ

መ. ለ እና ሐ

## ምዕራፍ 3 ማጠቃለያ

- የኦሮሞ ህዝብ ቅልቅል ባህል ያለውና የተለያዩ ስርአቶች ውስጥ ያለፈ እና የደረሰ ነው፡፡ ከዚህ ላይ በመነሳት ባህል እና ጥበብ በኦሮሞ ብሄር ለብዙ ዘመናት ሲጨቆን ነበር፡፡
- ዘፋኞች እና ጨፋሪዎች በሙዚቃ ስርዐት በኦሮሞ ባህል ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው እና ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሚገልፅ ነው፡፡ አርትሲቶች እና ጨፋሪዎችን በጥቂቱ ልንገልጽ እንችላለን፡፡
- የኦሮሞ ዘፋኞች ትላልቆች እና ታዋቂዎች የምንላቸው እንደ፡- ዌሊሶ ዲልቦ፣ለገሰ አብዲ፣አሊቢራ፣ሀሎ ዳዌ፣እልፍነሽ ቃኖ፣

ኡስማዮ ሙሳ፣ሀይሉ ዲሳሳ፣ኤቢሳ አዱኛ እና ሀጫሉ ሁንዴሳ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህ የኦሮሞ ዘፋኞች (ሙዚቀኞች) የራሳቸው ብሄር፣ባህል እና እሴት ለማሳወቅ እና ለማሳደግ ትልቅ ዋጋ ከፍለዋል፡፡

- በጥንት ዘመን ሰዎች ቤታቸው ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች እንደ ጋሻ እና ጦር የመሳሰሉት የተለያዩ ቀለማት በመቀባት (ያሸበርቁበት) ያሳምሩበት ነበር፡፡
- ከጥንት ዘመን ቀለም በመነሳት በእምነት ቤቶች ውስጥ የቀለም ቅብን ስራ እየተጠቀምንበት ነበር፡፡ ወይን ጠጅ፣ቢጫ፣ቀይ፣ አረንጓዴ፣ነጭ እና ከሰል ነው፡፡
- ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሰዎች ቀለምን ለማዘጋጀት ከአካባቢያቸው ውስጥ የሚገኙትን በመጭመቅ ወይም ፈጭተው በማዘጋጀት ለብዙ ዘመናት ሲጠቀሙበት ነበር፡፡

## የምዕራፉ መልመጃ

I. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ሀሳባቸውን ትክክል ከሆነ እውነት ትክክለኛ ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት በጽሁፍ መልስ፡፡

1. በቆዳ ላይ የሚጻፍ ጥበብ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ አመታት ያለው ነው፡፡
2. ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሰው ልጅ ከአካባቢው በሚገኙ እጽዋቶች በመጭመቅ አዘጋጅ ሲጠቀም ነበር፡፡
3. በሀገራችን ውስጥ ቀለም ሀይማኖታዊ መልዕክት ለማስተለላለፍ ያገለግል ነበር፡፡
4. የስነ-ቅብ ጥበብ ከሀገራችን ስነ-ጥበባት መካከል ያልቆየ ነው፡፡
5. ሀሎ ዳዌ ከኦሮሞ አንጋፋ ዘፋኞች አንዷ ናት፡፡

6. የኦሮሞ አፍረን ቀሎን ከመሰረታዊ አርቲስቶች አንዱ አሊይ ሸቦ አንዱ ነው፡፡

## II. ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች በማንበብ ትክክለኛወን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ፡፡

1. ከዚህ በታች ካሉት ምርጫዎች አንዱ በዱሮ ዘመን ቀለም ለማምረት ሲጠቀሙ የነበሩት የትኛው ነው?

   ሀ. ከሰል　　　ሐ. የኖራ ድንጋይ

   ለ. አበቦች　　　መ. ሁሉም መልስ ነው

2. በሰሜን ኢትዮጵያ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሲተቀሙበት የነበረው ቀለም የትኛው ነው?

   ሀ. ሰማያዊ　　　ሐ. ከሰል(ጥቁር)

   ለ. ብጫ　　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

3. በጥንት ዘመን በቀለም ቅብ የሳሉትን ስዕል እንዳይፈነዳ እና እንዳይታጠብ ምን ሲጠቀሙ ነበር?

   ሀ. የነጭ ሽንኩርት　　　ሐ. ማጣበቂያ

   ለ. ስኳር　　　መ. ዘይት

4. የዶሮ እንቁላል በቤቱ እምነት ስነ-ስዕል ውስጥ ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

   ሀ. እንዲያብረቀርቅ　　　ሐ. በውሃ እንዳይታጠብ ያደርጋል

   ለ. እዳይፈነዳዳ ያደርጋል　　　መ. ሁሊም መልስ ናቸው፡፡

5. ዶክት አሊ ቢራ አፍረን ቀሎ የተቀላቀለበት አመተ ምህረት የትኛው ነው?

   ሀ. 1963 ዓ.ም.　　　ሐ. 1950 ዓ.ም

   ለ. 1971 ዓ.ም.　　　መ. 1965 ዓ.ም

6. አርቲስት እልፍነሽ ቀኖ የትኛው ዞን ውስጥ ተወለደች

   ሀ. ምዕራብ አርሲ ለ. ባሌ ሐ. ምስራቅ ወለጋ

   መ. ምዕራብ ወለጋ

7. ኦቦሌሲ ጋሪን ሲ አሌ ገለታ የሚለው ሙዚቃ በማን ተዘፈነ

   ሀ. እልፍነሽ ቀኖ ለ. አሊ ሸቦ ሐ. ሃሎ ዳዊ መ. አሊ ቢራ

III. ከዚህ በታች በተሰጡት ባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ዪ

1. ______________________________ በ1988 ሀምሌ 24 እ.ኢ..አ አቆጣጠር በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሽሮ ሜዳ ቦታ ላይ ተገድሏል፡፡

2. ______________________________በ 1967 በኢ..አ. አቆጣጠር ምስራቅ ኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሀረማያ ከተማ ተወልዷል፡፡

3. ______________________________ኢትዮጵያ ውስጥ የማስንቆ ሲጫወት ይታወቅ ነበር፡፡

4. ______________________________በ 1930 በኢትዮጵያ አቆጣጠር ጀምሮ የማስንቆ ዜማን በመጠቀም በመዝፈን ይታወቃል፡፡

5. ______________________________በ1950 የድሬደዋ ከተማ ለገ-ሀር በሚባል ስፍራ ተወልዷል፡፡

# ምዕራፍ 4

# የሥነ-ጥበባት መስዕቦች

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ጠቀሜታው፡-

ተማሪዎች የዚህን ትምህርት ክፍል ሲያጠናቅቁ

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ነገሮች ላይ ቀለሞችን በማዘጋጀት ለይታችሁ ታደንቃላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የተዘጋጁ ቀለሞች ስለ አቀባባቸው ትረዳላችሁ
- የተግባር ትምህርት ያለው ጠቀሜታ ትረዳላችሁ
- ሀገር በቀል እውቀት ስራ በስነ-ጥበባት ውስጥ የህብረተሰብ ጠቀሜታ ታውቃላችሁ
- ሀገር በቀል እውቀት በስነ-ጥበባት ስራዎችን ትረዳላችሁ

## መግቢያ

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሰው ልጅ የባህል ቀለሞች በማዘጋጀት ሲጠቀሙበት የነበረ ነው፡፡ ቀለም ለማዘጋጀት የነበሩት፡- የአካባቢያቸው ለማስመር እና የራሳቸው ተፈጥሮ በመቀባት የሚያሳምሩበት ነው፡፡ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የኦሮሞ ዘፋኞች እና ጨፋሪዎች ታሪክ ተምረሃል፡፡ እንዲሁም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሀገር በቀል እውቀት እና ስነ-ጥበባት ትማራላችሁ፡፡

## 4.1 የስነ-ጥበባት ስራ ጥቅም በተግባር ማሳየት

**ተግባር 1. በስነ-ጥበባት ስራ ውስጥ አንዱን በመምረጥ ከአዘጋጃችሁ በኋላ በቡድን ሆናችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ**

ስነ-ጥበብ በህብረተሰብ ውስጥ ያለው ድርሻና ጥቅም የህብረተሰብን በሀል ለማሳወቅ ያለው ትልቅ ነው፡፡ ይሁን እና ከዚህ ውስጥ ትላልቅ ስራዎች እነደ ቀጥተኛ ስርጭት፣የተለያዩ ስብሰባዎች፣የተሌቪዢን ስርጭት፣ የትያትር ዝግጅት፣የዘፈን ቅጅ፣ማህበራዊ ጉዳይ፣በስነ ጥበብ ውስጥ መድረክን ማሳመር፣መሀከለኛ መዝናኛ እና ዘፈን እና ውዝዋዜ የስነ-ጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡ እንደዚሁም በስነ ጥበባት ውስጥ ተከታታይ ግንኙነቶች የምናጠናክርበት፣የምንገልጽበት እና የአኗኗሮች የምናጠናክርበት ነው፡፡

## 4.2 ሀገር በቀል ስነ-ጥበባት ስራዎች

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት ከዚህ ትምህርት ርዕስ በስተ መጨረሻ፡-**

- **በአካባቢያቹህ ያሉት ነገሮች ላይ ቀለሞችን በማዘጋጀት ትገልጻላችሁ፡፡**
- **በአካባቢያችሁ ያሉት ቀለሞች የተዘጋጀበት ጠቀሜታን ትገልጻላችሁ፡፡**

**ውይይት 1 ያለህበት ህብረተሰብ በራሳቸው መንገድ አዘጋጅተው የሚጠቀሙት ቀለም አለ አይተህ የምታውቅ ከሆነ ምን አይነት መልኮች (ቀለም) እና ከምን ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡**

ያዘጋጃችሁት ቀለም ለምን ለምን ይጠቅሙታል እንደ አቀማመጣችሁ በቡድን ተወያዩ እና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

የሰው ልጆች ከጥንት ጀምሮ በቴክኖሎጂ መታገዝ ሳይጀመሩ በፊት በራሱ መንገድ የተለያዩ ቀለማትን በቀላል ዘዴ በማምረት የቀለም ቅብ ስራን እንሚሰሩ ታሪክ ያመለክታል፡፡ እኚህን ቀለማትም ከቅጠሎች፣ አበቦች፣ስራስር፣የእጽዋት ግንድ፣መልክ ያላቸው አፍሮዎች፣ኖራ ድንጋይ፣ ከሰል እና የመሳሰሉትን በማዘጋጀት ለቀለም ቅብ ስራ ይጠቀሙ እንደነበር ይታወቃል፡፡ መሃበረሰባችን ከላይ የተጠቀሱትን ቀለሞች በተለያየ ሁኔታዎች እና ስፍራዎች ላይ ቤታቸውን ለማሳመር ብሎም የተለያዩ ውበቶችን ለመፍጠር እና ሰውነታቸውን ማስዋብ ሲሉ ቀለሞችን አዘጋጅተው ይጠቀሙ ነበር፡፡

በተጨማሪም፡- በተለያዩ ስፍራዎች የቤተ እምነት ስዕሎች፣ ጽሁፎች እና የተለያዩ እምነታዊ መልዕክት ያላቸውን በጣሪያ፣ምሰሶ እና ሌላ የተለያዩ ስፍራዎች ላይ ቀለማትን አዘጋጅተው ይሰሩ ነበር፡፡ ይህን በቀለም ቅብ ከሰሩ በኋላ ደግሞ እንዳይሰነጣጠቅ ወይም በውሃ እንዳይታጠብ የእንቁላል ነጩን ፍሳሽ (ከቅርፊቱ እና አስኳሉ መሀል ያለው) ከተጨቀጨቀ ነጭ ሽንኩርት ውሃ ጋር በማደባለቅ የስዕሉን ውጫዊ ገጽታ ይቀቡት ነበር፡፡ ይህም የስዕሉን ውበት እና ቆይታ ይጨምራል ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ አካባቢያችን በሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች በመጠቀም ቀለማት አምርተን የተለያዩ ጉዳዮች መጠቀም ይቻላል፡፡ ማህበረሰባችንም ከዚህ በታች ያሉትን ቀለማት በማዘጋጀት ስንጠቀምበት ነበር፡፡ እኛም ቀለማትን እንዴት እና በምን ቅድመ ተከተል ስያዘጋጅ እንደነበረ ከዚህ በታች እንመልከት፡-

**ቀይ ቀለም**

ቀይ ቀለምበሁለት (2) ነገሮች ይዘጋጃሉ፡፡ እነርሱም፡-

1. ከቀይ አበባ ላይ ይዘጋጃል
2. ከቀይ አፈር ከሆነ ላይ ይዘጋጃል

ሀ. ቀይ ቀለም ብሩ ቀይ አበባ ከሆነ ላይ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉን ቁሳቁሶች (እቃዎች)

- የአበባ ማስቀመጫ
- ውሃ
- ኩባያ
- ማንኪያ

**አዘገጃጀቱ**

**ከቀይ አበባ**

የአበባው ማስቀመጫ ውስጥ አበባውን በደንብ ማሸት

የተፈለገውን ብርሃን ማገናኘት አለበት

ሁለት ኩባያ ቀይ አበባ ውስጥ አምስት የሻይ ማንኪያ ውሃ መጨመር፡፡

ይህ ማለት እንደ አስፈላጊነቱ ውሃውን መጨመር ወይም መቀነስ እንችላለን፡፡

ከዛ በኋላ የአበባ ቀለም እስከሚይዝ መጨመር ለሦስት ቀን ያህል በማሸግ ቤት ውስጥ ማስቀመጥ

ከሶስት ቀን በኋላ ስዕሉን ማስመሰል ይቻላል፡፡

ለ. ቀይ ቀለም ከቀይ አፈር ላይ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ነገሮች

- የተመረጠ ቀይ አፈር
- ውሃ የምናፈላበት
- ስኳር
- ቀይ አፈሩ የሚፈጭበጥ ነገር (መጅ)

- መጥረቢያ
- ወንፊት

**አዘገጃጀቱ**

1. የተመረጠ ቀይ አፈር  መሆኑን ማረጋገት አለብን፡፡
2. ቀይ አፈርን አንድ ላይ በምናደባልቅበት ግዜ ሌላ አፈር እንዳይደባለቅበት መጠንቀቅ ወይም ሳርና ከሰል ከውስጡ ማጽዳት
3. ተቆፍሮ የወጣውን አፈር በሙቀጫ መውቀጥ ወይም በወፍጮ ድንጋይ ላይ በመጅ በመፍጨት ማድቀቅ
4. የተፈጨውን ወይም የደቀቀውን አፈር በወንፊት መንፋት ትንሽ ጠጠሮች ከውስጡ ማጽዳት
5. በተገኘው እቃ ወይም ብረተማ ነገሮች እንደ በረትድስት እና ማንቆርቆሪያ በመሳሰሉት ውሃውን ማፍላት
6. የደቀቀውን ወይም የተፈጨውን አፈር ንጹህ መሆኑን ከአረጋገጣችሁ በኋላ የተዘጋጀውን ንጹህ አፈር የፈላወን ውሃ ቀስ ብለን በማርከፍከፍ ማዳረስ
7. አፈር እና ውሃውን ከአደባለቅን በኋላ ስኳር እንጨምራለን፡፡
8. 1 ኪ.ግራም አፈር እና ሁለት ማንኪያ ስኳር እንጨምራለን፡፡
9. ስኳሩን እና አፈሩን አብረን ካብላላን /ከደባለቅን/ በኋላ እናቦካዋለን
10. ቀዝቀዝ ያለ ቦታ ውስጥ ከ 24 እስከ 48 ሰዓት እንዲቀመጥ /እንዲቀዘቀዝ/ ማድረግ
11. ከዚህ በኋላ በደንብ ማብላላት እንዲዋሀድ ማድረግ እና የውሃውን ቀለም በመጨመር መጠቀም እንችላለን፡፡

2\. ጥቁር ቀለም

ጥቁር ቀለም፡- ማዘጋጀት የምንችለው ነገሮች እነደ ከሰል፣ምጣድ፣ ሸክላ፣ እና የኩራዝ ጥላሸት የመሳሰሉትን በማዋሀድ ማዘጋጀት እንችላለን፡፡

ጥቁር ቀለም ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች /እቃዎች/ በእንጨት ማማሰል

- ቆርቆሮ
- ኩባያ
- ማንኪያ
- ስኳር
- ውሃ

## አዘገጃጀቱ

1. የምጣድ ጥላሸት፣ኩራዝ እና ጀበና /የብረት ምጣድ፣ኩራዝ አና ጀበና ከመሳሰሉት ላይ በሹል እንጨት እየፈቀፈቃችሁ ሲኒ ውስጥ አስቀምጡ፡፡
2. አንድ ላይ የተቀመጠውን /የተደረገውን/ ከሰል ውሃ በትንሽ ትንሽ መጨመር በእንጨት ማሸት
3. ግማሽ ኩባያ ሻይ ላይ ሰባት ማንኪያ ውሃ መጨመር
4. በደንብ የተብላላውን ከሰል የጸሀይ ብርሃን ላይ ማስቀመጥ፡፡ ምክንያቱም በውስጡ የያዘውን ውሃ እንዲፈላ ይረዳዋል፡፡
5. አሁንም ሁለት ግዜ ትንሽ ውሃ በመጨመር ጸሀይ ብርሃን የሚያገኝበት ቦታ ላይ ማስቀመጥ፡፡
6. በሶስተኛው ቀን መልሰን እዛው ማስቀመጥ አለብን፡፡
7. በሶስተኛው ቀን ውሃ እንጨምራለን፡፡ ከጨመርንም በኋላ በደንብ ማሸት ከአሸን በኋላ አንድ ማንኪያ ስኳር መጨመር ከዛን በደንብ

ስኳሩን ከውሃ ጋር ካሸን በኋላ ወደ ፀሀይ ብርሃን የሚገኝበት ቦታ ላይ ማስቀመጥ፡፡

8. ከዝያም በኋላ በውሃ በማቅጠን መጠቀም ይቻላል፡፡ ቀለሙም ሲደርቅ እንኳን ውሃ በመጨመር ለሳምንት እና ከዚያም በላይ መተቀም ይቻላል፡፡

ጥቁር ቀለምን የምናዘጋጅባቸው ነገሮች እንደ ከሳል፣አሻሮ፣የእጽዋቶች ስራ ስር እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ተግባር 1

ከላይ የተዘረዘሩትን ቀደም ተከተል መከተል ጥቁር ቀለምን መግኘት ከምትችሉት ነገር ላይ በቤታችሁ በማዘጋጀት ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

3. ቢጫ ቀለም

ቢጫ ቀለም ከእርድ ስራ ስሮች ላይ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉን ነገሮች

- ቢላ፣ከተር ወይም መጥረቢያ
- ቆረቆሮ እና ውሃ
- ሙቀጫ ወይም መጅ

## አዘገጃጀትነቱ

1. የአንድ ስር እነደ ድንች ስሮች ስለሆኑ ከመሬት ውስጥ በማውጣት በደንብ ማጽዳት፡፡
2. በደንብ ከአጠባችሁ በኋላ የድንቹን ልጣጭ በቢላ መፋቅ
3. የእርድ ስር እንደ ድንች ስሮች ስለሆነ ከመሬት ውስጥ በማውጣት በደንብ ማጽዳት
4. በደንብ ከአጠባችሁ/ከአጸዳችሁ/ በኋላ የድንቹን ልጣጭ በቢላ መፋቅ ከዚያ በኋላ እንደ ሸንኩርት መቁረጥ እና የጸሀይ ብርሃን ያለበት

ቦታ ማስቀመጥ እሰከ (3) ቀን የጸሀይ ብርሃን ሲያገኝ የነበረውን በአራተኛ (4) ቀን መውቀጥ ወይም መፍጨት፡፡

5. እርድ (መመቆ) ስሮች በደንብ ከወቀጣችሁ ወይም ከአደቀቃችሁ በኋላ በወንፊት መንፋት ከነፋችሁ በኋላ ልጣጩን፣ጸጉሩን እና ስር ያልተፈለጉ ነገሮችን ማጽዳት፡፡
   ውሃውን በደንብ ማፍላት በኋላ የተፈጨውን እርድ (መመቆ) ቀስ በቀስ እንደ ሽሮ በመጨመር እና እንዳይጓጉል በደንብ ማማሰል ወይም ማየት፡፡
6. ቀለም እንዳይቀጥን እና እነዳይወፍር በማየት ውሃውን ቀስ በቀስ ከጨመርን በኋላ በማውታት እንዲቀዘቅዝ ማድረግ፡፡
7. ከዚህ በላይ ያሉትን ቅደም ተከተል ካለፍን በኋላ የቀለም ቅብ ስራ መጠቀም እንችላለን፡፡

### 4 . አረንጓዴ ቀለም

አረንጓዴ ቀለም ከብሳና ቅጠል ወይም የአጸ ፋሪስ ቅጠል ላይ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-

- የድንጋይ ወፍጮ መፍጫ መጅ ወይም ሙቀጫ
- ጎርጓዳ ሳህን
- ኩባያ

## አዘገጃጀት

- የብሳና ቅጠል ወይም የ አጸፋሪስ ቅጠል በአንድ ላይ ማድረግ መውቀጥ
- የተወቀጠውን ቅጠል ጎርጓዳ ሳህን ውስጥ ማስቀመጥ ቀስ በቀስ ውሃውን በመጨመር መጭመቅ
- የብሳና ቅጠል ግማሹን የሻይ ኩባያ ውስጥ ኑስ ውሃ በመጨመር መጠቀም እንችላለን፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ይህ ቀለም ከጥቂት ግዜ በኋላ አረንጓዴ መልክ የያዘ ሲሆን ለመጻፍ ስማይችል መልኩን ወደ አፈር ስለሚቀይር ለመጻፍ አይሆንም፡፡ ይሁን እንጂ፡- ከረጋ በኋላም ውሃ በመጨመር ስዕል ልንስልበት እንችላለን፡፡ ከዚም ውጪ አረንጓዴ ቀለምን ከቅጠላ ቅጠሎች፣ስራ ስሮች፣ከዛፍ ፍሬዎች፣እና የመሳሰሉት ላይ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ነገር ብን አንዳንድ እጽዋቶች በጣም መርዛማ ስለሆኑ መቅመስም ሆነ ወደ አይናችን እና ቆዳችን ማምጣት ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአጭሩ፣ሰዎች ከዱሮ ዘመን ጀምረው ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ከአካባቢያቸው በቀላሉ ማግኘት ከሚችሉት ነገሮች ተጠቀመው ብዙ ቀለማትን ፈጥረው (አዘጋጅተው) ይጠቀሙ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን አንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚጠቀሙት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቤታቸውን፡ አበባዎች እና ጥላሸትን በመጠቀም የተለያዩ ፓተርን (ድግግሞሽ) ሰርተው ያሳምራሉ፡፡

**ተግባር 2**

ቀይ ቀለም፣ቢጫ፣ሰማያዊ፣አረንጓዴ እና የመሳሰሉትን ቀለማትን በአካባቢያችሁ ማግኘት ከምትችሉበት ነገሮች ላይ አዘጋጁና በክፍላችሁ ውስጥ ለሙሉ ተማሪዎች አሳዩ፡፡ በተጨማሪም የዘጋጃቹበትን ቅደም ተከተል እና የተጎናጸፋችሁን እውቀት አቀናብሩና ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

### 4.2.2. ሀገር በቀል የሆኑ የሙዚቃ ስራዎች

ሀ. ሀገር በቀል ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ለህብረተሰቡ ለማቆየት ምን አይነት ጥበቀና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

ለ. የሀገር በቀል ሙዚቃ በአካባቢያችሁ ያለውን ከጻፋችሁ በኋላ በተግባረ አሳዩ

እድገት እና ስልጣኔ በአደገ መጠን የሀገር በቀል ሙዚቃ እንዲጠፋና የህብረተሰቡ ትኩረት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ በሀገር በቀል የአንድ ህብረተሰብ ግንኙነትን የሚያሳይ እና የሚያሳድግ ስለሆነ በቂ ጥበቃ እና እንክብካቤ መደረግ አለበት፡፡ በተረፈ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ የአንድ ህብረተሰብ ማንነት የሚጠብቅ፣ የሚያሳድግ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ  ከማስተላለፍም አልፎበአንድ ብሔር ስሜት መካከል ያውን ለማስተሳሰር እና በማጠናከር  ላይ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

## 4.2.3. የሀገር በቀል የትያትር ስራዎች

የሀገር በቀል እውቀት የህብረተሰብ የባህል አይነት ሲሆን በዓል እና ክብረ በዓላት ላይ ተረት፣ትረካ፣ወግ እና የህብረተሰብ አኗኗር ሁኔታ ካለፈው እና አሁን ካለው የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ የሀገር በቀል የእውቀት ክዋኔ በቀላሉ የድሮ እና የአሁን (ዘመናዊ) በመባል መመደብ አይችልም፡፡ ግን ሀገር በቀል አውቀት ባህላዊ ልማዶችን መሰረት በማድረግ በሚኖሩበት ህብረተሰብ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ነው፡፡

የሀገር በቀል እውቀት ክዋኔ ከዚህ በታች ባለው መግለጽ ይቻላል፡፡ አነሱም፡-

- ጭውውት
- ውዝዋዜ
- ክዋኔ
- ዝግጅት

የሀገር በቀል እውቀት ክንዋኔ ፎርምና ድራማ ዝግጅት ሁኔታ ከውስጡ አለው፡፡ እነርሱም ፡-

የመንገድ ላይ ትያትር

- ጽሁፍ
- ክብረ በዓል
- የውዝዋዜ ክወና
- የድራማ ክወና
- ፌስቲ ቫል /በዓል/

በአጠቀላይ የሀገር በቀል እውቀት ክዋኔ የተለያዩ ባለሞያዎችን በማሳተፍ የሚሰራ ነው፡፡

የሀገር በቀል ክወና ማሳያ ከስነ ጥበባት አይነት በብዛት በውስጡ ይይዛል፡፡ ከእነረሱም ውስጥ ሙዚቃ፣ተቀናጀ ተውኔት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የሀገር በቀል ዕውቀት ክዋኔ ባህሪ

የሀገር በቀል እውቀት ማሳያ ሀገራት እና በተለያዩ ብሄረሰብ ውስጥ በመሰራጨት አንድ የህብረተሰብ ባህል በማስተዋወቅ እና በማስፋፋት ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

ትላልቅ የሀገር በቀል አውቀት ማሳያ ሀገራት እና በተለያዩ ብሄረሰብ ውስጥ በመሰራጨት የአንድን ህብረተሰብ ባህል በማስተዋወቅ እና በማስፋፋት ውስጥ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ትላልቅ የሀገር በቀል እውቀት ክዋኔ ባህሪያት በመባል የሚታወቁ፡-

- ባህል እና ህገ-መንግስት ማሳደስ እና ማስተማር
- ክብረ በአላት
- ትረካ ወግ /ተረት/
- የአንድ ህብረተሰብ ቋንቋን ማሳደግ
- ማዝናናት
- የግለሰቦችን ልምድ ማቆየት /መቅረጽ/ እና ማሳየት፡፡

- ከሀገር በቀል እውቀት ልምድ ጋር አብሮ መቆየት እና ግልጽ ማድረግ፡፡
- የአንድ ህብረተሰብ የሀገር በቀል እውቀት ለሰፊው ህዝብ ማሳየት፡፡

የሀገር በቀል እውቀት ክዋኔ የባህል ቅረሶች ከነበረው እና ወደ ፊት መምጣት የሚችሉትን የምናሳይበት ዘዴ ነው፡፡ የሀገር በቀል እውቀት ክዋኔ በተለያየ ቦታ ሊካሄድ የሚችል ሲሆን በትያትር አዳራሽ እና በመንገድ ላይ ሊታይ የችላል፡፡

ባለፉት ክፍል ውስጥ እንደተማራችሁት የሀገር በቀል ክወና የባህል ድራማ በመባል ይታወቃል፡፡ ስለኢህ ይህ የባህል ድራመ የባህል ቅርሶች እንደ ዜማ/መዝሙር፣ውዝዋዜ፣ትረካ ወይም በአንድ አይነት ላይ የተመሰረት መተረክ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በመሰረታዊ መመዘኛ ላይ የተመሰረተ የባህል ቅርሶች መጠበቅ ይቻላል፡፡

እነዚህ መመዘኛዎችም፡-

- የሀገር በቀል ጥበቃ
- ማብራሪያ፣ሙሉነት፣እውነተኛነት
- በራስ ምስጢር መተማመን
- ባህርይ
- የጠፋን ባህል መመለስ
- የባህል ቀጣይነት

ከዚህ በመቀጠል አንዳንድ መሰረታዊ ከዚህ ስር የቅርሶች ተጠቀሚነት የባህል መሳሪያዎች እና የተዋንያን ግንኙነት ፕሮፋይልን የሀገር በቀል እውቀት እና በህብረተሰብ ማካከል ያለውን እንመለከታለን፡፡

## ከበሬታ

ማንኛውም በሀገር በቀል እውቀት ላይ የሚሠራ ሰው የባህል ቅርስ መሳሪያዎች እና የህብረተሰቡን እውቀት ማክበር አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ከበሬታ የሚባለው መመዘኛ መከተል አለበት፡፡ ሌላኛው የሀገር በቀል እውቀት በዚያ ሀገር ውስጥ ያለውን በመውሰድ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በባህል ፣በፌሰቲቫል ወይም ማሳያ በማዘጋጀት በአቀድነው ግዜ የሀገር ሽማግሌ ማንነት ወይም ልዩ ችሎታ ያላቸውን ማግኘት አለብን፡፡

ማንነትን ካገኘን በኋላ በሚታይ ቦታ እና በሚፈጸምበት ቦታ ሁሉ ለሀገራቱ የባህል ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች እውቅና መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የሀገር በቀል ባህል አስፈላጊነት የሀገር በቀል እውቀት መተካት ይቻላል፡፡ የባህል ልዩነት በመውሰድ እና በማክበር የሀገር በቀል እውቀት ማሳያ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

## የሀገር በቀል እውቀት ጥበቃ

አንድ ህብረተሰብ ባህል እና የባህል ቅርሶች መሳሪያ ላይ ለመወሰን ሙሉ መብት አለው፡፡ በድራማ እድገት እና ስራ ውስጥ የህብረተሰቡ መብት የሚከበሩበት ዘዴዎች ብዙ ናቸው፡፡ ይህም በድራማ ስራ ውስጥ ማን ነው የሚተካው ብለው መለየት፣በትክክል እውቀት ያላቸውን መለየት፣መረጃ በመሰብሰብ የባህል ቅርሶች፣መሳሪያዎች የተለያየ ትርጉም ስላላቸው በማሳያ ውስጥ የምንጠቀምባቸው መለየት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## የባህላዊ ድራማ ክወና

በባህላዊ ድራማ ማሳያ ወይም የሀገር በቀል እውቀት ለስራው እውነተኛነት እና ሙሉነት ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ለምሳሌ፡- ዜማ በሚዜምበት ግዜ ወይም በሀገር በቀል እውቀት ሲታይ በህብረተሰቡ

ቋንቋ እና ባህል መሆኑ የዜማ ባህርይ ወይም ባህሉ እንደለው ማቅረብ፣ ለማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት እንደየ አገባባቸው ማስተላለፍ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

## የሀገር በቀል ዕውቀት አስፈላጊነት

የሀገር በቀል ዕውቀት በኢኮኖሚ ፣ ማህበረሰብአዊነት እና በባህላዊ ዘርፍ ትልቅ ጥቅም አለው፡፡ የሀገር በቀል ዕውቀት ክወና ቲያትር በሚቀየርበት ግዜ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ጥቅሞች በትክክል መግለጽ ይቻላል፡፡

ሀ. የሀገር በቀል እውቀት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ትቅም

የሀገር በቀል ዕውቀት በትያትር በማሳየት፣ እንደ ስነ-ጥበባት ሌላ ገቢ ማግኘት ይቻላል፡፡ የሚገኘው ገቢ ከግለሰብ ጥቅም ጀምሮ ከመነሳት ህብረተሰብ እና በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

ለ. የሀገር በቀለል እውቀት ማሳያ የሆኑ የህዝብ ግንኙነት እና ማህበረሰብ መካከል ያለውን ያጠነክራል፡፡

ከዚህም ሌላ የሀገር በቀል ዕውቀት ባለሙያ (የባህሉ ባለቤት የሆኑትን) በማገናኘት ብንኙነትን ያጠናክራላል፡፡

አንዱ ህብረተሰብ ሌላውን እንዲያከብር ትልቅ ሚና/ድርሻ አለው፡፡

የስነ-ጥበባት ሥራ ሰው በሰውነቱ እኩል አድርጎ ስለሚያሳትፍ በሀገር በቀል ዕውቀት ክወና ውስጥ አካል ጉዳተኞች፣ሴቶች፣ወጣቶች፣ሕጻናት እና ሽማግሌዎች ሁሉ በእኩልነት ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ ስለዚህ ያደገ ማህበረሰባዊነት፣እኩልነት በመንግስት ውስጥ ትልቅ ሚና አለው፡፡

ሐ. የሀገር በቀል ዕውቀት በባህል ውስጥ ያው ጥቅም

የሀገር በቀል ስራዎች እንደአየናቸው በአጠቃላይ በህብረተሰብ ባህል ላይ የመሰረታል፡፡ ስለዚህ አንድ የህብረተሰብ ባህል በመድረክ ላይ

ማሳየት የህብረተሰቡን ባህል እና እውቀት ለዓለም ማሳየት እና ማሳደግ ውስጥ ትልቅ ሚና/ድርሻ አለው፡፡

## ምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

- ለረጅም ዓመት የቀለም አቀባብ ስራ እየሰሩ የነበሩ የተለያዩ የራሳቸው ቀለም ከአካባቢያቸው በቀላሉ ከሚገኙ ነገሮች ላይ በማዘጋጀት ይሰሩ እንደነበር ታሪክ ይገልጻል፡፡
- የቀለም አቀባብ ለእምነት ወይም ሀይማኖ ጉዳይ በጥንት አመት ውስጥ እንዳይሰነጠቅ እንቁላል እና ነጭ ሽንኩርት በመጨቅጨቅ ከውሃ ጋር በመደባለቅ በድጋሜ ቀለም ይቀቡ ነበር፡፡
- ከአካባቢያችን ከሚገኙ ለይ በተለያየ ሁኔታ ቀለምን በማዘጋጀት ለተለያዩ ነገሮች መጠቀም ይቻላል፡፡
- ቀይን ቀለም ከቀይ አፈር ማዘጋጀት ይቻላል፡፡
- ጥቁርን አፈር የተለያዩ ከሰሎችን እንደ ምጣድ፣ማሰሮ እና ከኩረዝ ጭስ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡
- የሀገር በቀል እውቀት ከህብረተሰብ የባህል አይነት አንዱ ነው፡፡
- የሀገር በቀል ማሳያ እና ክወና ብዙ የስነ-ጥበባት ዓይነቶች በውስጡ አለው፡፡
- የባህልን ልዩነት መውሰድ እና ማክበር በሀገር በቀል እውቀት ማሳያ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

### የምዕራፍ አራት መልማጃ

I. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ቀይን ቀለም ከሁሉም አበባዎች ማዘጋጀት ይቻላል፡፡
2. ብጫን ቀለም ከመቅመቆ ሥር ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

3. አረንጓዴን ቀለም ከብሳና ቅጥል ከአጻፋሪስ ማዘጋጀት አይቻልም፡፡
4. የሀገር በቀል ዕውቀት ስነ-ትያትር ጋር ግንኙነት አለው፡፡
5. እሬቻ የሁሉም ህዝብ ሀገር በቀል እውቀት ነው፡፡

## II. ከዚህ በታች ያሉትን ጥቃቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ቀለማትን ለማዘገጀት የሚያገለግለው የቱ ነው?

   ሀ. አበባ ለ. የእጽዋት ስር ሐ. አፈር መ. መልስ አልተሰጠም

2. ቀይ ቀለምን በባህላዊ ዘዴ ለማዘጋጀት የሚያገለግል የትኛው ነው?

   ሀ. ከሰል ለ. አፈር ሐ. ቅጥል መ. አበባ እና አመድ

3. ጥቁርን ቀለም ለማዘጋጀት ከዚህ በታች ካሉት ውስጥ የሚያገለግል የትኛው ነው?

   ሀ. ምጣድ ለ. ማሰሮ ሐ. ጭስ መ. ሁሉም

4. የሀገር በቀል እውቀት ክወና በምን ሁኔታ መግለጽ ይቻላል፡፡

   ሀ. በተውኔት ለ. በውዝዋዜ ሐ. በክወና መ. ሁሉም

5. የቱ የስነ -ትያትር የሀገር በቀል ዕውቀት ጥቅም አይደለም

   ሀ. ኢኮኖሚን ማሳደግ ለ. የህዝብ ባህል ማስፋፋት ሐ. የህብረተሰብ ፖለቲካ መግለጽ መ. የአንድን ህብረተሰብ እሴት ማሳት

6. ሀገር በቀል እውቀት ትወና ባህርይ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ክብረ በአላት ሐ. ማዝናናት

   ለ. የአንድን ህብረተሰብ ቋንቋ ማሳደግ መ. ሁሉም

# ምእራፍ አምስት

# የስነ - ጥበባት ትስስር

**የዚህ ትምህርት ምዕራፍ ውጤት**

**በዚህ ትምህርት ምዕራፍ መጨረሻ**

- የስነ-ውበት ሙያ ይለዩ
- ከሸክላ አፈር የተለያዩ ነገሮችን ይሰራሉ፡፡
- የስነ-ጥበባት ግንኙነት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን ይረዳሉ፡፡

## በግቢያ

የሸክላ አፈር የተለያዩ አይነት አለው፡፡ በዓይነቱ ላይ በመመስረት ጥቀሙንና የስራው ቅደም ተከተል መጠቀምን ይይዛል፡፡ በተጨማሪም የተለያየ ጥንካሬ ደረጃ ስላላቸው የሚውሉበት አገልግሎት የተለያየ ነው፡፡እንዲሁም ከስነ-ጥበባት ትምህርት ጋር ያለው ግንኙነት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

## 5.1 የሸክላ ስራና ማሳመሪያ ሙያ ቅደም ተከተል

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

**በዚህ ትምህርት ርዕስ መጨረሻ**

- ለሸክላ አፈር ስራ ዓይነቶች የሚውሉትን ይረዳሉ፡፡
- የሸክላ አፈር ስራ ማምረቻ ሁኔታ እና ማሳመሪያ ይናገራሉ፡፡

## 5.1.1.የስነ-ጥበብ ጌጣ ጌጥ /Decoration/

የሥነ-ጥበብ ጌጥ ከስነ-ጥበብ የስራ አይነት ዲዛይን እና ማስዋቢያ መሳሪያዎች ጋር ትስስር ያለው ሆኖ በተለይ እነኚህ የጌጣ ጌጥ እቃዎች ያላቸው ጥራት በይበልጥ ጥቅም ያላቸው እና ዋጋ ያላቸው የሆኑ ማለት ነው፡፡

የጌጣ ጌጥ ስነ-ጥበባት የስነ-ጥበብ ወይም የእጅ ስራ መሳሪያዎች ዲዛይን እና ለጌጣ ጌጥ ማምረቻ የሚያገለግሉ በሆኑ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የጌጣ ጌጥ ስነ-ጥበብ በህንጻ ውስጥ እና ውጪ ያሉ የተለያዩ ዲዛይኖች በማስዋብ/በማስጌጥ መስራት ነው፡፡ ለህንጻ መሳሪያ ማስዋቢያ ለተለያዩ ዲዛይኖች የሚውሉ እንደ የሸክላ ስራ፣የብረታ ብረት ስራ፣የእንጨት ስራ፣የተለያዩ ጌጣ ጌጦች ስራ፣የሽመና ስራ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 5.1.1.1. የሸክላ ማምረቻ ማስዋቢያ

ለሥነ-ጥበብ ማስዋቢያ /ማሳመሪያ/ ማምረቻ የሆኑ ነገሮች በሁለት መንገድ የሚሰራ ነው፡፡ ሌላው አንዱ ከሸክላ የተሰሩ በእሳት ሳይሚሹ እና ከተሚሹ በኋላ የሚሰራ ነው፡፡ ስለዚህ ለሸክላ ስራ ማምረቻ የሆኑ እንደ ልዩነታቸው መዋብ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ከማስዋቢያ ቅደም ተከተሎች ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

- ቀለም መቀባት
- ማብረቅረቅ
- ማለስለስ
- ቫርንሽ መቀባት

## ሀ. ቀለም መቀባት

ቀለምን በመጠቀም ከሸክላ አፈር መሳሪያዎች የተሰሩ በማስዋብ በታሪክ መጀመሪያ ዓመት እየተሰራ የነበረ እና በጣም የታወቀ ነው፡፡ በመጀመሪያ መሳሪያው በእሳት ከተሟሸ በኋላ ቀለምን በመጠቀም የተለያዩ ነገሮች በላዩ ከተሰራ እና ከተዋበ በኋላ እንዲያብረቀርቅ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የተለያዩ ቀለማት መቀየር ይቻላል፡፡

## ለ. ማብረቅረቅ

የሸክላ አፈር ማስዋቢያ ዘዴ የሚሠራበት አንዱ እና የተለመደ ነው፡፡ በእሳት ስለሚሟሽ በጣም ከመጨማደዱ ውሃን በስውስጡ መምጠት ስለማይችል ከሸክላ መሳሪያ ከሚሠሩ በቀላሉ እንዳይሰበር ያደርባል፡፡

## ሐ. ማለስለስ

ቢላዋ እና ቀለል ያሉትን የተለያዩ መሳሪያዎች በመጠቀም ከሸክላ አፈር የተሰሩትን በማለስለስ የተለያዩ ዲዛይን መስራት፣ ማሳመር ይቻላል፡፡ በይበልጥ ይህ ዘዴ ከሸክላ አፈር ላይ የተሰራ እና ያልደረቀ ቢሆን ጥሩ ይሆናል፡፡

## መ. ቫርኒሽ መቀባት

በመጀመሪያ በእሳት ከተሟሸ በኋላ የሚያስፈልጉትን ነገሮች በሚሰራበት ጊዜ በመስሪያው ላይ ያለው ድንጋይ፣እንጨት እና ብረት በመታገዝ በትክክል ካለሰለስን ወይም ከፈገፈግን በኋላ ቨርኒሽ ይቀባል፡፡

## 5.2 የስነ-ትያትር ትምህርት ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነት

ውይይት 1

የስነ-ጥበብ ትምህርት ከሌሎች ትምህርት ጋር ያለውን ግንኙነት እና ጥቅም በየቡድናችሁ ተወያዩበት፡፡ የስነ ጥበብ ትምህርት ከሌሎች ትምህርት ጋር ያለው ትስስር ማለት የስነ-ጥበባት ግንኙነት (ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ ስነ-ጥበብ እና የመሳሰሉት) ከሌሎች የትምህርት አይነት ማለትም ሂሳብ፣የተፈጥሮ ሳይንስ፣የህብረተሰብ ሳይንስ ቋንቋ እና ከመሳሰሉት ጋር ያለው ነው፡፡

የስነ-ጥበብ ትምህርት ጥቅም ከሌሎች የትምህርት አይነት መማሪያ ሆነ ማስተማሪያ ወስጥ ያለው ብዙ እንደሆነ ተምራችኋል፡፡ በአንደኛ ትምህርት ደረጃጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ባለው ውጤታማ በማድረግ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ /ሚና/ አለው፡፡ የስነ ጥበብ ጥቅም ከሌሎች የትምህርት አይነት ማስተማር ውስጥ ያለው ለምሳሌ የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት እና የህብረተሰብ ሳይነስ በማስተማር ውስጥ ምሳሌ ወስደን እንመልከት፡፡

### በአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ይዘት ውስጥ

ለምሳሌ በአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ከ1-4 ክፍል የሚማሩበት ይዘት ትምህርት ውስጥ አንዱ ስለ ሰውነት ህዋሳት ነው፡፡ ይህን የዘት ተማሪዎችን ለማስረዳት የሰውነት ህዋሳትን የሚያሳይ ስዕል በማሳየት የተማሪዎቹን ስለሰውነታቸው ህዋሳት እና የሰውነት ህዋሳት ጥቅም ያለውን ማስረዳት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም አጠቀላይ ሳይንስ ውስጥ ስለ ምግብ ስርዓት ማብላያ አካል መዋቀር፣የሰው ልጅ አጥንት መዋቀር፣የሰው ልብ መዋቀር፣የሳንባ

መዋቀር፣የኩላሊት መዋቀር፣የአእምሮ መዋቀር እና የመሳሰሉት በማስተማር በቃል ብቻ በመጠቀም የምናስተምር ከሆነ ሊከብድ ይችላል፡፡ ይህም እየአንዳንዱን በስእል ላይ በመመልከት በሚማሩበት ጊዜ በቀላሉ መረዳት ይችላሉ፡፡

እንደ አካባቢ ሳይንስ ከ 1-4 ክፍል በሚማሩበት ውስጥ ስለ አካባቢያቸው ማወቅ ነው፡፡ አካባቢያቸውን ማወቅ ስንል ቀበሌ፣ወረዳ እና ክልል እያሉ ደረጃቸው ይሄዳል፡፡ በዚህ ውስጥ ስዕል ወይም ካርታን በመጠቀም ተማሪዎች እንደ የቦታ ግኝት ወይም ወረዳ፣ዞን እና ክልላቸውን እንዲረዱ በማድረግ ተማሪዎች በይበልጥ አካባቢያቸውን እንዲሁም የወረዳዎች አቅጣጫ፣ዞን እና ክልሎች ከሌሎች ትምህርት ቤት ካሉት በላይ መረዳት እንችላለን፡፡ በአጠቀላይ የሳይንስ ትምህርት ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ የተማሪዎች የትምህርት ይዘት እየጠነከረ የሚሄድ እና ከአካባቢያቸው የሚገናኝ ወይም አዲስ ነገር ለመማር የሚካሄድ እና የተለያየ ስዕልን እና ካርታዎች መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የአየር ብክለት፣የአለም፣የመሬት ክፍሎች፣የውሃ ገጽታ የአፍሪካ ሕብረት እና መአድን የመሳሰሉትን ለመምህራችሁ በማስረዳት ስዕል ወይም ካርታ በመጠቀም በስነ-ጥበብ ውስጥ ከሌላ ትምህርት በላይ ለማሳደግ ያለው ድርሻ ትልቅ ነው፡፡

ስነ-ጥበብ ከሌላ ትምህርት አይነት ጋር ያለውን ነገር ምን ብለህ ትገልጻለህ?

**ተግባር**

**የሙዚቃ ትምህርት ድርሻ ከሌላው ትምህርት ጋር ያለውን ነገር በማያያዝ እና ምሳሌዎችን በመውሰድ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ**

ሀ. የሂሳብ እና ሙዚቃ

ለ. የቋንቋ እና ሙዚቃ

ሐ. የአካባቢ ሳይንስ እና ሙዚቃ

መ. ስፖርት እና ሙዚቃ

ሰ. ሳይንስ እና ሙዚቃ

## 5.3 ትያትር ከጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ጋር ያለው ትስስር

ስነ-ጥበባት ከብዙ ትምህርት አይነቶች ጋር ህብረት አላቸው፡፡ ይህ ማለት ስነ-ጥበባትን በመጠቀም እያዝናናን ማንንም ሳይሰለች ማስትማር እንችላን፡፡ ስለዚህ በዚህ ርዕስ ስር ትያትር ከጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ጋር ያለውን ግንኙነት እንማረለን፡፡ አንድ የትያትር-ተውኔት ጽሁፍ ተጽፎ ለተዋናይ ከተሰጠ በኋላ ለተመልካች ለመድረስ ብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ ያልፋል፡፡ በልምምድ ሂደት ውስጥ መድረክ ላይ ከመውጣት በፊት ሰውነታቸውን ቅድሚያ ያሟሙቃሉ፡፡ ሰውነታቸውን ከአሟሟቁ በኋላ ድምጻቸው ጠርቶ እንዲሰማ የሰውነት እንቅስቃሴ እና የድምጽ ልምምድ መስራት አለባቸው፡፡ በፊልም እና የትያትር

ልምምድ ስራ ውስጥ ተዋናዮች ወደ መተወን ከመግባታቸውበፊት ሰውነታቸውን ያጠናክራሉ፣ያፍታታሉ፣እንደ ፍላጎት ሰውነታቸውን ለማዟዟር ሲባል እንቅስቃሴን ያደርጋሉ፡፡

አንድ ተዋንያን ገጸ ባህሪን ለመተካት በሰውነቱ፣ድምጹ እና ሁሉንም የሚተውነውን ገጸ-ባህሪን መስሎ (ሆኖ) ለመገኘት የሰውነት እንቅስቃሴ ማድረግ አለበት፡፡ ስለዚህ ተዋንያኖች እንቅስቃሴን ማድረግ አለባቸው፡ ፡ ይህም እነደፈለጉ የተረለገውን ገጸ-ባህሪ እንዲጫወቱ ይረዳል፡፡

ሰውነት ማሟሟቅ

መሰረታዊ እንቅስቃሴን ከመጀመራችን በፊት ሰውነት ማሟሟቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰውነት ሳይሟሟቅ እንቅስቃሴን በከባድ ሁኔታ መጀመር አካላዊ ጉዳት እና ሰውነት በሚፈልገው ልክ በተግባሩ እናዳይወጣ ያደርገዋል እንደ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም የሰውነት ማሟሟቂያ እንቅስቃሴን ማድረግ የተለያዩ ጠቀሜታ አሉት፡፡ እነሱም፡-

- የሰውነት ሙቀት መጨመር ሰውነታችን እንዲታዘዝ ያደርጋል
- ቀጥሎ ለሚመጣው(ለሚቀጥለው) ድርጊት በሰውነትም ሆነ በአእምሮ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡
- ሰውነት ጉልበትን የሚያዘጋጅበትን ፍጥነት ይጨምራል (Energy Production)
- የሰውነታችን ጡንቻዎች ስራን የማስፈፀም አቅማቸው ይጨምራል፡፡
- የልብ ምትን በመጨመር ለሰውነታች ክፍሎች የሚያደርሰውን የደም መጠን በመጨመር ሰውነታችን የመስራት ሀይልን ያጎለብታል፡፡ ሰውነታችን እንዲፍታታና ከፍተኛ መነሳሳት እንዲኖረው በማድረግ የትወና ፍላጎት እና አቅምን ይጨምራል፡፡
    - ✓ በአጠቃላይ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ለተዋንያን
    - ✓ ድምጽን ያጠራል (ቅላጼን ያሳምራል)

- ✓ ጡንቻን ያፍታታል
- ✓ ጡንቻን ያጠነክራል
- ✓ በደስታ እንዲተውኑ ያደርጋል
- ✓ ሰውነታቸው እንዲነቃቃ በማድረግ ወደ ፍላጎት እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል
- ✓ የአእምሮ ጭንቀትን ያስቀራል፡፡
- ✓ የሰውነት ፍላጎታቸውን እንዲገልጹ ያደርጋል
- ✓ የሰውነታቸውን ሚዛን እንዲጠብቁ ይረዳል
- ✓ ሰውነታቸው ጤናማ፣የተረጋጋ እና የሚታዘዝ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
- ✓ ሰውነት እንዳይጎዳ ያደርጋል

**ማጠቃለያ**፡- ጭንቅላት (አእምሮ)፣አይን፣እጅ፣እግር፣ሳንባ፣ድምጽ፣ጀርባ፣ አንገት፣ጭንቅላት፣ምላስ፣አገጭ(መንጋጋ) እና የመሳሰሉት ሁሉ የትያትር ጨዋታዎች ትልቅ ስለሆነ የሰውነት እንቅስቃሴ ማሰራት የተሻለ ነው፡፡